www.chilot.me

# የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች

www.chilot.me

C-2 ~~342~~

2 ~~120~~

~~358~~
361

SUPREME COURT
LIBRARY

www.chilot.me

# የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች

እስከ ጳጉሜ ፭ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.
በሥራ ላይ ያሉ ብሔራዊ ሕጎች።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት
SUPREME COURT LIBRARY
ቤተ መጻሕፍት

## ፪ኛ መጽሐፍ

(ክፍል ፳-፴፫)

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ተባባሪነት

በ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ
የሕግ ፋኩልቲ
ተዘጋጀ

፲፱፻፷፪ ዓ. ም.

የፕሮጀክቱ ዲሬክተር
ዊልያም ኤች ዩዊንግ

ረዳት ዲሬክተር
በየነ አብዲ

www.chilot.me

የእትሙ ባለመብት
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ
የሕግ ፋኩልቲ

ይህን መጽሐፍ በሙሉ ወይም በከፊል በማናቸውም
መልክ ያለባለመብቱ ፈቃድ ማራባት ክልክል ነው

በአዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ
ሴንትራል ማተሚያ ቤት
ታተመ

፲፱፻፶፭ ዓ. ም.

www.chilot.me



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለምክር ቤት ንግግር ሲያደርጉ

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት

www.chilot.me

# የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች

## አጭር ማውጫ

### ፩ኛ መጽሐፍ

### የመግቢያ ጽሑፎች

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩. | መቅድም ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | ፭ |
| ፪. | አጭር ማውጫ (ሳመሪ ኦፍ ኮንቴንትስ) ... ... ... ... ... ... ... ... | ፮ |
| ፫. | የአርእስት ማውጫ (ቴብል ኦፍ ኮንቴንትስ) ... ... ... ... ... ... ... | ፱ |
| ፬. | የተጠቃለሉ ሕጎች አጀማመርና አሠራር ... ... ... ... ... ... ... ... | ፲ |
| ፭. | ምስጋና ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | ፲፮ |
| ፮. | የተጠቃለሉ ሕጎች አጠቃቀም ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | ፲፰ |
| ፯. | የምሕጻረ ቃላት ዝርዝር ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | ፳፮ |


### ሕጎቹ


| | | |
|---|---|---|
| ፩. | የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት ቃል ኪዳን ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 1 |
| ፪. | የኤርትራ ግዛት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ጋር መቀላቀል ... ... | 37 |
| ፫. | የሚኒስቴሮች አቋም ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 56 |
| ፬. | ፓርላማና ምርጫ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 77 |
| ፭. | ፍርድ ቤቶችና ፍርድ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 94 |
| ፮. | የጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 136 |
| ፯. | የውስጥ አስተዳደር ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 178 |
| ፰. | የመንግሥት አገልግሎት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 201 |
| ፱. | ዜግነትና የውጭ አገር ሰዎች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 263 |
| ፲. | መከላከያና የጦር ኃይሎች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 275 |
| ፲፩. | የባሕር ጉዳዮች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 304 |
| ፲፪. | ያገር ውስጥ ፀጥታ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 330 |
| ፲፫. | ማስታወቂያና ሳንሱር ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 372 |
| ፲፬. | መመርመር (ኦዲት) እና መቆጣጠር ... ... ... ... ... ... ... ... | 382 |
| ፲፭. | ባንኮችና ገንዘብ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 387 |
| ፲፮. | ጉምሩክ ፤ የገቢና የወጪ ዕቃዎች ታክስ ... ... ... ... ... ... ... ... | 429 |
| ፲፯. | ታክስ (ከጉምሩክ ሌላ) ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 562 |
| ፲፰. | የመንግሥት ዕዳ ሠነዶች (ቦንድ) ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 695 |
| ፲፱. | የኤኮኖሚ ዕድገትና ፕላን ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 710 |


### ፪ኛ መጽሐፍ


| | | |
|---|---|---|
| ፳. | በመንግሥት ሥር የሚካሄዱ ሥራዎችና የኤሌክትሪክ ኃይል ... ... ... ... | 738 |
| ፳፩. | ትራንስፖርትና መገናኛዎች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 753 |
| ፳፪. | ፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 865 |
| ፳፫. | ንግድና ኢንዱስትሪ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 902 |
| ፳፬. | እርሻ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... | 950 |

www.chilot.me



ገጽ

## ክፍል ፴፫

## ስለሽልማቶች ስለክብር እና ስለሜዳዮች


፩. የአርበኞች ሜዳይ ፲፱፻፳፰—፲፱፻፴፫ ፬/፫ (፲፱፻፴፯) ድ. ፬ በ፲፩/፯ (፲፱፻፵፩) ድ. ፲፩ ፤ በ፲፩/፯ (፲፱፻፵፩) ማ. ፳፱ እንደታረመ ተሻሻለ፤ 1300

፪. ለጦር ሠራዊት ሰንደቅ ዓላማ መሸለም
፬/፭ (፲፱፻፵፭) ድ. ፭ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 1302

፫. የሜዳዮች ደንብ
፲፩/፮ (፲፱፻፵፩) ድ. ፲ በ፲፩/፮ (፲፱፻፵፩) ማ. ፳፱ ታረመ ፤ ፲፩/፯ (፲፱፻፵፩) ድ. ፲፭ ፤ በ፲፩/፲ (፲፱፻፵፬) ድ. ፲፬ ፤ ፲፯/፲ (፲፱፻፵፱) መ. ፪፻፳፭ ፤ ፲፯/፲፬ (፲፱፻፵፱) ድ. ፳፩ ፤ ፲፯/፲፩ (፲፱፻፶) መ. ፪፻፴፰ በግ. ሳ. ተሻሻለ። ... ... ... ... ... ... 1303

፬. ስለኮሪያ ሜዳይ መቋቋም የወጣ ደንብ
፲፩/፮ (፲፱፻፵፬) ድ. ፲፪ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 1307

፭. ስለኒሻኖች
፲፫/፲፬ (፲፱፻፵፮) ድ. ፲፭ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 1308

፮. ስለፖሊስ የአገልግሎት ሜዳይ
፲፯/፲፬ (፲፱፻፵፱) ድ. ፳፩ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 1315

www.chilot.me



## የምሕፃረ ቃላት ዝርዝር

| | |
|---|---|
| ሕ. | የሕግ ክፍል ማስታወቂያ |
| መ. | የመንግሥት ማስታወቂያ |
| መሠ. ማስ. | የመሠረዣ ማስታወቂያ |
| ማ. | ማረሚያ |
| ማስ. | ማስታወቂያ |
| ማጽ. ማስ. | የማጽደቂያ ማስታወቂያ |
| ሠን. | ሠንጠረዥ |
| በተ. የ. | በተለይ የወጣ |
| በግ. ሳ. | በግልጽ ሳይነገር |
| ተ. | ተጨማሪ |
| ት. | ትዕዛዝ |
| ን. ሕ. | የንግድ ሕግ |
| አ. | አዋጅ |
| የአ. አ. | የአዲስ አበባ |
| የኢት. | የኢትዮጵያ |
| ወ. መ. ሕ. | የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ |
| ወ. መ. ሕ. ሥ. ሥ. | የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት |
| ድ. | ድንጋጌ |
| ፍ. ሕ. | የፍትሐ ብሔር ሕግ |
| ፍ. ሕ. ሥ. ሥ. | የፍትሐ ብሔር ሕግ ሥነ ሥርዓት |

www.chilot.me



፩/ «የኮንስትራክሽን ሥራ ጨረታዎች አጥኚ ኮሚቴ» ማለት በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሰው ኮሚቴ ማለት ነው ።

፪/ «የኮንስትራክሽን ሥራ ኮንትራት» ማለት የኮንስትራክሽኑን ሥራ ዕቅድ ለመሥራት ከተመረጠው ተጫራች ጋራ የተደረገ ኮንትራት ማለት ነው ።

፫/ «የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ» ማለት ማናቸውም አዲስ የኮንስትራክሽን ሥራ ወይም አስቀድሞ ያለውን የኮንስትራክሽን ሥራ ማሻሻል ፣ ማስፋፋት ወይም በሰፊው ማደስ ማለት ነው ።

፬/ «የአማካሪነት ስምምነት» ማለት በኮንስትራክሽኑ ሥራ ዕቅድ በማናቸውም የሥራ ደረጃ የሞያ አገልግሎት ስለመስጠት በሚኒስቴሩና በቴክኒክ ዐዋቂዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ማለት ነው ።

፭/ «ተቋራጭ» ማለት የኮንስትራክሽኑን የሥራ ዕቅድ እንዲሠራ የተመረጠ የኮንስትራክሽን ሥራ ኮንትራት ያለው ተጫራች ማለት ነው ።

፮/ «የመጨረሻ የሥራ ዕቅድ» ማለት ሚኒስትሩና አሠሪው ባለሥልጣን የተስማሙበት የመጨረሻው የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ የሥራ ዝርዝር ማለት ነው ።

፯/ «መንግሥት» ማለት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ማለት ነው ።

፰/ «ሚኒስትር» እና «ሚኒስቴር» ማለት እያንዳንዳቸው የሥራ ሚኒስትርና ሚኒስቴር ማለት ነው ። ይኸውም በዚህ ደንብ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የተሰጣቸውን ሥራ ለመፈጸም በተለይ የተፈቀደላቸውን የሚኒስቴሩን የሥራ ክፍሎችና ሹማምንቶች ይጠቀልላል ።

፱/ «የመጀመሪያ ፕሮግራም» ማለት ለሚኒስትሩ የሚቀርበው የኮንስትረክሽኑ ሥራ ዕቅድ የመጀመሪያው የሥራ ዝርዝር ማለት ነው ።

፲/ «አሠሪው ባለሥልጣን» የሚለው ቃል ትእዛዙ የሚፈጸምበትን ማንኛውንም ሚኒስቴር ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ፣ የመንግሥት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤትና የመንግሥት የወኪል መሥሪያ ቤትን የሚጠቀልል ሆኖ በተለይ የግል ኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ ለማሠራት የሚያቅድ ድርጅትን ይጠቅሳል ።

፲፩/ «የጨረታ ሠነዶች» ማለት ማንኛውንም የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ ስለመሥራት ዋጋ ለመጠየቅ ተዘጋጅተው የቀረቡ ሠነዶች ማለት ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፩/፳፫ (፲፱፻፶፰) ት. ማ. አን. ፱ (፭፱)፤ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፪ (፭፱) በሚ.ሲ. ተሻሻለ ። (የቀድሞው የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር በሁለት ሲከፈል የሥራ ሚኒስቴርና የመገናኛ ሚኒስቴር የተባሉ ሁለት ሚኒስቴሮች ተቋቋሙ ።)

፪/ ደንቡ የሚጸናበት ወሰን ።

፩/ እያንዳንዱ አሠሪ ባለሥልጣን ለማሠራት በሳቀደው ስለማናቸውም የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ በዚህ ደንብ ውስጥ የተወሰነውን የሥራ አፈጻጸም መፈጸምና መከተል አለበት ።

፪/ በዚህ ደንብ ውስጥ ተቃራኒ ተጽፎ ቢገኝም እንኳ ሚኒስትሩ በቂ ምክንያት ካገኘ ማናቸውንም አሠሪ ባለሥልጣን ወይም ማናቸውንም የተለየ የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ በዚህ ደንብ ውስጥ ከተጻፉት በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ለማድረግ ይችላል ።

www.chilot.me



## ፭/ የመጀመሪያ ፕሮግራም ።

ማናቸውንም የኮንስትራክሽን ሥራ ለማሠራት የሚያስብ እያንዳንዱ አሠሪ ባለሥልጣን ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ጉዳዮች ያሉበት የመጀመሪያ ፕሮግራም ለሚኒስትሩ ማቅረብ አለበት ።

፩/ የአሠሪውን ባለሥልጣን ልዩ ፍላጐትና ይህንኑ ፍላጐት ለመፈጸም የኮንስትራክሽኑ ሥራ ዕቅድ የታሰበበትን አኳኋን ከሚያሳይ መግለጫ ጋር የኮንስትራክሽኑ ሥራ ዕቅድ ጠቅላላ የሥራ ዝርዝር ።

፪/ ለኮንስትራክሽኑ ሥራ ማሠሪያ የታሰበው ገንዘብ (ካፒታል) ዝርዝር መግለጫ ።

## ፮/ የመጨረሻውን የሥራ ዕቅድ ስለ ማዘጋጀት ።

፩/ ሚኒስትሩና አሠሪው ባለሥልጣን እያንዳንዱን የመጀመሪያ ፕሮግራም በአንድነት አጥንተው የመጨረሻውን የሥራ ዕቅድ ያዘጋጃሉ ። በመጨረሻው የሥራ ዕቅድ ውስጥ ስለኮንስትራክሽን የሥራ ዕቅድ ወደፊት የኤክስፐርት ምርመራ ለማድረግ መሠረት ለመሆን የሚያስፈልጉት ኮንስትራክሽኑ የሚሠራበትን ሥፍራ የሚገልጽ አጭር መግለጫ ፣ ንድፎች ፣ ፕላኖችና የገንዘብ ሠነዶች ጭምር አስፈላጊዎቹ ዝርዝር ጉዳዮች ይገኙበታል ።

፪/ የኮንስትራክሽን የሥራ ዕቅድ ወደፊት ለመመርመርና የጨረታ ሠነዶችን ለማዘጋጀት መሠረት የሚሆነው የመጨረሻው የሥራ ዕቅድ ነው ። የመጨረሻው የሥራ ዕቅድ የኮንስትራክሽን ሥራ ኮንትራት እስኪፈጸም ድረስ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፩ በተመለከተው አኳኋን በማናቸውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል ።

## ፯/ ለአማካሪነት ስለመቀጠር ።

፩/ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የመጨረሻው የሥራ ዕቅድ ከተፈጸመ በኋላ በማናቸውም ጊዜና የኮንስትራክሽን ሥራ በሚከናወንበት በማናቸውም ደረጃ ሚኒስቴሩ ስለኮንስትራክሽኑ ሥራ አስፈላጊውን አገልግሎት ከሚሰጥ ከአንድ (፩) ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መሐንዲሶች ፣ አርሽቴክቶች ወይም ሌሎች እስፔሲያሊስቶች ጋራ አንድ (፩) ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የአማካሪነት ስምምነቶች ለመዋዋል ይችላል ። ይህ ያማካሪነት ስምምነት ረቂቅ በጠቅላላው ሚኒስቴሩ የተስማማበትን መደበኛ ፎርም የሚከተል ሆኖ አሠሪው ባለሥልጣን የተስማማበት ለመሆኑ በጽሑፍ እንዲያረጋግጠው ያስፈልጋል ። ይህም የጽሑፍ መረጋገጫ በስምምነቱ ውስጥ የተጣለበትን ግዴታዎች በሚገባና በጊዜው ለመፈጸም አሠሪውን ባለሥልጣን የሚያስገድድና ወዲያውኑም ወኪሉ ለመሆኑ የሚኒስቴሩን ሥልጣን የሚያረጋግጥ ይሆናል ።

፪/ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስትሩ በጠቅላላ ስለውድድር በሚሠራባቸው ሁኔታዎች መሠረት አማካሪዎች በአገር ውስጥ ወይም በኢንተርናሽናል ደረጃ በውድድር እንዲመረጡ ለማዘዝ ይችላል ።

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ መሠረት የሚቀጠረውን የማናቸውንም አማካሪ የአገልግሎት አፈጻጸም መቆጣጠር ይችላል ። ስለሆነ ግን የአገልግሎቱን ተግባር በመፈጸም የአማካሪው የሥራ አላፊነት በሚኒስትሩ መቆጣጠር በማናቸውም አኳኋን መቀነስ የለበትም ።

፬/ የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ ለመፈጸም በማናቸውም ደረጃ አስቀድሞ አገልግሎት መፈጸም በሚከተለው የኮንስትራክሽን ሥራ አፈጻጸም አማካሪዎችን ለመቅጠር እንደውለታ አያስቆጥርም ።

www.chilot.me



፰/ የጨረታ ሠነዶችን ስለመመርመርና በጽሑፍ ስለማረጋገጥ ።

የጨረታ ሠነዶች ሁሉ በተፈጸሙ ጊዜ አሠሪው ባለሥልጣን ሚኒስቴሩ በአንድነት ከመረመሩዋቸው በኋላ የተስማሙባቸው እንደሆነ በአሠሪው ባለሥልጣንና በሚኒስቴሩ በጽሑፍ እንዲረጋገጡ ያስፈልጋል ። ይህም የጽሑፍ ማረጋገጥ እያንዳንዳቸውን አሠሪውን ባለሥልጣንና ሚኒስቴሩን በሚመለከቱት ዝርዝር ጉዳዮች ለምሳሌ ፤

፩/ ስለአሠሪው ባለሥልጣን ሲሆን ፤ ሠነዶቹ ፍላጐቱን የሚያጣግቡ ሆነ ከአለው የገንዘብ ችሎታ በላይ የኰንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ ያልተወሰነባቸው ለመሆናቸው ፤

፪/ ስለሚኒስቴሩ ሲሆን ፤ ሠነዶቹ ተገቢውን የቴክኒክ ደረጃና የአፈጻጸም ቴክኒክ የያዙ ለመሆናቸው ፤
በሠነዶች እንደመስማማት ያስቆጥራል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የዚህ አንቀጽ የእንግሊዝኛው ቅጂ «አሠሪው ባለሥልጣንና ሚኒስቴሩ» ይላል ።

፱/ ውድድሩን ስለመክፈት ።

፩/ የጨረታው ሠነዶች ከተፈጸሙ በኋላ ወዲያውኑ ሚኒስቴሩ የኰንስትራክሽን የሥራ ዕቅድ ለመሥራት የጨረታ ዋጋ እንዲቀርብ መጠየቅና ስለፎርሞቹ አሠራር ፤ ለሚኒስቴሩ ተስማሚ መስለው የሚታዩትን ሁኔታዎች ስለመፈጸምና እነዚህን ስለ መሳሰሉት ጭምር የጨረታውን ሁኔታዎች ለይቶ መዘርዘር አለበት ።

፪/ ሚኒስትሩ ተገቢ መስሎ ከታየው ስለማናቸውም የኰንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ የሚደረገውን ጨረታ የሥራውን ዕቅድ ዓይነትና ጠቃሚነት በመከተል ለተመረጡ ቁጥራቸው ለተወሰነ ተቋራጮች ብቻ መወሰን ይችላል ወይም የኰንስትራክሽን ሥራ ኰንትራት ስለመዋዋል በቀጥታ ለመነጋገር መወሰን ይችላል ።

፫/ እንደ ደንቡ ሚኒስቴሩ በተለይ ስለታሰበው የኰንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ አሠራርና የኰንስትራክሽን ሥራ ስለሚሠራባቸው አስፈላጊ ነገሮች ዓይነትና አገልግሎት የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ በጨረታው ሠነዶች ውስጥ ተለይተው በሚዘረዘሩት ሁኔታዎች ለተወዳዳሪዎቹ የተወሰነ ዕድል ይሰጣቸዋል ።

፲/ ጨረታዎችን ስለመቀበል ።

፩/ ጨረታዎቹ ሁሉ በስም በታሸገ ኤንቬሎፕ ሆነው ስለኰንስትራክሽን ሥራ የሚቀርቡትን ጨረታዎች ለሚመረምረው ሚኒስትሩ ለሾመው ኮሚቴ መቅረብ አለባቸው። ጨረታዎቹ በሚከፈቱበት ጊዜ አሠሪው ባለሥልጣንና እያንዳንዱ ተጫራች ሊገኙ ይችላሉ ።

፪/ ጨረታዎቹ ከተከፈቱ በኋላ ኮሚቴው ጨረታዎቹ የተሟሉና በጨረታው ሠነዶች የሚፈለጉትን ግዴታዎች ሁሉ የፈጸሙ መሆናቸውን ይወስናል ። ኮሚቴው ተሟልተው ያልተገኙትን ወይም በጨረታው ሠነዶች ውስጥ የተወሰኑትን ግዴታዎች ዓይነተኛ ፍላጐት ወይም ፎርም ለመፈጸም ያልቻሉትን ጨረታዎች ላይቀበላቸው ይችላል ።

፫/ ሚኒስቴሩ በኮሚቴው ከተመረጠው የኮሚቴው ወኪልና በጉዳዩ ስለተመለከተው የኰንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ የተቀጠረው አማካሪ ያለ እንደሆነ ከእርሱ ጋር ሆኖ

www.chilot.me



፲፬/ ስለወጪዎች አከፋፈል ።

በዚህ ደንብ መሠረት በሚኒስቴሩ የሚከናወኑት የመቆጣጠር ሥራዎች ሁሉ የሚፈጸሙት በሚኒስቴሩ ሆኖ ስለዚሁ መቆጣጠር የሚወጣው ወጪ የሚከፈለው ከራሱ ከሚኒስቴሩ በጀት ነው ። ይሁን እንጂ ማናቸውንም የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ ለማዘጋጀት ወይም ለመፈጸም የሚወጣው ሌላው ወጪ ሁሉ በዚህም ብቻ ሳይወሰን የአማካሪዎች አበል የጥልቅ ምርመራና ፕላን ለምግባሬ የተፖግራፊ ጥናት ፣ የአፈርና የግቦራትሪ ምርመራ ፣ የኤክስፐርት ጥናት ሠነዶች ለማባዛት የሚያስፈልገው ወጪ ሁሉ ፤ የጉዞ ወጪና ሌላውንም ወጪ ለምሳሌ የጠቅላላ ጥናት ወጪ የግል ንብረት ባለቤትነትን ለማስለቀቅ የሚከፈለው ወጪና የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ የሚመለከት የካሣ ወጪ ሁሉ በተቋራጩ እንዲከፈል በኮንስትራክሽን ሥራ ኮንትራት አስቀድሞ ካልተወሰነ በቀር ፤ የአሠሪው ባለሥልጣን ሂሳብ ይሆናል ።

፲፭/ አሠሪው ባለሥልጣን ከአማካሪዎቹና ከተቋራጮች ጋር ያለው ግንኙነት ።

ሚኒስቴሩ ካልፈቀደለት በቀር አሠሪው ባለሥልጣን ለማሠራት ስላቀደው ስለማናቸውም የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ኃላፊ ከሆነ ከማናቸውም አማካሪ ወይም ተቋራጭ ጋራ ስምምነት ማድረግ የለበትም ። እንደዚሁም ሁሉ ሚኒስቴሩ በግልጽ ከፈቀደለት በቀር ማናቸውንም ሰው እንዲህ ላለው ማናቸውም አማካሪ ወይም ተቋራጭ ትእዛዝ መስጠት የለበትም ።

፲፮/ ሠነዶች በጽሑፍ የሚረጋገጡበት አኳኋን ።

በዚህ ደንብ መሠረት በጽሑፍ እንዲረጋገጡ የሚያስፈልጉት ሠነዶች ሁሉ ተገቢዎቹ ሰዎች በጽሑፍ እንዲረጋገጥ ከሚያስፈልገው ሠነድ ቢያንስ በሦስት (በ፫) ግልባጮች በእንዳንድ ገጽ ላይ አጭር የፊርማ ምልክት በማድረግ ይረጋገጣሉ ።

፲፯/ ስለውስጥ ደንብ ።

ሚኒስቴሩ የውስጥ ደንብ በማውጣት በዚህ ውስጥ ስለተጠቀሱት ማናቸውም ጉዳዮች ሰፋ ያለ ዝርዝር በመስጠት አስፈላጊውን መወሰን ይችላል ። ደንቡም እንደ አግባቡ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሰዎች ሁሉ የጸና ይሆናል ።

፲፰/ ይህ ደንብ በሚጸናበት ጊዜ ።

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም.

www.chilot.me



ያወጣውን የፌዴራል ታክስ፣ ይህንንም የመሳሰሉ የአገር ውስጥና የማዘጋጃ ቤት ታክሶች ጭምር ይከፍላል ።

፲/ መጠባበቂያ ድርሻዎች፤ ካፒታሉ በመቶ ሃያ እስኪያህል ድረስ ከባለሥልጣኑ የተጣራ ትርፍ ላይ በያመቱ በመቶ አምስት (5%) እየተነሣ ደንበኛ መጠባበቂያ ሆኖ ይቀመጣል ፡፡ ነገር ግን ይህ ደንበኛ መጠባበቂያ ከተቀመጠ በኋላ ከካፒታሉ ከመቶ ሃያ ያነሰ እንደሆነ ይኸው መደበኛ መጠባበቂያ የካፒታሉን በመቶ ሃያ እስኪያህል ድረስ እንደቀድሞው ከባለሥልጣኑ የተጣራ ትርፍ ላይ እየተቀነሰ ይሟላል ። በዚህ ቻርተር በ፫ኛው አንቀጽ እንደተዘረዘረው የዲሬክተሮች ቦርድ በሚወስነው መሠረት ባለሥልጣኑ ሥራውን ለማሻሻልና ለማስፋፋያ የሚሆን ሌላ የሚተካከል መጠባበቂያ ሂሳብ ከትርፉ ላይ ለማስቀመጥ ይችላል ። ባለሥልጣኑ ለባለ አክሲዮኖች ድርሻ መክፈል የሚችለው ማናቸውም የሥራ ማስኬጃ ወጭ፤ ደንበኛውና ሌላው መጠባበቂያ ሂሳብ ለሚየረጁ ዕቃዎች መተኪያ የሚያስፈልገው ሂሳብና ሥራውን ለማሻሻያና ለማስፋፊያ በተፈቀደው ፕላን መሠረት የሚያስፈልገው ወጭ ሁሉ ተቀንሶ ከሚተርፈው ከተጣራው ትርፍ ላይ ብቻ ነው ። የባለአክሲዮኖች ድርሻ ሊታወቅና ሊከፈል የሚቻለው የዲሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ነው ።

ይሁን እንጂ ይህ ጥሩ ትርፍ በሙሉ ስለኤሌክትሪክ ሥራ ብቻ ማስፋፊያና ማሻሻያ እንዲውል በተለየ ይቀመጣል ። ይህም ገንዘብ ምንም ባለሥልጣኑ አጥንቶ ለሚያቀርባቸው ፕሮግራሞች ማከናወን የተመደበ ቢሆን፤ አስቀድሞ በገንዘብ ሚኒስትራችን አማካይነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ካልተፈቀደ ወጭ ሊሆን አይችልም ።

፲፩/ የንብረት ባለቤትነት ማዘዋወር፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለቤትነት የቆየ ወይም ሲሠራበት የነበረው ማናቸውም ንብረት የባለቤትነት መብትና የሚገኘው ጥቅም ከዚህም በቀር ማናቸውም መብቶች፤ ሥልጣኖች፤ በክስ ላይ ያሉ ነገሮች ውሎች ሁሉ በዚህ ቻርተር በአንቀጽ ፭ እንደተመለከተው ባለሥልጣኑ በካፒታል ስም ላወጣቸው ዋጋቸው አሥር ሚሊዮን የኢት ብር ለሆኑት አክሲዮኖች ለውጥና ለነዚህም ሙሉ ዋጋ ክፍያ ሆኖ በዚህ ቻርተር ለተቋቋመው «የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን » ተዛውረዋል ።

፲፪/ ኦዲተሮች፤ የባለሥልጣኑ ሥራዎች በዲሬክተሮቹ ቦርድ በሚሾሙ በሂሳብ ምርመራ ሥራ የታወቀ ችሎታ ባላቸው ኦዲተሮች በያመቱ ይመረመራሉ ። የባለሥልጣኑ ሂሳብ በገንዘብ ሚኒስትራችን ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው በማናቸውም ጊዜ ሊመረመር ይቻላል ።

፲፫/ የውስጥ ደንቦች፤ የባለሥልጣኑ የዲሬክተሮች ቦርድ የዚህን ቻርተር ቃል ሳያታውስ የባለሥልጣኑን ጉዳዮች ለማካሄድ የሚያስፈልጉትን ደንቦች፣ ድንጋጌዎችና የውስጥ ደንቦች ለማውጣት ሥልጣን አለው ።

አዲስ አበባ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፭ ዓ. ም.

www.chilot.me



ዳይሬክተሩ ሒሳብ ያቀርባል ። ለቦርዱም የውስጥ ሥራ አመራር አስፈላጊዎችን ደንቦች ራሱ ያዘጋጃል ።

ሐ/ አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ መሪዎችና ሠራተኞች ይመርጣል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፷፰) ት. ቁ. ፺፯ አን. ፰ (፲፱) ፣ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፰ (፲፱) በግ.ሳ. ተሻሻለ። (በዚህ ትእዛዝ መሠረት የድሮው የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር ፤ የሥራ ሚኒስቴር ፤ የመገናኛ ሚኒስቴር በመባል በሁለት ተከፈለ ።)

፬/ የሲቪል አቪያሲዮን አስተዳደር በሕጉ መሠረት ከዚህ የሚከተለውን ለመፈጸም አላፊ ነው ።

ሀ/ የሲቪል አቪያሲዮንን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እያዘጋጀ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ፤

ለ/ ማናቸውንም የሲቪል አቪያሲዮንን የሥራ እቅዶችና ፕሮግራሞች በሚገባ ለማስፈጸምና ለማስተዳደር አስፈላጊና ጠቃሚ ሆኖ በሚገኘው መጠን የሥራ ማካሄጃ ድርጅት ማቋቋም ፤

ሐ/ የመሥሪያ ቤቱን የዓመት በጀት አዘጋጅቶ ማቅረብ ፤

መ/ በሕጉ የተሰጡትን ማናቸውንም ሌሎች ተጨማሪ ተግባሮች መፈጸም ፤

፭/ የመገናኛ ሚኒስትራችን ከሲቪል አቪያሲዮን ቦርድ የሚቀርብለትን አሳብ ተቀብሎ የዚህን ትእዛዝ ቃል በትክክል ለማስፈጸም አስፈላጊ የሚሆኑትን ደንቦች ለማውጣት ይችላል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፷፰) ት. ቁ. ፺፯ አን. ፰ (፲፱) ፤ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፰ (፲፱) በግ.ሳ. ተሻሻለ ። (የድሮው የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር በሁለት ተከፍሎ የሥራ ሚኒስቴርና የመገናኛ ሚኒስቴር ሆነ ።)

፮/ ይህ ትእዛዝ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም.

www.chilot.me



፩/ ለአይሮፕላን ነጂዎችና ሌሎችም ያየር ጉዞ ሠራተኞች ለሆኑ ሰዎች አስፈላጊ ውን የሥራ ፈቃድ ለመስጠትና እነዚሁ ፈቃዶች ለጊዜው እንዳይሠራባቸው ወይም እንዲሠረዙ ለማድረግ ፤

፪/ ማናቸውንም ዓይነት አይሮፕላን ለመመዝገብ ፤ የመለያ ቁጥር ለመስጠት ፤ ለመመርመርና የምስክር ወረቀትና ፈቃድም እንዲቀበል ለማድረግ ፤

፫/ ለማናቸውም አይሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎች ፤ የአየር መጓጓዣ ድርጅቶችና አገልግሎቶች ፈቃድ ለመስጠት ፤ እነዚሁንም ለመመርመርና ሥራው በደንብ እንዲካሄድ ለማድረግ ፤

፬/ አይሮፕላን ሊያገለግልና በሥራ ላይ ሊውል የሚችልበትን አኳኋን ለመወሰን ፤

፭/ ዕቃዎች ፤ ፖስታዎችና መንገደኞች በአይሮፕላን የሚጓጓዙበትን አኳኋን ለመወሰን ፤

፮/ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ ወይም ከግዛታችን ውጭ ተለይ ተው በተነገሩ ክልሎች ላይ ለሁልጊዜ ወይም በደንቦች ውስጥ ለተወሰኑት ጊዜያቶች ወይም ሁኔታዎች ብቻ ከነጭራሹም ሆነ ወይም ከነዚህ በቀር ወይም በነዚህ ሁኔታዎች ብቻ ተብሎ በሚገለጸው አኳኋን የአይሮፕላን መተ ላለፍን ለመከልከል ፤

፯/ ከንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውጭ ከሆነ ከማናቸውም አገር የሚመጣ አይሮፕላን ሊያርፍባቸው የሚገባውን ቦታዎችና እንደዚሁ ማናቸውም አይሮ ፕላን መፈጸም ያለበትን አገባብ ለመወሰን ፤

፰/ የአየር ጉዞ መስመሮችን አቋም ለማደራጀት ፤ ለመቆጣጠርና አገልግሎታቸ ውንም ለመወሰን ፤

፱/ አይሮፕላኖች በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ተመዝግበው በማናቸውም ቦታ የሚገኙትን ጭምር በመንግሥታችን ግዛትና በግዛታችን የባሕር ክልሎች ላይ የተረጋገጠና የሚያስተማምን ያየር ጉዞ ለማድረግ እንዲችሉ ለዚሁ የወ ጡትን ሕጎች ትእዛዞች ደንቦች ለማስከበር ፤

፲/ በልዩ ልዩ አይሮፕላን የሚያገለግሉ ሰዎች በኢኮኖሚ በኩል መፈጸም የሚገ ባቸውን ለመወሰን ፤

፲፩/ አይሮፕላን በንግድ ሥራ ላይ ለማዋል ኮንሲሲዮኖች ፤ መብቶች ወይም ስምም ነቶች ለመፍቀድ ወይም ለመስጠት የሚቻልበትን አኳኋን ለመወሰን ፤

፲፪/ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ወይም በስሙ በሚዘጋጁት የአይሮፕ ላን ማረፊያ ሜዳዎች ፤ ያየር መጓጓዣ ድርጅቶችና አገልግሎቶች እንዲሁም የሲቪል አቪያሲዮን አስተዳደር ከሲቪል አቪያሲዮን ሥራ ጋር ግንኙነት ላላቸው በሚለው ሌሎች ድርጅቶችና ንብረቶች ወይም ሰርቪሶች ለመጠቀም የሚከፈለውን ዋጋ ለመወሰን ፤

፲፫/ በንግድ ሥራ ላይ የሆነ አይሮፕላን የሚከፍለውን ዋጋ (ታሪፍ) ለመወሰን ፤

፲፬/ ማናቸውም አይሮፕላን በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ወይም በባሕር ክልሎቻችን ውስጥ በመብረር ላይ ሆኖ ወይም በግዛታችን የተመዘገበ ማናቸ ውም አይሮፕላን የሚገኝበት ቦታ የትም ቢሆን የደረሰበትን ማንኛውንም አደጋ ለመመርመር ።

www.chilot.me



### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፶፰) ት. ፵፮ አን. ፪(፲፱)፤ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፪ (፲፱) በግ.ሳ. ተሻሻለ ። (የቀድሞው የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር በሁለት ተከፍሎ የሥራ ሚኒስቴር ፤ የመገናኛ ሚኒስቴር ሆነ ።)

፭/ የዚህን ድንጋጌ ቃል የጣሰ ማናቸውም ሰው በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ደንብ መሠረት ይቀጣል ።

### የተጠቀሰው ሕግ

ወ.መ.ሕ. ፤ ፲፮/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) አን. ፬፻፲፱—፭፻፪ ።

፮/ ይህ ድንጋጌ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም.

## ፳፬/፲፰ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፳.*
## በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. በወጣው የሲቪል አቪያሲዮን ድንጋጌ መሠረት የወጣ ደንብ ።

፩/ አውጭው ባለሥልጣን ፤

በቁጥር ፵፰/፲፱፻፶፩ ዓ.ም. በወጣው የሲቪል አቪያሲዮን ድንጋጌ በአንቀጽ ፫ በ(ለ) ፊደል በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ፤ የሲቪል አቪያሲዮን ቦርድ ያቀረበውን ሐሳብ ተቀብሎ የመገናኛ ሚኒስትር ያወጣው ደንብ ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፶፰) ት. ፵፮ አን. ፪ (፲፱)፤ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፪ (፲፱) በግ.ሳ. ተሻሻለ ። (ድሮ የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር የነበረው በሁለት ተከፍሎ የሥራ ሚኒስቴር ፤ የመገናኛ ሚኒስቴር በመባል ተቋቋመ ።)

፪/ አጭር አርእስት ፤

ይህ ደንብ «የ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. የአውሮፕላን አመዘጋገብ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

---

*የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፶፰) ት. ፵፮ በግ.ሳ. ተሻሻለ ።

www.chilot.me



፫/ የአውሮፕላኖች መመዝገቢያ መዝገብ ፤ ለመመዝገብ የሚፈጸሙ ግዴታዎች ፤

፩/ ከዚህ ቀጥሎ «አስተዳደሩ» እየተባለ የሚጠራው የሲቪል አቪያሲዮን አስተዳደር አብዛኛው አገልግሎታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የንግድና የግል አውሮፕላኖች ሁሉ የሚመዘገቡበት መዝገብ ያቋቁማል ።

፪/ ማናቸውም ሰው ወይም በሕግ ፊት እንደ ሰው የሚቆጠር ማናቸውም ድርጅት በግል የሚኖረው ወይም በኪራይ ስም የያዘው ወይም ደግሞ በሌላ ማናቸውም አኳኋን በእጁ አድርጎ የሚሠራበትን አውሮፕላን በዚህ ደንብ መሠረት ሊመዘገብ የሚገባው መሆን አለመሆኑን አስተዳደሩን ጠይቆ መረዳት ይኖርበታል ።

፫/ ከዚህ በላይ በ፫ኛው አንቀጽ በክፍል (፪) በተመለከተው መሠረት አስተዳደሩ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜም የሚከተሉትን ሁኔታዎች መመርመርና መሠረት ማድረግ አለበት ።

ሀ/ ይህን የመሰለ ውሳኔ እንዲደረግለት የሚጠይቀውን ሰው ዜግነት ፤ አድራሻና መኖሪያ ቦታ ፤

ለ/ የአውሮፕላኑ መደበኛ አገልግሎት ፤

ሐ/ ከዚህ ቀደም ሌላ አገር ተመዝግቦ እንደሆነ የተመዘገበበትን የምስክር ወረቀት ፤

መ/ በማናቸውም ሌላ አገር ተመዝግቦ የሚገኘው አውሮፕላን በዚያ በተመዘገበበት ሥፍራ አገልግሎቱን ለመቀጠል ይፈቀድለት እንደሆነና የሚሠራውንም የሥራ ዓይነት ፤

ሠ/ በሌላ አገር የተመዘገበው አውሮፕላን በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎቱን እንዲቀጥል የሚፈለግ መሆኑንና እንዲሁም የአውሮፕላን መጫያዎች ፤ የመብረር ተገቢነቱና ይህንንም የመሳሰሉት ጉዳዮች አስተዳደሩ የሚጠይቃቸውን ግዴታዎች ሁሉ ሊፈጽሙ የሚችሉ መሆናቸውን መመርመር አለበት ።

፬/ መመዝገብ ያለባቸው ሁኔታዎች ፤

በዚህ ደንብ መሠረት በግልም ሆነ በማኅበር በአውሮፕላን ለመጠቀም ፤ ጥቅሙን ለማዛወር ፤ ወይም ከዚህ ጥቅም ተካፋይ የሆነው የአንድ ወይም የብዙ ሰዎችን ጥቅም ለማስቀረት የሚፈጸመው ሁኔታ ሁሉ በዚህ ደንብ መሠረት በአውሮፕላኖች መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለባቸው ። በተጨማሪም እነዚህ ሁኔታዎች ሳይጓደሉ የሚከተሉትም መመዝገብ ይኖርባቸዋል ።

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ለማያጸርጥ ስድሣ (፷) ቀን ወይም በማናቸውም አንድ ዓመት ውስጥ ከአንድ መቶ ሃያ (፻፳) ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚደረጉ የአውሮፕላን ኪራይ ስምምነቶችና ፤

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት በአንድ አውሮፕላን ዋስትና በመስጠት ለመጠቀም ፤ ይህንኑ ጥቅም ለማዛወር ፤ ለማሻሻል ወይም ከዚህ ጥቅም ለማስወጣት የሚፈጸም ሁኔታና በጠቅላላው ከአውሮፕላኑ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ ዋስትና ለማስያዝ የሚፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ ።

፭/ የማስመዝገብ አላፊነት የሚመለከታቸው ሰዎች ፤

፩/ በመጀመሪያ አውሮፕላኑ በአስተዳደሩ የሚመዘገበው በዚህ ደንብ መሠረት የአውሮፕላኑ ባለንብረት ፤ ተከራይ ወይም የአውሮፕላኑ ሠራተኛ በሆነው ሰው አማካይነት ነው ፤

www.chilot.me



፪/ ከዚህ በኋላ በዚህ ደንብ በአራተኛው አንቀጽ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ለማስመዝገብ ኃላፊ የሚሆኑት በመጀመሪያ በአውሮፕላኑ የሚጠቀመው ፤ በተሻሻለ ሁኔታ ጥቅሙ የርሱ የሆነው ወይም ለርሱ ተዛውሮለት ተጠቃሚ የሆነው ሰው ወይም ሰዎች ናቸው ።

፮/ ለማስመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ ፤

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ለማስመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርበው ለአስተዳደሩ ሲሆን አቀራረቡም ከአስተዳደሩ የሚሰጠውን ፎርም በመሙላት ነው ፤

፪/ አንድ አውሮፕላን በአስተዳደሩ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲመዘገብ ለማድረግ የሚከተሉት መረጃዎች በፎርሙ ላይ ተሞልተው መቅረብ አለባቸው ፡—

ሀ/ የአውሮፕላኑ ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ ፤

ለ/ አውሮፕላኑን የሠራው ፋብሪካ ስምና አድራሻ ፤

ሐ/ አውሮፕላኑ ከፋብሪካው የተሰጠው ሴሪ ቁጥር ፤

መ/ እንደነገሩ ሁኔታ በመለየት የባለንብረቱ ወይም የተከራዩ ወይም ደግሞ በአውሮፕላኑ ላይ የሚሠራው ሰው ስም ፤

ሠ/ እንደሁኔታው የባለንብረቱ ወይም የተከራዩ ወይም በአውሮፕላኑ ላይ የሚሠራው ሰው አድራሻ ፤

ረ/ እንደሁኔታው የባለንብረቱ ወይም የተከራዩ ወይም ደግሞ በአውሮፕላኑ ላይ የሚሠራው ሰው ዜግነት ፤

ሰ/ በተጨማሪ ከዚህ ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት ሠነዶች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው ፡—

፩/ አውሮፕላኑ በመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ሊከፈሉ የሚገባቸው ቀረጦችና ግብሮች ሁሉ መከፈላቸውን የሚያረጋግጥ የገንዘብ ሚኒስቴር ጉምሩክ ዋና መሥሪያ ቤት ማስረጃ ፤

፪/ አውሮፕላኑ ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት በሌላ አገር አልተመዘገበ እንደሆነ አውሮፕላኑ ከመጣበት አገር ወይም ደግሞ ይኸው አውሮፕላን አስቀድሞ ተመዝግቦ እንደሆነ ከተመዘገበበት አገር አውሮፕላኑ ለመብረር ተገቢ መሆኑን የሚያረጋግጥ አንድ የምስክር ወረቀት ፤

፫/ በዚሁ አንቀጽ ፮ በክፍል ፪ ከተዘረዘሩት መግለጫዎች ሌላ የአውሮፕላኑን ጥቅም ነክ ጉዳዮች ለመመዝገብ የሚከተሉት ተጨማሪ መረጃዎች መቅረብ አለባቸው ፡—

ሀ/ የውሉና የጥቅሙ ዓይነት ፤

ለ/ በአውሮፕላኑ መጠቀም የጀመረው ፤ አሁን ጥቅሙ የተዛወረለት ፤ የጥቅሙ ሁኔታ የተሻሻለለት ወይም ጥቅሙ የቀረበት ሰው ወይም ሰዎች ስምና አድራሻ ፤

ሐ/ የውሰታው ገንዘብ መጠን ፤

መ/ የውሰታው ዘመን ፤

፬/ ሀ/ ለመጀመሪያ ምዝገባ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ አንድ መቶ የኢትዮጵያ ብር (የኢት/ $100) ይከፈላል ። እንዲሁም ማመልከቻ አቅራቢው የአውሮፕላኑ ባለንብረት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ የሚሆኑትን እንደ የሽያጭ ውል የመሰሉ

www.chilot.me



ሠነዶች ወይም ቀደም ብሎ በተመዘገበበት አገር የተሰጠው አውሮፕላኑ የተመዘገበበት የምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው ፤

ለ/ የአውሮፕላኑ ጥቅም ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ለማስመዝገብ ሃያ የኢትዮጵያ ብር (የኢት/ $ 20) ይከፈላል ። በተጨማሪም የሚመዘገቡት ሁኔታዎችና ጥቅሞች በእርግጥ ያሉ መሆናቸውን የሚገልጹ በቂ ማስረጃዎች አብረው መቅረብ አለባቸው ።

፯/ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ፤

፩/ የመጀመሪያ ምዝገባ በሚደረግበት ጊዜ አስተዳደሩ አውሮፕላኑን ባስመዘገበው ሰው የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ። ይህም የምስክር ወረቀት እንደ አውሮ ፕላኑ የባለንብረትነት መረጃ ሆኖ ይቆጠራል ።

፪/ የአውሮፕላኑ ጥቅም ነክ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች በሚመዘገቡበት ጊዜ አስተዳደሩ ሁኔታውንና ጥቅሙን በመዛግብቱ ላይ ያሰፍራል ።

፫/ አስተዳደሩ በዚህ ደንብ በ፯ኛው አንቀጽ በ፪ኛው ክፍል የተመለከተውን በሚፈጽምበት ጊዜ የምዝገባው ምስክር ወረቀት እንዲቀርብለት በማድረግ በምስክር ወረቀቱ ላይ የተመለከተው ማናቸውም ሁኔታና ጥቅም ሁሉ መኖሩን እየተቆጣጠረ ይመዘግባል ።

አስተዳደሩ የድርጊቱ ወይም የጥቅሙ ሁኔታ የሚያስፈልገው መስሎ ባገኘው ጊዜ ፤ እነዚህን ሁኔታዎች ለማስመዝገብ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርብለትን የቀድሞ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በሁለት ኦርጂናል ኮፒ አባዝቶ (ዱፕሊኬት አድርጎ) ዋናውን ለራሱ በማስቀረት ከዱፕሊኬቶቹ አንዱን በመጀመሪያ አውሮፕላኑን ላስመዘገበው ሰው ሲሰጥ ሁለተኛውን ደግሞ ጥቅሙ በስሙ ለሚመዘግብለት ሰው ይሰጣል ። እነዚህ ሁለቱም ኦርጂናል ቅጂዎች (ዱፕሊኬቶች) እንደ አውሮፕላኑ የባለንብረትነት መረጃዎች ሆነው ይቆጠራሉ ።

፰/ የአውሮፕላኑን ባለንብረትነት ስም ስለማዛወር ፤

በማናቸውም አኳኋን የአንድ አውሮፕላን ባለንብረትነት ወይም ስም የማዛወር ተግባር አውሮፕላኑ ከዚህ የተመዘገበበትን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፯ በሦስተኛው ክፍል የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም የምዝገባው ምስክር ወረቀት ሁለቱም ኦርጂናል ቅጂዎች ቀርበው ዝውውሩ በአውሮፕላኖች መመዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ በማድረግ ይፈጸማል ።

፱/ አንድ ውል በሌሎች ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት ፤

በዚህ ደንብ በአራተኛው አንቀጽ መሠረት የሚመዘገብ ውል አግባብ ባላቸው በሌሎች ላይ የሚጸናው ውሉ በአውሮፕላኖች መመዝገቢያ መዝገብ ከተመዘገበ ቀን አንስቶ ብቻ ነው ።

፲/ ሳያስመዘግቡ ስለመቅረት ፤

ይህ ደንብ በሚያዘው መሠረት መመዝገብ የሚገባቸው አውሮፕላኖች ሳይመዘገቡ ቢቀሩ ተገቢ ምዝገባውን እስከፈጸሙ ድረስ አስተዳደሩ በአውሮፕላኖቹ ላይ መስለው

www.chilot.me



የታዩትን እርምጃዎች ሁሉ ለመውሰድና አውሮፕላኖቹ ከምድር እንዳይንቀሳቀሱ ለማገድም ይችላል ።

፲፩/ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ ፤

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ.ም.

## ለ/ ማመላለሻ (ትራንስፖርት)

፳፯/፲ (፲፱፻፷) አ. ፪፻፶፮*

### በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን (ትራንስፖርትን) ለመቆጣጠርና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት የኤኮኖሚና የንግድ ልማት እየተፋጠነ መሔድ ፤ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገዶች ላይ ዕቃዎችንና መንገደኞችን በተፋጠነና ለኤኮኖሚ በሚጠቅም አኳኋን ለማመላለስ የሚረዳ ሕግ እንዲወጣ ስላስፈለገ ፤

በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በ፴፬ኛውና በ፹፰ኛው አንቀጽ የተጻፈውን ተመልክተንና የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶቻችን የመከሩበትን ተቀብለን ቀጥሎ ያለውን አውጀናል ።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ።

፩/ አጭር አርእስት ፤

ይህ አዋጅ «በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን (ትራንስፖርትን) ለመቆጣጠር የወጣ የ፲፱፻፷ ዓ. ም. አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ፤

፪/ የተሻሩ ሕጎች ፤

ከዚህ የሚከተሉት ተሽረው በዚህ አዋጅ ተተክተዋል ።

፩/ በቁጥር ፴፰/፲፱፻፴፭ ዓ. ም. የወጣው የትራንስፖርት አዋጅ ፤

---

*የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳፯/፲፫ (፲፱፻፷) ማ. ፳፯ ፤ በ፳፰/፱ (፲፱፻፷፩) ማ. ፳፱ (እንግሊዝኛው ብቻ) ታረመ ።

www.chilot.me



፯/ «የመንገደኛ» ሲባል በተሽከርካሪ ተሳፍሮ የሚሔድ ማናቸውም ሰው ማለት ነው፤ ስለሆነም ነጂውንና ገንዘብ ተቀባዩን አይጨምርም።

፰/ «የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) ማኅበር» ሲባል የጋራ ጥቅ ማቸውን ለመጠበቅና ሥራቸውን በጋራ ለመሥራት የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራን የሚሠራ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት በሕግ የተቋቋመና የተመዘገበ ማኅበር ሆነው ሲገኙ ነው።

፱/ «መንገድ» ሲባል ከግል መንገዶች በቀር፤ ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙ በት፤ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ጐዳና፤ የከተማ መንገድ፤ አውራ ጐዳና ወይም መተላለፊያ ማለት ነው።

፲/ «ተሽከርካሪ» ሲባል በተለይ በመንገድ ላይ እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ በመንኰራ ኵር የሚሔድ ማናቸውም ዓይነት ተሽከርካሪ ማለት ነው። እርሱም እንደሚከተለው ይከፋፈላል።

ሀ/ «ሠረገላ» ማለት ከብስክሌት፤ ከባለሞተር ተሽከርካሪ፤ ከግማሽ ተሳቢ፤ ከተ ሳቢና ከባቡር በስተቀር ማናቸውም ተሽከርካሪ ማለት ነው።

ለ/ «ብስክሌት» ማለት በሚነዳው ሰው ኃይል እየተመራ የሚሔድ ተሽከርካሪ ማለት ነው።

ሐ/ «ባለሞተር ተሽከርካሪ» ማለት በመኪና ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተመራ የሚሔድ ተሽከርካሪ ማለት ነው። እርሱም ከዚህ እንደሚከተለው ይከፋፈላል፤

፩/ «የንግድ ተሽከርካሪ» ማለት ዋና አገልግሎቱ ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሠራ፤ ለዚሁም የሚያገለግል ባለሞተር ተሽ ከርካሪ ነው። እርሱም ጐታች መኪናን ይጨምራል።

፪/ «ሞተር ብስክሌት» ማለት የጐን ተሽከርካሪው ሳይጨመር፤ ክብደቱ ከአራት መቶ (፬፻) ኪሎ ግራም የማይበልጥ፤ ከአራት መንኰራኩር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው።

፫/ «የግል አቶሞቢል» ማለት ከንግድ ተሽከርካሪ፤ ከሞተር ብስክሌት ወይም ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪና ከጐታች መኪና የተለየ ባለሞተር ተሽ ከርካሪ ነው።

፬/ «የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ» ማለት በተቀረጠ ወይም ባልተቀረጠ ዋጋ እንደቦታው ርቀት እኳኋን መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው። እርሱም እንደሚከተለው ይከፈላል።

ሀ/ «የኪራይ ተሽከርካሪ» ማለት ከሰባት (፯) መንገደኞች በታች የሚ ያሳፍር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው።

ለ/ «አውቶቡስ» ማለት ከሰባት (፯) መንገደኞች በላይ ለማሳፈር የሚ ችል የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው።

፭/ «ጐታች መኪና» ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጐተት የሚያገለግል ሆኖ የተጐታች ተሽከርካሪ ክብደትና ጭነቱን በከፊል ለመሸከም ብቻ የተሠራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው።

መ/ «ግማሽ ተሳቢ» ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግ ልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪው የጭነቱም ክብ

www.chilot.me



ይህ ተግባር ጉዳዩ የሚመለከተው የማዘጋጃ ቤት ወይም የከተማ ባለሥልጣን ኃላፊነት ነው ።

ለ/ መንገዶች እንዳይጐዱ መከላከያ ለማበጀት ፤

ሐ/ በመንገዶች የሚጠቀሙትን ተሽከርካሪዎች አሠራርና የሚሸከሟቸውን ዕቃዎች ለመወሰን ፤

ቀ/ ስለተሽከርካሪዎች ባከራዮችና በተከራዮች መካከል ስለሚደረገውና የሁለቱም ወገን መብት ስለሚጠበቅበት ስምምነት መሪ ደንብ ለመስጠት ፤

በ/ በዚህ አዋጅ እንደተወሰነው ፤ በሥልጣኑ ስለሚካሄድ ስለማናቸውም ጉዳይ ደንብ ለማውጣት ፤

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፯/፲፫ (፲፱፻፷) ማ. ፳፯ (እንግሊዝኛው ብቻ) ታረመ ።

## ለ/ ስለተሽከርካሪዎች መመዝገብ

፯/ ተሽከርካሪዎችን ስለማስመዝገብ ግዴታ ፤

፩/ ከቢስክሌት በቀር ፤

ሀ/ በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ መሠረት በሚነስቴሩ ያልተመዘገበውን ተሽከርካሪና

ለ/ በግልጽ የሚታይ ደንበኛ የመኪና ሠሌዳ ወይም ሌላ መለያ ምልክት የሌለውን ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ መንዳት አይፈቀድም ።

፪/ የደንበኛ የመኪና ሠሌዳ ወይም የሌላ መለያ ምልክት አለመኖር ተሽከርካሪውን እንዳልተመዘገበ ስለሚያስቆጥረው ተገቢው ምርመራ እስኪፈጸም ድረስ ፖሊስ እንዲህ ያለውን ተሽከርካሪ ይዞ ለማቆየት ይችላል ።

፰/ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ስለማስመዝገብ ፤

የግል ወይም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ በሚሠሩ ተሽከርካሪውች ላይ የሚከተሉት ተጨማሪ ግዴታዎች ይፈጸሙባቸዋል ፤

፩/ የግል ወይም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ከሥራቸው የሚበዛውን ክፍል የሚያከናውኑት በሕግ መሠረት ራሱን ችሎ በሚተዳደር ማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ በሆነ ጊዜ ፤ የተሽከርካሪዎቹ ባለቤቶች በልዩ ይመዘገባሉ ፤ ለዚህ ጉዳይ በሕግ የተወሰነውን ግብርም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣኖች ሊያስከፍሏቸው ይችላሉ ።

፪/ የግል ወይም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ከሥራቸው የሚበዛውን ክፍል የሚያከነውኑት ከማዘጋጃ ቤቶች ክልል ውጭ በሆነ ጊዜ የተሽከርካሪዎቹ ባለቤቶች ከአስተዳደሩ በልዩ ይመዘገባሉ ፤ አስተዳደሩ ስለዚህ ጉዳይ በሚያወጣው ደንብ የሚወሰነውንም ግብር ይከፍላሉ ። ስለሆነ ግን ፤ ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት ወይም አስተዳደሩ ይህንን ልዩ ምዝገባ ምክንያት አድርጎ ማናቸውም ተሽከርካሪ እንዲገና እንዲመረመር ወይም እንዲፈተሽ ማስገደድ አይችሉም ።

www.chilot.me



## ሐ/ ስለመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ፤

### ፳/ ያለመንጃ ፈቃድ ተሽከርካሪዎችን መንዳት ክልክል ስለመሆኑ ፤

ለማንም ሰው ፤ ዓይነቱ የተለየ የሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት የሚያስችል ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የመንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ፤ በማናቸውም መንገድ ላይ ማናቸውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት አይፈቀድም ። እንደዚሁም የማናቸውም የሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የመንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑን እያወቀ ለማንም ሰው ተሽከርካሪውን እንዲነዳ መፍቀድ የለበትም ። ስለሆነ ግን ፤ ሚኒስትሩ ደንበኛ የመንጃ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ለትምህርት ጉዳይ መንዳት የሚችሉበትን ሁኔታ መወሰን ይችላል ። ከዚህም በቀር ፤ ሚኒስትሩ ከሌሎች ባለሥልጣኖች የተሰጡትን የመንጃ ፈቃዶች በዚህ አዋጅ ለተመለከተው ጉዳይ ደንበኛ ሆነው እንዲሠራባቸው እንዲፈቀድ ማድረግ ይችላል ።

### ፳፩/ የማዘጋጃ ቤቶች ሥልጣን ፤

ከሥራው የሚበዛው ክፍል በማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ የሆነ ፤ የግል ወይም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠራ ተሽከርካሪ ለመንዳት የተቀጠረው ሰው ልዩ ፈቃድ እንዲኖረውና ስለዚህ በሕግ የሚወሰነውን ግብር እንዲከፍል ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት ይችላል ። ስለሆነም ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት እንዲህ ያለውን ልዩ የመንጃ ፈቃድ መስጠትን ምክንያት አድርጎ እንዲህ ያለውን ሰው እንደገና እንዲፈተን ወይም እንዲመረመር ማስገደድ አይችልም ።

## ክፍል ሦስት

## የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ስለመከታተልና ስለመቆጣጠር

## ሀ/ የመንገድ ትራንስፖርት አስተዳደር

### ፲/ የአስተዳደሩ ሥራ ፤ ተግባርና ሥልጣን ፤

፩/ አስተዳደሩ ሕግን ተከትሎ የግልና የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩትን ድርጅቶች ፤ የተሽከርካሪዎችን ባለቤትነት ፤ የሥራ አካሄድና አገልግሎት ፤ እንዲሁም የዕቃዎችንና የመንገደኞችን አጓጓዝ ሁኔታ ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራልም ።

፪/ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጠቅላላነት ሳይቀነስ አስተዳደሩ ሕጉን ተከትሎ ከዚህ የሚከተሉትን ለማድረግ ሥልጣን አለው ፤

ሀ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች በማኅበር እንዲቋቋሙና እንዲመዘገቡ ለመፍቀድ ፤

ለ/ የግልና የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩትን ተሽከርካሪዎች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ በተመለከተው መሠረት ለመመዝገብ ፤

ሐ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች እንዲቋቋሙ ለማትጋት ይህ በቂ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነም እንደዚህ ያሉትን ማኅበሮች ለማቋቋም ፤

መ/ ሥራውን ለማካሄድ ሙሉ ኃላፊነት ያልተቀበለውን የማናቸውንም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበርን ለሥራ ለመምራትና ለመቆጣጠር ፤

www.chilot.me



ሠ/ ሥራውን ለማካሄድ ሙሉ ኃላፊነት የተቀበለውን የማናቸውንም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበር ሥራ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ፤

ረ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ ለመሥራት የሚከፈለውን አነስተኛና ከፍተኛ ታሪፍ ለመወሰንና ለማስፈጸም ፤

ሰ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ የሚሠራበትን ፕሮግራም ለመ ወሰንና ለማስፈጸም ፤

ሸ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች ራሳቸው በማይሠሩበት ጊዜ ተመላላሹ ሕዝብና በሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አማካይ ነት ዕቃዎችን የሚጭኑ ሰዎች የሚገለገሉባቸው አስፈላጊና ተጨማሪ ድርጅ ቶችን ለማቋቋም ወይም ለማስገኘት ፤ ለመጠበቅና ለማካሔድ ፤

ቀ/ ስለግል የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ጉዳይ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፩ እስከ ፲፬ የተመደበውን ለማስፈጸም ፤

በ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከሚፈለገው እንዳይበልጥ ለማረጋገጥና በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፫ የተወሰነው ጭምር እንዲጠበቅ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ፤

ተ/ አስተዳደሩ ባቋቋማቸው ድርጅቶችና በሰጠው አገልግሎት በመጠቀማቸው ምክንያት የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች የሚከፍሉትን ታሪፍ ለመወሰንና ለመሰብሰብ ፤

ቸ/ በተሽከርካሪው የጭነት ችሎታ መጠን ወይም ባለው የመንገደኛ መቀመጫ መሠረት ፤ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠራ እያንዳንዱ ድርጅት ለአስተዳደሩ በዓመት የሚከፍለውን ታሪፍ ለመወሰንና ለመሰብሰብ ፤

ኀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፰፩ በተመደበው መሠረት የሚቋቋመውን ገንዘብ (ፈንድ) ለማስተዳደር ፤

ነ/ በጠቅላላው የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ በሚገባና ለኤኮ ኖሚ በሚጠቅም አኳኋን የሚካሔድ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ወይም ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ ፤

ኘ/ የግልና የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸውን የማስረጃዎችና የሪፖርቶች ዓይነት ለይቶ ለመወሰንና ፤

አ/ በዚህ አዋጅ እንደተወሰነው ፤ በሥልጣኑ ሥር ስለሚካሔደው ስለማናቸውም ጉዳይ ደንብ ለማውጣት ፤

<u>የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ማስታወሻ</u>

<u>የማመላለሻ (ትራንስፖርት) ቦርድ ፈቃድ ለመስጠት ያለው ሥልጣን ፤</u>

በድሮው ሕግ መሠረት ያዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማመላለሻ (ትራንስፖርት) ቦርድ ፈቃድ የሰጣቸውን የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች የሚያገለግሉበትን ጊዜ የሚወስን የሰ ዓት ቁጥጥር ለማድረግ ሥልጣን አለው ብሎ ወሰነ ። የዚህ ሥልጣን ዋና ዓላማ ለተጓዦች ጥሩ አገልግሎትን ለመስጠት ብቻ ነው ። ጽሑፉም ሆነ የሕጉ መንፈስ ቦርዱ ሥልጣኑን በሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች መካከል የሚደረገውን ውድድር ለመወሰን እንዲጠቀምበት አይፈ ቅድም ።

www.chilot.me



፲፩/ የንግድና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን አገልግሎትና ዝውውር ስለመወሰን ፤

ለግል የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከውጭ አገር የመጣውን ማናቸውንም የንግድ ወይም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ፤ አስተዳደሩ ሳይስማማበት ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት መሸጥ ፤ ማከራየት ወይም በሌላ አኳኋን ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲውል ማድረግ አይፈቀድም ።

፲፪/ የራስን ዕቃዎች ለማጓጓዝ በራስ ተሽከርካሪ ስለመጠቀም ፤

ማናቸውም ሰው ባስፈለገው ጊዜ ወይም አልፎ አልፎ የራሱን ዕቃዎች በራሱ ተሽከርካሪ ለማጓጓዝ ያለውን መብት በዚህ ክፍል የተመደበው አይወስነውም ወይም አያግደውም ።

፲፫/ ስለብቸኛ መብቶችና ብቸኛ ኮንትራቶች ፤

፩/ አስተዳደሩ በእርግጥ ለሕዝብ የሚጠቅም መስሎ ሲታየው ፤ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ ለሚሠሩ ድርጅቶች ወይም ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች ብቸኛ ወይም የተወሰኑ መብቶች ለመስጠት ይችላል ። ስለሆነም ፤ ሕዝቡ ራሱ በሚያዋጣው ገንዘብና በጉልበቱ የተሠራና የሚጠገን መንገድ ሲሆን የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን እስኪረከበው ድረስ የመሥመሩ ፈቃድ በቅድሚያ የሚሰጠው መንገዱን ያሠራው ሕዝብ ለሚያቆመው ድርጅት ይሆናል ።

፪/ ዕቃዎችን የሚያስጭን ማናቸውም ሰው የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ ከሚሠሩ ድርጅቶች ጋር ስለዕቃዎቹ ብቸኛ ኮንትራት ለማድረግ ያለውን መብት በዚህ ክፍል የተመደበው አይከለክለውም ወይም አይወስነውም ።

## ሐ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች ።

፲፬/ ስለሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች መቋቋም ፤

፩/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች ፤ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮችን ለማቋቋምና የማኅበሩ አባሎች ለመሆን ይችላሉ ።

፪/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠራ ማናቸውም ድርጅት ባንድ ጊዜ ከአንድ (፩) ማኅበር ለበለጠ ማኅበርተኛ ሊሆን አይችልም ።

፫/ ቁጥራቸው ከሃምሳ (፶) ያነሰ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች ማኅበር ሊያቋቁሙ አይችሉም ፤ ስለሆነም አስተዳደሩ በቂ ምክንያት ሲኖረው ይህንን ቁጥር ለጊዜው ለመቀነስ ይችላል ።

፬/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ በሚገባና ለኤኮኖሚ በሚጠቅም አኳኋን ለማካሄድ የሚበጅ መስሎ ሲታየው ፤ አስተዳዳሪው ማኅበሮች በአውራጃ ወይም በቀበሌ ተለይተው እንዲቋቋሙ ማድረግ ይችላል ።

፲፭/ ስለማኅበሮች ሕጋዊ አቋምና መመዝገብ ፤

፩/ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ ፤ ከአንቀጽ ፬፻፬ እስከ ፬፻፹፪ የተጻፈው ፤ ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች የጸና ይሆናል ። ሆኖም በነ

www.chilot.me



ዚህ አንቀጾች ለአገር ግዛት ሚኒስቴርና ለማኅበሮች ጽሕፈት ቤት የተሰጠው ኃላፊነትም ሁሉ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮችን በሚመለከተው ጉዳይ በዚህ አዋጅ ለአስተዳደሩ ተዛውሮ በአስተዳደሩ ይካሄዳል ። ከዚህም በቀር በክፍል (ሐ) የተመደበው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፬፻፬ እስከ ፬፻፹፪ ከተመደበው ጋር የማይስማማ ሆኖ ቢገኝ በዚህ ክፍል (ሐ) የተጻፈው ይጸናል ።

፪/ ማንኛቸውም ማኅበር ወዲያው እንደ ተቋቋመ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ የማኅበሩን መቋቋሚያ ሠነድ ወይም ደንብ ለአስተዳደሩ ማቅረብ አለበት ።

፫/ የማኅበሩ መቋቋሚያ ሠነድ ወይም ደንብ ለአስተዳደሩ መቅረብ ማኅበሩ ለመመዝገብ ለአስተዳዳሪው ማመልከቻ እንዳቀረበ ይቆጠራል ። አስተዳዳሪውም ፤

ሀ/ የማኅበሩ መቋቋሚያ ሠነድ ወይም ደንብ ሕግን ወይም የተወሰነውን ደንብ የፈጸመ ከሆነ ፤

ለ/ ጉዳዩን የሚመለከተው ማናቸውም ሕግ የሚያስገድደው ማናቸውም ሌላ ግዴታ የተፈጸመ ከሆነ ፤

ሐ/ አስተዳዳሪው የወሰነውንና ጸንቶ የሚሠራበትን ማናቸውንም የሥራ መምሪያ ማኅበሩ የፈጸመ ከሆነ ፤ ማኅበሩን ይመዘግበዋል ።

፬/ አስተዳዳሪው የማኅበሩን መመዝገብ የማይቀበለው የሆነ እንደሆነ ይህንኑ ለማኅበሩ ማስታወቅና ምክንያቱን መግለጽ አለበት ።

፭/ አስተዳዳሪው ማመልከቻው በቀረበለት በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ለምዝገባ በቀረበለት ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ሳያደርግ ቢቀር ማኅበሩ እንደተመዘገበ ይቆጠራል ።

፮/ ማኅበሩ በአስተዳደሩ ከተመዘገበ በኋላ ሕጋዊ ሥራዎችን ሁሉ መሥራት ይችላል ።

የተጠቀሰው ሕግ

የፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፪) አን. ፬፻፬—፬፻፹፪ ።

፲፱/ የማኅበሮች የሥራ ዓላማ ፤

የሕዝብ የንግድ የትራንስፖርት ማኅበሮች የሥራ ዓላማ ፤ በጠቅላላው የማኅበርተኞች ጥቅም የሚስፋፋበትንና ዕቃዎችንና መንገደኞችን በሚገባና ለኤኮኖሚ በሚጠቅም አኳኋን ለማጓጓዝ የሚቻልበትን ዘዴ ሁሉ ለመፈጸምና በተለይም የሚከተለውን ማከናወን ነው ፤

፩/ ለጋራ ጥቅም የሚያገለግሉትን ድርጅቶች ፤ ለምሳሌ የመንገድ ባቢያዎችን ፤ የጭነት ማከፋፈያ ጽሕፈት ቤቶችንና ጋራዦችን ማቋቋምና ማካሔድ ፤

፪/ ለማኅበርተኞች ሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎችና አስፈላጊ ነገሮች ፤ ለምሳሌ ነዳጅንና መለዋወጫ ዕቃዎችን በፈጁት ዋጋ ማቅረብና ፤

፫/ ማኅበርተኞች በየበኩላቸው ስለንግድ የመንገድ ትራንስፖርት የወጡት ሕጎች ሁሉ እንዲከበሩ ማድረግ ነው ።

፳/ አስተዳዳሪው ለመጀመሪያ ጊዜ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበርን ሥራ ለመምራትና ለመከታተል የሚችል ስለመሆኑ ፤

አስተዳዳሪው ለሚወስነው ለመጀመሪያ ጊዜና የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበር የራሱን ሥራ በራሱ ኃላፊነት ለመምራት ችሎታና ፈቃድ ያለው መሆኑ እስኪ

www.chilot.me



ሪጋገጥ ድረስ ፤ አስተዳዳሪው የእያንዳንዱ የትራንስፖርት ማኅበርን ሥራ ለመምራትና ለመከታተል ይችላል ። ይህን በሚያደርግበትም ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከተውን ማኅበር ሥልጣን ሁሉ ይዞ ይሠራበታል ።

፳፩/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ገንዘብ (ፈንድ)

፩/ ከዚህ የሚከተሉ ገቢዎች የሚገኙበት ገንዘብ (ፈንድ) ይቋቋማል ።

ሀ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ከሚሠሩ ድርጅቶች አስተዳደሩ የሚቀበለው የአገልግሎት ዋጋ ሁሉ ፤

ለ/ ከሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮች አስተዳደሩ የሚቀበለው የአገልግሎት ዋጋ ሁሉ ፤

ሐ/ ለፈንዱ የሚሰጡት ሌሎች የገንዘብ መዋጮዎች ወይም ስጦታዎች ።

፪/ ይህ ፈንድ በአስተዳደሩ ስም በተለየ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ሆኖ አስተዳደሩ የሥራውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በዓመት በጀቱ መሠረት ይህንኑ ወጪ ለማድረግ ኃላፊ ይሆናል ።

፫/ አስተዳዳሪው የዚህን ፈንድ የወጪና የገቢ ሂሣብ ይይዛል ።

፬/ አስተዳዳሪው ያለፈውን ዓመት ገቢና ወጪ መግለጫ በየዓመቱ ያዘጋጃል ፤ መግለ ጫውም በየዓመቱ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል ።

## ክፍል አራት

## መጨረሻ ውሳኔዎች ፤

፳፪/ ግብርና ቀረጥ ከመክፈል ነፃ ስለመሆን ፤

ተሽከርካሪዎች ሲመዘገቡና የመንጃ ፈቃዶች ሲሰጡ ተገዝተው ለሚሰጡ ዕቃዎች ዋጋና ለአገልግሎት ዋጋ ከሚከፈለው በቀር ፤ ከዚህ በታች የተመለከቱት ከግብርና ከቀረጥ ነፃ ናቸው ፤

፩/ በጋራ ጥቅም መሠረት በስምምነት ወይም በኢንተርናስዮናል ልማድ ፤ የዲፕሎማ ቲክና የቆንስላ መልእክተኞች ፤ ሌሎች የውጪ አገር መልእክተኞችና ድርጅቶች ወይም የኢንተርናስዮናል መልእክተኞችና ድርጅቶች ከታክስ ነፃ ናቸው ብሎ ሚኒስትሩ ሲወስን ።

፪/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ልዩ መብት ያላቸው ፤ ሥራቸው ከታክስ ነፃ የሆነ ድር ጅቶች ።

፳፫/ የሥልጣን ውክልና ለመስጠት ።

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተስማምቶበት በነጋሪት ጋዜጣ በሚወጣ ደንብ ፤ ሚኒስ ትሩ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭ በክፍል (፪) (ሀ) ና (ለ) የተመለከቱ ሥልጣኖቹን ለተመረጡና በተባለው ደንብ ውስጥ ለሚጠቀሱ ማዘጋጃ ቤቶች በውክልና ይሰ ጣል ።

www.chilot.me



## ሠንጠረዥ

| በተሽከርካሪው በመጀመሪያውና በመጨረሻው እክስ መካከል መኖር የሚገባው ርቀት ልክ በሳንቲ ሜትር ። | ለተሽከርካሪ መኪና እክሶች የሚፈቀድ የማይታለፍ ጭነት ልክ በኪሎ ግራም ። |
|---|---|
| 120 | 14,515 |
| 150 | 14,515 |
| 185 | 14,515 |
| 215 | 14,515 |
| 245 | 14,790 |
| 275 | 15,230 |
| 305 | 15,670 |
| 335 | 16,105 |
| 365 | 16,545 |
| 395 | 16,975 |
| 425 | 17,400 |
| 455 | 17,875 |
| 485 | 18,250 |
| 520 | 18,670 |
| 550 | 19,085 |
| 580 | 19,500 |
| 610 | 19,915 |
| 640 | 20,320 |
| 670 | 20,730 |
| 700 | 21,135 |
| 730 | 21,530 |
| 760 | 21,930 |
| 790 | 22,325 |
| 820 | 22,720 |
| 855 | 23,110 |
| 885 | 23,495 |
| 915 | 23,880 |
| 945 | 24,265 |
| 975 | 24,645 |
| 1005 | 25,020 |
| 1035 | 25,395 |
| 1065 | 25,765 |
| 1095 | 26,130 |
| 1130 | 26,500 |
| 1160 | 26,860 |
| 1190 | 27,220 |
| 1220 | 27,580 |
| 1250 | 27,930 |
| 1280 | 28,285 |
| 1310 | 28,635 |
| 1340 | 28,980 |

www.chilot.me



| ርቀት ልክ በሳንቲ ሜትር ። | በኪሎ ግራም ። |
|---|---|
| 1370 | 29,325 |
| 1400 | 29,665 |
| 1450 | 30,175 |
| 1500 | 30,675 |

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፪/፱ (፲፱፻፶፭) ማ. ፵፭ ታረመ ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ.ም.

## ፳፫/፭ (፲፱፻፶፭) ሕ. ፪፻፫፱.*

## ስለትራንስፖርት በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ

### አንቀጽ ፩

### ደንብ ለማውጣት የተፈቀደበት ሥልጣን ፤

የመገናኛ ሚኒስቴር ስለትራንስፖርት በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. በቁጥር ፴፰ በወጣውና በተሻሻለው አዋጅ በአንቀጽ ፶፱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደምብ አውጥቷል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፶፰) ት. ፵፮ አን. ፪ (፲፬)፣ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፪ (፲፬) በግ.ሳ. ተሻሻለ ። (ቀድሞ የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር የነበረው በሁለት ተከፍሎ የሥራ ሚኒስቴር ፣ የመገናኛ ሚኒስቴር ተባለ ።)

### አንቀጽ ፪

### አጭር አርእስት ፤

ይህ ደንብ «የ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

### አንቀጽ ፫

### ስለ መሻር ፤

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሕግ ክፍል ማስታወቂያዎች በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ተሽረዋል ።

---

*የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳፫/፮ (፲፱፻፶፯) ማ. ፶፩ ታረመ ፤ በ፳፫/፰ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፪፻፲ ፣ በ፳፰/፱ (፲፱፻፷፩) ሕ. ፫፻፷፩ ተሻሻለ ፤ በ፳፭/፳፫ (፲፱፻፶፰) ት. ፵፮ በግ.ሳ. ተሻሻለ ።

www.chilot.me



፮/ «መስቀልኛ መንገድ» ማለት ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ ጐዳናዎች ወይም መንገዶች በመስቀልኛ መልክ የሚገናኙበት ሥፍራ ነው ።

፯/ «ነጠላ መንገድ» ማለት በአንድ ረድፍ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን ለማስተላለፍ በቂ ስፋት ያለው የመንገድ ክፍል ነው ።

፰/ «የማብሪያ ጊዜ» ማለት ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መውጫ ድረስ ያለው ጊዜና እንደዚሁም በአየር ምክንያት ለማየት የማይቻልበት ወቅት ነው ።

፱/ «ሞተር ቢስክሌት» ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው ።

፲/ «አውቶቡስ» ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው ።

፲፩/ «ባለሞተር ተሽከርካሪ» ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው ።

፲፪/ «የማዘጋጃ ቤት ክልል» ማለት ማዘጋጃ ቤት ወይም የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት በቀጥታ የሚያስተዳድረው ቀበሌ ወይም የከተማ ክልል ነው ።

፲፫/ «የማዘጋጃ ቤት መንገድ» ማለት በማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም መንገድ ነው ።

፲፬/ «ባለአንድ አቅጣጫ ጐዳና ወይም መንገድ» ማለት ተሽከርካሪዎች በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲሄዱበት የተፈቀደ ጐዳና ወይም መንገድ ነው ።

፲፭/ «ተሽከርካሪን በመዘግየት ማቆም» ማለት ተሳፋሪዎችን ለማሳፈር ወይም ለማውረድ ወይም የንግድ ዕቃዎችን ለመጫን ወይም ለማራገፍ ከሚያስፈልገው ጊዜ በላይ ተሳፋሪ ወይም የንግድ ዕቃ በውስጡ ቢኖርም ባይኖርም የተሽከርካሪው መቆም ነው ።

፲፮/ «የእግረኛ ማቋረጫ» ማለት እግረኞች አቋርጠው እንዲያልፉበት ተብሎ በመንገዱ ላይ የመንገድ ምልክት የተደረገበት የመንገድ ክፍል ነው ።

፲፯/ «አዋጅ» ማለት በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም. በቁጥር ፵፭ የወጣውና የተሻሻለው የትራንስፖርት አዋጅ ነው ።

፲፰/ «የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ መኪና» ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው ።

፲፱/ «የሐዲድ መንገድ ማቋረጫ» ማለት መንገድና የሐዲድ መንገድ የሚገናኙበት መስቀልኛ ሥፍራ ነው ።

፳/ «ቀኝ» እና «ግራ» ማለት ተላላፊው በሚሄድበት አቅጣጫ በቀኙ ወይም በግራው ያለው ወገን ነው ።

፳፩/ «መንገድ» ማለት ለተሽከርካሪዎች መሄጃ ተብሎ አስፋልት ወይም ሌላ ዓይነት ልባስ የተደረገበት የጐዳና ወይም የመንገድ ክፍል ነው ። ይኸውም የጐዳናውን ወይም የመንገዱን ጠርዝ አይጨምርም ።

፳፪/ «የመንገድ ምልክት» ማለት ተሽከርካሪዎች የሚተላለፉበት አቅጣጫ ለመወሰንና እንዲሁም ለተላላፊዎች ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የሚያገለግል የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን የሚያወጣው ማንኛውም ምልክት ነው ።

፳፫/ «የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን» ማለት ከዚህ የሚከተሉት አባሎች የሚገኙበት በቦርዱ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው ።

ሀ/ <u>በእያንዳንዱ ማዘጋጃ ቤትና ከተማ ፤</u>

የመገናኛ ሚኒስቴር ወኪል ፤ ከንቲባው ወይም እርሱ የሚወክለው ሰውና የፖሊሱ አዛዥ ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ፤

www.chilot.me



ለ/ <u>በእያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ፤</u>

የመገናኛ ሚኒስትር ወኪል ፤

ጠቅላይ ገዥው ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ፤

የፖሊሱ አዛዥ ወይም እርሱ የሚወክለው ሰውና የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን ዲሬክተር ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ፤

እያንዳንዱ የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን ኃላፊነቱ ለቦርዱ ሆኖ ቦርዱ በየጊዜው በሚወስነው ጠቅላላ መምሪያና በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት ሥራውን ያከናውናል ። ቦርዱ ሕዝቡና እያንዳንዱ የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን የሚፈጽመው ከዚህ ደንብ ጋር የሚስማማ ትእዛዝና ማስታወቂያ በየጊዜው ለማውጣት ይችላል ። የመንገድ ምልክት ባለሥልጣኖች ከቦርዱ የሚሰጠውን ትእዛዝና ማስታወቂያ በሥራ ላይ ማዋል አለባቸው ።

፳፬/ «ግማሽ ተሳቢ» ማለት ለመንገደኛ ወይም ለጭነት ማጓጓዣ የሚያገለግልና ሞተር ባለው በሌላ መኪና የሚሳብ ሆኖ ነጠላ ክብደቱና የተሸከመውም የጭነቱ ክብደት ጭምር በከፊል በሌላው መኪና ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላው መኪና እንዲሳብ ተደርጎ የተሠራ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው ።

፳፭/ «ተሽከርካሪን ለጥቂት ጊዜ ማቆም» ማለት ተሳፋሪዎችን ለማሳፈር ወይም ለማውረድ ወይም የንግድ ዕቃዎችን ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሲባል በመጫኑ ወይም በማውረድ ጊዜ ብቻ በውስጡ ተሳፋሪ ወይም የንግድ ዕቃ ቢኖርም ባይኖርም ተሽከርካሪው ለጥቂት ጊዜ ሲቆም ነው ።

፳፮/ «ተሽከርካሪን ለጊዜው ማቆም » ማለት በውስጡ ተሳፋሪ ወይም የንግድ ዕቃ ቢኖርም ተሽከርካሪን ለጊዜውም ቢሆን ማቆም ነው ።

፳፯/ «የማቆሚያ መስመር» ማለት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት ወይም የቁም ምልክት ፤ ወይም የትራፊክ ፖሊስ እንዲቆም ምልክት ሲሰጥ ትራፊክ እንዲቆምበት ተብሎ በጐዳና ወይም በመንገድ ላይ የሚደረግ የመስመር ምልክት ነው ።

፳፰/ «ጐታች መኪና» ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጐተት የሚያገለግል ሆኖ የተጐታቹ ተሽከርካሪ ነጠላ ክብደቱና ጭነቱም ጭምር በሱ ላይ እንደሚያርፍ ተደርጎ የተሠራ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው ።

፳፱/ «ትራፊክ» ማለት በማንኛውም ጐዳና ወይም መንገድ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ተቀምጦባቸው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚሄዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው ።

፴/ «የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት» ማለት ተላላፊዎችን ለማቆምና ለማስተላለፍ የሚያገለግል በእጅ ወይም በመካኒክ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል የሚካሄድ የመንገድ ምልክት ነው ።

፴፩/ «ተሳቢ» ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለውና ጐታች በሆነ በሌላ ተሽከርካሪ መኪና ሊቀጠልና ሊጐተት የሚችል ነጠላ ክብደቱ በጐታቹ መኪና ላይ እንዳሚያርፍ ተደርጎ የተሠራ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው ።

፴፪/ «የምድር ባቡር» ማለት በምድር ባቡር ሐዲድ ላይ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው ።

፴፫/ «ተሽከርካሪ» ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው ።

፴፬/ «በመጐተት ያለ ተሽከርካሪ» ማለት ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ያልሆነ በሌላ ተሽከርካሪ የሚሳብ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው ።

www.chilot.me



፳/ ስለ ተሽከርካሪ ነጂ ፤

ማናቸውም ሰው ፦

ሀ/ በመድኃኒት ወይም በመጠጥ ተመርዞ ወይም ፤

ለ/ በሰውነቱ ጤናማ ያለመሆን የተነሳ ወይም ፤

ሐ/ በአእምሮ ጉድለት የተነሳ አደጋ ለማያስከትል አኳኋን ለመንዳት በማይችልበት ጊዜ ማናቸውንም ተሽከርካሪ መኪና እንዳይነዳ ክልክል ነው ።

፳፩/ ተሽከርካሪ መኪና መንዳት የሚከለከልበት ሁኔታ ፤

ማናቸውም ሰው አሠራሩ ፤ ዕቃዎቹና ሁኔታው በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ ወይም መብቱ የሚፈቅድበት ባለሥልጣን በሚያወጣው ማናቸውም ሌላ ደንብ ከተወሰነው ውጭ የሆነ ተሽከርካሪ መኪና እንዳይነዳ ክልክል ነው ።

፳፪/ የተሽከርካሪዎችንና የእንስሶችን እንቅስቃሴ የመቆጣጠር ተግባር ፤

ሀ/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ተሽከርካሪው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ መሪውን ፤ ወይም ተሽከርካሪውን ለመንዳትና ለመቆጣጠር የሚያገለግሉትን የእጅ መግሪያዎች መያዝ አለበት ።

ለ/ ማናቸውም ሰው በእንስሳ ላይ ተቀምጦ ወይም እየነዳ ፤ ወይም እየሳበ በመንገድ ወይም በጐዳና ላይ በሚተላለፍበት ጊዜ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ።

## አንቀጽ ፯

## ጠቅላላ የትራፊክ ደንብ

፩/ ትራፊክ ቀኙን ይዞ እንዲሄድ ግዴታ ስለመሆኑ ፤

በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልታዘዘ በቀር ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ በተቻለ መጠን የመንገዱን ቀኝ ጥግ ይዞ መሄድ አለበት ።

፪/ በዝግታ ስለሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ፤

ከሚከተሉትና ባጠገቡ ከሚተላለፉ ተሽከርካሪዎች ፍጥነቱን አሳንሶ የሚሄድ ተሽከርካሪ ከቀኝ በኩል የሚገኘውን የጐዳናውን ወይም የመንገዱን ጠርዝ ተጠግቶ መሄድ አለበት ።

፫/ ማየት ባልተቻለበት ጊዜ ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ እንደልብ ለማየት ባልቻለበት ጊዜ የሚሄድበትን ነጠላ መንገድ ለውጦ ወደ ሌላው መሥመር ለመሻገር አይፈቀድለትም ።

፬/ በመንገዶች ስለመጠቀም ፤

ሀ/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ አውራ ጐዳና ካለ በአውራ ጐዳናው ላይ ብቻ መንዳት አለበት ።

www.chilot.me



ለ/ ለአንድ ዓይነት ተሽከርካሪ ተብሎ የተዘጋጀ የተለየ ነጠላ መንገድ ሲኖር ማንኛ ውም የዚህ ዓይነት ተሽከርካሪ ነጂ በዚሁ ነጠላ መንገድ ብቻ መንዳት አለበት ። የሌላ ዓይነት ተሽከርካሪ ነጂዎች በዚሁ ነጠላ መንገድ እንዲተላለፉ አይፈቀድም ።

፩/ የተከፋፈሉ መንገዶች ፤

ሀ/ ጐዳና ወይም መንገድ በድንጋይ ምልክት ፣ በአትክልት ፣ በትራፊክ ደሴትና ይህን በመሳሰለ የተከፋፈለ እንደሆን እያንዳንዱ የጐዳናው ወይም የመንገዱ አጋማሽ ባለአንድ አቅጣጫ ጐዳና ወይም መንገድ ሆኖ ይቆጠራል ።

ለ/ በማያቋርጥ የቀለም መሥመር በተከፈለ ጐዳና ወይም መንገድ ላይ የሚጓዙ ተሽ ከርካሪዎች የቀኙን ወገን መሥመር ይዘው መሄድ አለባቸው ። የቀለሙ መሥመር በሚያቋርጥበት ቦታ ላይ ካልሆነ በቀር ፤ ተሽከርካሪዎች ከቀኝ ወደ ግራ እንዲሻገሩ አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፮

## ስለትራፊክ ምልክቶች

፩/ «እለፍ» የሚል ምልክት የሚሰጥ ፤

ሀ/ በትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት ሲሆን አረንጓዴ ቀለም ወይም አረንጓዴ መብራት ይወጣል ።

ለ/ በፖሊስ ሲሆን ተሽከርካሪው እንዲያልፍ ወደሚፈቀድበት አቅጣጫ ፖሊሱ አንድ ወይም ሁለት ክንዶቹን ዘርግቶ መዳፉን በመክፈት ያመለክታል ።

፪/ «ቁም» የሚል ምልክት የሚሰጥ ፤

ሀ/ በትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት ሲሆን ቀይ ቀለም ወይም ቀይ መብራት ይወጣል ።

ለ/ በፖሊስ ሲሆን ተሽከርካሪው ወደሚቆምበት መሥመር ፖሊስ አንድ ወይም ሁለት ክንዶቹን ዘርግቶ የእጁን መዳፍ ከፍቶ ያመለክታል ።

፫/ «ተጠንቀቅ» የሚል ምልክት ሲሰጥ ፤

ሀ/ በትራፊክ መቆጣጠሪያ ሲሆን ብጫ መብራት ይወጣል ወይም ብጫና ቀይ መብ ራት በመፈራረቅ ይወጣል ።

ለ/ በፖሊስ ሲሆን ፖሊሱ አንድ ክንዱን ከራሱ በላይ በቀጥታ ዘርግቶ ያመለክታል ።

፬/ የፖሊሱ የምልክት አሰጣጥ በእርግጥ የሚያጠራጥር ካልሆነ በስተቀር የምልክቱ አሰ ጣጥ በዚህ ደንብ በተወሰነው አኳኋን ባይሆንም ፖሊሱ የሚሰጠው ትእዛዝ ግድ መፈ ጸም አለበት ።

## አንቀጽ ፯

## የትራፊክ ምልክቶች ትርጉም

፩/ «እለፍ» የሚል ምልክት ፤

ሀ/ በትራፊክ መቆጣጠሪያ ወይም በፖሊስ ሲሰጥ ፤

፩/ ተሽከርካሪው ጉዞውን በቀጥታ ወደፊት ለመቀጠልና ወደቀኝ ለመታጠፍ ይችላል ።

www.chilot.me



ለ/ በማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ ሲሆን ከስድስት (፮) ሰዓት በላይ ፤ በአንድ ቦታ ላይ መቆየት የለበትም ።

፪/ አንድ ተሽከርካሪ ባለማቋረጥ በዚህ በ፲፫ኛው አንቀጽ በተራ ቁጥር (፩) ከተወሰነው ጊዜ በላይ በአንድ ቦታ ላይ ቢቆይ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፵፪ የተጻፈው ይፈጸምበታል ።

፫/ ማናቸውም ሰው የተጐዳ ወይም የተበላሸ ተሽከርካሪ መኪና ከመንገድ ላይ በሚያነሳበት ጊዜ በጐዳናው ላይ የወዳደቁትን የመስታወት ስብርባሪዎችና በሌሎች ተላላፊዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉትን ነገሮች ሁሉ ከመንገዱ ላይ ማስወገድ አለበት ።

## አንቀጽ ፲፬

### ስለጢስና ዘይት ፤

ማናቸውም ሰው ለአንድ ዓይነት ተሽከርካሪ ከሚገባው በላይ ጢስ ፤ እንፋሎት ፤ ዘይት ወይም ነዳጅ የሚተፋ ሆኖ ለሌሎች ተላላፊዎች ጉዳት የሚያመጣ ወይም የሚያውክና በደንብ ያልተጠገነ ተሽከርካሪ እንዲነዳ ወይም በመንገድ ላይ እንዲያቆም አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፲፭

### ከመጠን በላይ ድምፅ ስለማሰማት ፤

ማናቸውም ሰው በሚገባ ባለመታደሱ ወይም የቴክኒኩ ሁኔታ በሚገባ ባለመጠበቁ ወይም ከአጫጫኑ ጉድለት የተነሳ ከመጠን በላይ ድምፅ የሚያሰማ ተሽከርካሪን በማንኛውም ጐዳና ወይም መንገድ ላይ እንዲነዳ አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፲፮

### በአንዳንድ መንገዶች እንዳይሄድባቸው ስለመቆጣጠር ፤

የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን ደንብ ወይም ማስታወቂያ በማውጣት ወይም የመንገድ ምልክት በማድረግ ተሽከርካሪዎች ሁሉ ወይም ከተሽከርካሪዎች አንዱ ክፍል ፤ እግረኞች ወይም እንስሶች ወደ ማናቸውም መንገድ ወይም የመንገድ ክፍል እንዳይገቡ ወይም እንዳይወጡ መቆጣጠር ወይም መከልከል ይቻላል ።

## ፫ኛ/ ክፍል ፤ ስለፍጥነት

## አንቀጽ ፲፯—፲፰

[በ፳፰/፱ (፲፱፻፷፩) ሕ. ፫፻፷፩ አን. ፫ ተሻረ ፣ ፳፩ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፱ ።]

## አንቀጽ ፲፱

### በዝግታ ስለመንዳት ፤

ማንኛውም የተሽከርካሪ ነጂ ከመስቀልኛ መንገድ ፤ ከጐባጣ መንገድ ፤ ከእግረኛ ማቋረጫ ፤ ከጠማማ መንገድ ፤ ከጠባብ ድልድይ ፤ ከኮረብታ ጫፍ ወይም ቁልቁለት መንገድ ሲደ

www.chilot.me



ርስ ፤ እንዲሁም በጠባብ ድልድይ ወይም በጠባብ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ ላይ በሚነዳበት ጊዜ ፤ የማየትም ኃይል በተቀነሰበት ወቅትና ለእግረኛና በመንገዱ በሚጠቀሙት ሁሉ ፤ አደጋ ሊያስከትል በሚያሰጋበት ጊዜ ሁሉ የተሽከርካሪውን ፍጥነት በጣም መቀነስ አለበት ።

## ፱ኛ/ ክፍል ፤ ስለትራፊክ ደንብ

### አንቀጽ ፳

### ተሽከርካሪ ተከትሎ ስለመንዳት ፤

ማናቸውም ሰው ሌላ ተሽከርካሪ ተከትሎ ሲነዳ ፤ በማናቸውም ጊዜ ያላንዳች አደጋ ማቆም እንዲችል የራሱንና ከፊቱ የሚሄደውን ተሽከርካሪ ፍጥነት ፤ የጐዳናውን ሁኔታ ተላላፊው ግልጽ ሆኖ መታየቱን ፤ ብዛቱንና ሁኔታውን በማመዛዘን በሚነዳው ተሽከርካሪና ከፊቱ ባለው ተሽከርካሪ መካከል በቂ ርቀት ጠብቆ መሄድ አለበት ።

### አንቀጽ ፳፩

### ተከታትለው ስለሚሄዱ ተሽከርካሪዎች ፤

ቁጥራቸው አራት (፬) ወይም ከአራት በላይ በሆነ ከከተማ ክልል ውጭ ተከታትለው በሚሄዱ ተሽከርካሪዎች መካከል ተሽከርካሪ የሚነዳ ማናቸውም ሰው ሌላው ተሽከርካሪ ያለአንዳች አደጋ ከመካከል ለመግባት እንዲችል በተሽከርካሪው መካከል ሰፋ ያለ ርቀት ጠብቆ መንዳት አለበት ፤ ይሁን እንጂ ይህ ደንብ ፊላ አጅበው ወይም በሌላ ልዩ አጋጣሚ ምክንያት በአጀብ ለሚሄዱ ተሽከርካሪዎች አይጸናም ።

### አንቀጽ ፳፪

### ፊት ለፊት ስለመገናኘት ፤

፩/ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚተላለፉ ሁለት ተሽከርካሪዎች ከሚጓዙበት መስመር ሳይዛነፉ ሁለቱም ተሽከርካሪዎች ያላንዳች አደጋ ለማለፍ በማያስችል ጠባብ መንገድ ላይ የተገናኙ እንደሆነ ሁለቱም ነጂዎች ፍጥነታቸውን ቀንሰው በተቻለ መጠን የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዘው መሄድ አለባቸው ።

፪/ ተሽከርካሪዎች በዳገት ወይም በቁልቁለት ላይ ሲገናኙ ቁልቁል የሚሄደው ተሽከርካሪ ነጂ ወደ አቀበት ለሚወጣው የተሽከርካሪ ነጂ የማለፍ ቅድሚያ መስጠት አለበት ፤ ለአውቶቡስ የሆነ እንደሆነ ግን በማንኛውም ወገን ቢሆን ሁል ጊዜ የማለፍ ቅድሚያ ይሰጣል ።

### አንቀጽ ፳፫

### ቀድሞ ስለማለፍ ፤

፩/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ሌላውን ተሽከርካሪ ቀድሞ ለማለፍ ሲፈልግ በግራው በኩል ብቻ ማለፍ አለበት ።

www.chilot.me



፪/ ከፊት ለፊት ለሚመጣ ተሽከርካሪ ወይም ለሚቀድመው ተሽከርካሪ አደጋ ወይም እንቅፋት ሳያስከትል የመቅደሙን ተግባር ለመፈጸም በሚያስችል ርቀት ከፊት ለፊት የሚመጣ ተላላፊ አለመኖሩን ካላረጋገጠ በቀር ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ሌላውን ተሽከርካሪ ቀድሞ ማለፍ የለበትም ።

፫/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ፤

ሀ/ አርቆ ወይም አሻግሮ ለማየት ባልቻለበት ጊዜ ፤

ለ/ ከኮረብታ ጫፍ ወይም ከቁልቁለት ፤ ከድልድይ ፤ ተነድሎ ከተሠራ መሿለኪያ (ታነል) ወይም ከጉባጣ መንገድ ለመድረስ በተቃረበ ጊዜ ፤

ሐ/ ከመስቀልኛ ወይም ከሐዲድ በ፴ ሜትር ርቀት ውስጥ ሌላውን ተንቀሳቃሽ መኪና መቅደም አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፳፬

## ስለሚቀደሙ ተሽከርካሪዎች ፤

በሌላ ተሽከርካሪ የሚቀደም በመሄድ ላይ ያለ አንድ ተሽከርካሪ ነጂ ከመንገዱ ወደ ቀኝ መጠጋት አለበት ፤ እንዲሁም ቀዳሚው ተሽከርካሪ ጨርሶ አልፎት ከመሄዱና አደጋ በማያስከትል ርቀት ከመንገዱ ወደ ቀኝ ጥግ ከመመለሱ በፊት የነበረውን ፍጥነት መጨመር የለበትም ።

## አንቀጽ ፺፭

## አቅጣጫ ስለመለወጥ ፤

፩/ ወደ ግራ ስለመጠምዘዝ ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ፤

ሀ/ አርቆ ወይም አሻግሮ ለማየት ባልቻለበት ጊዜ ፤

ለ/ ከኮረብታ ጫፍ ወይም ከቁልቁለት ፤ ከድልድይ ወይም ተነድሎ ከተሠራ መሿለኪያ (ታነል) ወይም ከጉባጣ መንገድ ሲደርስ ፤

ሐ/ ከመስቀልኛ ወይም ከሐዲድ መንገድ ማቋረጫ በ፴ ሜትር ርቀት ውስጥ ወይም

መ/ የማያቋርጥ የቀለም መሥመር በተደረገበት መንገድ ላይ ፤ ወደ ግራ መጠምዘዝ አይፈቀድለትም ።

፪/ በትራፊክ ደሴት ዙሪያ ስለመንዳት ፤

በትራፊክ ደሴት ዙሪያ የሚነዳ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ የትራፊክን ደሴት ቀኙን ወገን ብቻ ተከትሎ መንዳት አለበት ።

፫/ በነጠላ መንገዶች ስለተከፋፈለ ጐዳና ፤

ሀ/ አንድ ጐዳና በነጠላ መንገዶች ተከፋፍሎ ሲገኝ ፤ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ በሌላው ተላላፊ ወይም በሚከተለው ተሽከርካሪ ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር ፤ ከአንዱ ነጠላ መንገድ ወደ ሌላው ለመሻገር አይፈቀድለትም ።

www.chilot.me



ለ/ አንድ ጐዳና በ፪ ወይም በ፫ ነጠላ መንገዶች ተከፋፍሎ ሲገኝ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ፤

፩/ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ ካልሆነ ፤

፪/ ሌላ ተሽከርካሪ ለመቅደም ካልሆነ ፤ ወይም

፫/ ነጠላውን መንገድ ተሽከርካሪው በሚሄድበት አቅጣጫ በአንድ አቅጣጫ ትራፊክ ብቻ የተመደበ ካልሆነ በተቀር ፤ ከመካከለኛው ነጠላ መንገድ ውስጥ ገብቶ እንዲነዳ አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፳፯

## ስለመጠምዘዝና ወደ ኋላ ስለመንዳት ፤

፩/ ስለመጠምዘዝና አቅጣጫ ስለመለወጥ ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ በሌላ ተሳፋሪና በሚከተሉት ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር በሚሄድበት አቅጣጫ ተሽከርካሪውን ወደሌላ መንገድ ለመጠምዘዝ ወይም የሚሄድበትን አቅጣጫ በማንኛውም አኳኋን ለመለወጥ ወይም የቆመ ተሽከርካሪውን ሲያስነሳ የነበረበትን አቅጣጫ ለመለወጥ አይፈቀድለትም ።

፪/ ወደ ቀኝ ስለ መጠምዘዝ ፤

ወደ ቀኝ የሚጠመዘዝ የተሽከርካሪ ነጂ በተቻለ መጠን የመንገዱን ቀኝ ጐን ተጠግቶ መጠምዘዝ አለበት ። ይህንንም ለማድረግ የሚችለው በቀኝ በኩል የሚጓዝ ሌላ ተሽከርካሪ የሌለ እንደሆነ ነው ።

፫/ ወደ ግራ ስለመጠምዘዝ ፤

ወደግራ የሚጠመዘዝ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ከማንባር የሚመጣ ተሽከርካሪ ከሌለ ተሽከርካሪውን ወደ ጐዳናው ማሀል ነድቶ ለመጠምዘዝ ይችላል ።

፬/ ወደኋላ ስለመንዳት ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ወደኋላ ለመንዳት ግድ አስፈላጊ ከሆነና ከአስፈላጊነቱ መጠን ሳይተላለፍ በሕይወትና በንብረት ላይ አደጋ እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ በማንኛውም መንገድ ላይ ወደ ኋላ መንዳት ይፈቀድለታል ።

## አንቀጽ ፳፰

## ስለሐዲድ ማቋረጥ ፤

፩/ በዝግታ ስለመንዳት ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ በሐዲድ ማቋረጫ ሲደርስ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ ለማቆም እንዲችል ተሽከርካሪውን በዝግታ መንዳትና ማቋረጫውንም ያለችግር ለማለፍ እንዲችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ መፈጸም አለበት ።

www.chilot.me



፪/ <u>ተሽከርካሪውን ስለማቆም ፤</u>

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ከባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ሲደርስ ፤

ሀ/ ባቡር የተቃረበ መሆኑን ለማስጠንቀቅ በዘበኛ ወይም በሜካኒክ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ ፤

ለ/ በማቋረጫው ላይ ያለው በር በሚከፈትበት ወይም በሚዘጋበት ጊዜ ፤

ሐ/ መጪ ባቡር በሚታይበት ፤ በሚሰማበት ወይም በማናቸውም አኳኋን መቃረቡ በሚታወቅበት ጊዜ ፤ ከሚቀርበው ሐዲድ ከስድስት (፮) ሜትር በማያንስ ርቀት ተሽከርካሪውን አቁሞ ፤ የሐዲድ በሮች ካልተከፈቱ ፤ ወይም በር የሌለ እንደሆነ ባቡሩ ካላለፈ በቀር ጉዞውን መቀጠል የለበትም ።

፫/ <u>ስለባቡር ሐዲድ በሮች ፤</u>

ማናቸውም ሰው በሐዲድ ማቋረጫ ላይ ያለው በር በመዘጋት ወይም በመከፈት ላይ ሳለ ወይም ከተዘጋ በኋላ በበሩ ላይ በሥሩ ወይም በሩን ዙሮ እንዲያልፍ አይፈቀድለትም ።

፬/ <u>አውቶቡስንና አደገኛ ዕቃዎችን የጫኑ ተሽከርካሪዎችን ስለማቆም ፤</u>

ሀ/ የአውቶቡስ ወይም ፈንጂ ነገሮች ወይም ተቀጣጣይ ነገሮችን የጫነ ወይም ከስምንት (፰) መንገደኞች በላይ የጫነ ተሽከርካሪ ነጂ ከባቡር ሐዲድ ማቋረጫ በደረሰ ጊዜ ከቅርቡ ሐዲድ ከስድስት (፮) ሜትር በማያንስ ርቀት ተሽከርካሪውን አቁሞ መጪው ባቡር አለመቃረቡን የሚያስጠነቅቅ ምልክት አለመሰጠቱን ለማረጋገጥ የሐዲዱን ግራና ቀኝ አቅጣጫ ከተመለከተና ካዳመጠ በኋላ ለሌላው መጪ ባቡር አደጋ የማያስከትል መሆኑን አረጋግጦ ጉዞውን መቀጠል ይችላል ።

ለ/ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር (ሀ) የተጻፈው በማዘጋጃ ቤት ክልል ለሚገኙ የሐዲድ ማቋረጫዎች አይጸናም ።

፭/ <u>ማርሽ መለወጥ ስለሚከለከልበት ሁኔታ ፤</u>

ሀ/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ከአንድ የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ በደረሰ ጊዜ ከቅርቡ ሐዲድ ለመድረስ በሚቀረው ስድስት (፮) ሜትር ርቀትና የሐዲዱን ማቋረጫ ተሻግሮ ባለው ስድስት (፮) ሜትር ርቀት መካከል ሲነዳ ማርሽ ሳይለውጥ የሐዲዱን ማቋረጫ ለማለፍ እንዲችል ከቅርቡ ሐዲድ ከስድስት (፮) ሜትር ርቀት ላይ ከመድረሱ በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ መፈጸም አለበት ።

ለ/ ማናቸውም የሞተር ተሽከርካሪ ነጂ ተሽከርካሪው ከባቡር ሐዲድ ማቋረጫ በስድስት (፮) ሜትር ውስጥ ባለበት ጊዜ ማርሽ መለወጥ አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፳፫

## <u>ምልክቶች ፤</u>

፩/ <u>ከመጠምዘዝ ፤ ፍጥነትን ከመቀነስ ፤ ወይም ከማቆም በፊት የሚሰጡ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ፤</u>

ሀ/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ምልክት ለመስጠት የማይችልበት በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር ከመጠምዘዝ ፤ አቅጣጫ ከመለወጥ ወይም ፍጥነት ከመቀነስ ወይም ከማቆም አስቀድሞ የሚገባውን የማስጠንቀቂያ ምልክት መስጠት አለበት ።

www.chilot.me



ለ/ ምልክቱ በቅርብ ላሉትና ለሚከተሉትም ተሳፋሪዎች ጉልህ ሆኖ እንዲሚታይና ሊታወቅ እንደሚቻል ሆኖ ካልተሰጠ በስተቀር እንዳልተሰጠ ይቆጠራል ።

ሐ/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ሌሎች ተሳፋሪዎች ምልክቱን አውቀው እንዲጠነቀቁ ቀደም ብሎ በሚበቃ ርቀት ላይ የማስጠንቀቂያ ምልክት መስጠት አለበት ።

፪/ የምልክት መስጫዎች ፤

ሀ/ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር (፩) የተጠቀሱት የማስጠንቀቂያ ምልክቶች የሚሰጡት በሜካኒክ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል በሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች ነው ። እነዚህ መሣሪያዎች የተበላሹ ወይም በመካኒክ ጉድለት ምክንያት ለመሥራት ባልቻሉ ጊዜ ፤ ነጂው የማስጠንቀቂያ ምልክት በእጅ መስጠት አለበት ።

ለ/ የማስጠንቀቂያ መሣሪያዎች በሚገባ መሥራታቸውን መቆጣጠር የነጂው ኃላፊነት ስለሆነ ፤ የእነዚህ መሣሪያዎች የመካኒክ ጉድለት ነጂው ተገቢውን የማስጠንቀቂያ ምልክት ባለመስጠቱ ለሚያደርገው ጥፋት መከላከያው ሊሆን አይችልም ።

፫/ የምልክቶች ትርጉም ፤

ሀ/ በመካኒክ ወይም በኤሌክትሪክ መሣሪያዎች የማስጠንቀቂያ ምልክት ሲሰጥ ፤

፩/ ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝ ወይም አቅጣጫ ለመለወጥ ነጂው በተሽከርካሪው ቀኝ ወገን ብርሃን ያለው ቀስት ወይም አመልካች ያሳያል ፤ ወይም ከተሽከርካሪው ኋላ በቀኝ ወገን የማያቋርጥ ቀይ ወይም ብጫ መብራትና በተሽከርካሪው ግን ባር በቀኝ ወገን የማያቋርጥ ነጭ ወይም ቢጫ መብራት ያሳያል ።

፪/ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ ወይም አቅጣጫ ለመለወጥ ነጂው በተሽከርካሪው ግራ ወገን ብርሃን ያለው ቀስት ወይም አመልካች ያሳያል ። ወይም ከተሽከርካሪው ኋላ በግራ ወገን የማያቋርጥ ቀይ ወይም ብጫ መብራትና በተሽከርካሪው ግንባር በግራ ወገን የማያቋርጥ ነጭ ወይም ብጫ መብራት ያሳያል ።

፫/ የተሽከርካሪውን ፍጥነት ለመቀነስ ወይም ለማቆም ፤ የተሽከርካሪው ነጂ ከተሽከርካሪው ኋላ ካሉት መብራቶች ቢያንስ አንዱን ቀይ መብራት ማሳየት አለበት ።

ለ/ መሪው በቀኝ በኩል ለሆነ ተሽከርካሪ በእጅ ስለሚሰጥ የማስጠንቀቂያ ምልክት ፤

፩/ ወደ ቀኝ በሚጠመዘዝበት ጊዜ ነጂው የቀኝ ክንዱን ወደውጭ አግድም ዘርግቶ የእጁን መዳፍ ወደታች በመክፈት ያመለክታል ።

፪/ ወደ ግራ በሚጠመዘዝበት ወይም አቅጣጫ በሚለውጥበት ጊዜ ነጂው የቀኝ ክንዱን አውጥቶ ከቀኝ ወደ ግራ በማዞር ያሳያል ።

፫/ በዝግታ ለመሄድ ወይም ለማቆም በሚፈልግበት ጊዜ ፤ ነጂው የቀኝ እጁን አውጥቶና ዘርግቶ ከፍና ዝቅ በማድረግ የጁን መዳፍ ወደታች አድርጎ ያሳያል ።

ሐ/ መሪው በግራ በኩል ለሆነ ተሽከርካሪ በእጅ ስለሚሰጥ የማስጠንቀቂያ ምልክት ፤

፩/ ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝ ወይም አቅጣጫን ለመለወጥ በፈለገ ጊዜ ነጂው የግራ ክንዱን ከግራ ወደ ቀኝ በማዞር ያመለክታል ።

፪/ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ በፈለገ ጊዜ ፤ ነጂው የግራ ክንዱን ወደ ውጭ አግድሞሽ በመዘርጋት መዳፉን ወደታች አድርጎ ያመለክታል ።

www.chilot.me



፫/ በዝግታ ለመንዳት ወይም ለማቆም በሚፈለግበት ጊዜ ፤ ነጂው የግራ ክንዱን ከፍና ዝቅ እያደረገ መዳፉን ወደታች በማድረግ ያሳያል ።

መ/ ምልክትን አይቶ ስለመፈጸም ፤

ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር ፫ እንደተመለከተው ፤ ከፊት ለፊት በሚሄድ የተሽከርካሪ ነጂ ምልክት የተሰጠው ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ፤ የተሽከርካሪውን ፍጥነት መቀነስ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማቆምና ምልክት ሰጪው ነጂ ያላንዳች እንቅፋት ለመጠምዘዝ ፤ አቅጣጫውን ለመለወጥ ፤ ፍጥነትን ለመቀነስ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ተሽከርካሪውን ለማቆም እንዲችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ መፈጸም አለበት ።

## አንቀጽ ፷፱

## የማስጠንቀቂያ ድምፅ መሣሪያዎች ፤

በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ አኳኋን በተለይ ካልታዘዘና በቦርዱ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሥልጣን በሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር ፤ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ በፉጨት ፤ በፊሽካ ፤ ወይም በደወል ፤ ወይም ከጭስ መውጫ ጋር በተያያዘ መሣሪያ ወይም በሕግ ባልተፈቀደ በሌላ በማናቸውም መሣሪያ የማስጠንቀቂያ ድምፅ እንዳይሰጥ ክልክል ነው ።

## አንቀጽ ፸

## በማስጠንቀቂያ ድምፅ ስለመጠቀም ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ የሚገጥመውን አደጋ ለመከላከል ግድ አስፈላጊ ካልሆነ ፤ አደጋውን የሚከላከልበት ሌላ መንገድ ከሌለውና የሚያሰማውም የማስጠንቀቂያ ድምፅ በተቻለ መጠን አጭር ካልሆነ በስተቀር ፤ በከተማ መንገድ ውስጥ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ማሰማት አይፈቀድለትም ። ተሽከርካሪው በቆመበት ጊዜ ፤ በማናቸውም አኳኋን የማስጠንቀቂያ ድምፅ ማሰማት ክልክል ነው ።

## ፩ኛ/ ክፍል ፤ ቅድሚያ ስለመስጠት ፤

## አንቀጽ ፸፩

## ከመስቀልኛ መንገዶች ስለመድረስና ስለመግባት ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ከአንድ መስቀልኛ መንገድ በደረሰ ጊዜ መስቀልኛውን መንገድ ለማለፍ አስቀድሞ ከመስቀልኛው መንገድ ውስጥ ለገባ ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት ። ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበዙ ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ከመስቀልኛው መንገድ የደረሱ እንደሆነ ማናቸውም ነጂ ከቀኝ በኩል ለተቃረበው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት ። በአንድ መስቀልኛ መንገድ ላይ የትራፊክ ክብ ተሠርቶ እንደሆነ ፤ ወደ ክቡ የተቃረበው ተሽከርካሪ ነጂ አስቀድሞ ክቡን በመዞር ላይ ላሉት ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለበት ።

## አንቀጽ ፸፪

## በመስቀልኛ መንገድ ላይ ወደ ግራ ስለመጠምዘዝ ፤

ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ከመስቀልኛ መንገድ ውስጥ ከገባ በኋላ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ የፈለገ እንደሆነ ፤ የግጭት አደጋ እንዳያስከትል በቂ በሆነ ርቀት ላይ አቁሞ ከፊት ለፊቱ ለተቃረበው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፴፫

## ቅድሚያ ወደሚሰጥበት ጐዳና ውስጥ ስለመግባት ፤

፩/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ቅድሚያ እሚሰጥበት መንገድ ጋር ከተያያዘ መስቀልኛ መንገድ በተቃረበ ጊዜ የማለፍ ቅድሚያ ምልክት ከተደረገበት መንገድ ከሁለቱ አቅጣጫ ወደ መስቀልኛው መንገድ ለተቃረበ ማናቸውም ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት ።

፪/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ከፊት ለፊቱ ቁም የሚል ምልክት ከተደረገበት መስቀልኛ መንገድ በደረሰ ጊዜ ፤ ተሽከርካሪውን በማቆሚያው መሥመር ወይም በእግረኛ ማቋረጫ ወይም አቋራጩን መንገድ አሻግሮ ለማየት በሚያስችለው ቅርብ ሥፍራ ላይ አቁሞ ከአቋራጭ መንገድ ለተቃረበው ማናቸውም ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት ።

## አንቀጽ ፴፬

## ከግል መንገድ ወደ ዋና ጐዳና ስለመግባት ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ከግል መንገድ ፡ ከአጥር ግቢ ወይም ከቤት መውጫ ወይም ከሌላ ቀጭን መንገድ ወጥቶ ወደ ዋና ጐዳና ለመግባት በፈለገ ጊዜ ፤ የእግረኞችን መሄጃ ወይም የመንገዱን ጠርዝ ከመሻገሩ በፊት ለእግረኞችና በዋናው ጐዳና ለማለፍ ለተቃረቡት ተሽከርካሪዎች ሁሉ ቅድሚያ መስጠት አለበት ።

## አንቀጽ ፴፭

## ከእግረኞች ማቋረጫ መንገድ ላይ ስለመቃረብ ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ከእግረኞች ማቋረጫ መንገድ ላይ በተቃረበ ጊዜ ፤ የተሽከርካሪውን ፍጥነት መቀነስና እግረኞቹ መንገዱን ጨርሰው እስኪሻገሩ ድረስ ተሽከርካሪውን ማቆም አለበት ። በዚህ በ፴፭ኛው አንቀጽ ስለተጻፈው «መንገድ» ማለት ተሽከርካሪው ከሚሄድበት አቅጣጫ ለትራፊክ የተመደበ የመንገድ ክፍል ነው ።

## አንቀጽ ፴፮

## ስለአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ፤

፩/ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ በተቃረበ ወይም በደረሰ ጊዜ ፤ ተሽከርካሪው በተቃረበበት ወይም በሚያልፍበት መንገድ ላይ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ከዚህ የሚከተለውን መፈጸም አለባቸው ።

ሀ/ ተሽከርካሪዎችን የሚነዱና ከብቶችን የሚጠብቁ ሁሉ ተሽከርካሪዎቻቸውን ፤ ወይም ከብቶቻቸውን ወዲያውኑ በፍጥነት ከመንገዱ ወደ ቀኝ ጠርዝ መንዳትና አደጋ በማያደርስ እርቀት ላይ የአደጋው አገልግሎት ተሽከርካሪው እስኪያልፍ ድረስ ማቆም አለባቸው ።

ለ/ በመንገዱ ላይ የሚገኙ እግረኞች ጐዳናውን በፍጥነት መልቀቅ አለባቸው ።

፪/ ተሽከርካሪው የአደጋ አገልግሎት ካልሆነ በቀር ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ወይም ተሳፋሪው ከተሽከርካሪው ላይ ቀይ ወይም ሰማያዊ ብርሃን እንዲያሳይ ወይም በፉጨትም ሆነ በደወል የማስጠንቀቂያ ምልክት እንዲሰጥ አይፈቀድለትም ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፴፯

## ስለአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች የተሰጠ ልዩ ደንብ ፤

፩/ ማናቸውም የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ ነጂ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ፤

ሀ/ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ደንብ የተጻፈውን ግዴታ ሳይጠብቅ ተሽከርካሪውን ለማቆም ፤

ለ/ አደጋ እንዳይደርስ በሚበቃ አኳኋን የተሽከርካሪውን ፍጥነት ቀንሶ ቁም በሚል ምልክት ላይ ሳይቆም ለማለፍ ፤

ሐ/ ከተወሰነው ፍጥነት በላይ ለመንዳት ፤

መ/ ተግባሩን ለመፈጸም በሚያስፈልገው መጠን ስለትራፊክ የወጡትን ደንቦችና ምልክቶች ሳይመለከት በፈቀደው አቅጣጫ ለመጠምዘዝ ተፈቅዶለታል ።

፪/ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር (፩) የተመለከተው እንዳለ ተጠብቆ ማናቸውም የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ ነጂ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲ በተራ ቁጥር ፳ የተጻፈውን ደንብ መፈጸም አለበት ።

፫/ ቀድሞ የሚሄደው የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ በሚፈጽመው ተግባር ተካፋይ የሆነ የሌላ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ ነጂ ካልሆነ በቀር ማናቸውም ሰው ከአንድ መቶ (፻) ሜትር ባነሰ ርቀት ከአንድ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ ኋላ ተጠግቶ እንዳይነዳ ክልክል ነው ።

## ፲ኛ/ ክፍል ፤ ስለተሽከርካሪ መቆሚያ ሥፍራ

## አንቀጽ ፴፰

## ተሽከርካሪ እንዳይቆም ስለሚከለከልበት ሁኔታ ፤

፩/ ከከተማ ክልል ውጭ በሆነ በማንኛቸውም መንገድ ላይ ተሽከርካሪ የሚነዳ ማናቸውም ሰው ከመንገዱ ላይ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ከሌላ በስተቀር ፤ ከመኪናው ቢወርድም ባይወርድም ትራፊክ በብዛት በሚተላለፍበት ጐዳና ላይ ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ ተሽከርካሪውን እንዲያቆም አይፈቀድም ።

፪/ ማናቸውም ሰው የመንገዱ ስፋት ከ፲፪ ሜትር በላይ ካልሆነ በቀር ፤ ተሽከርካሪውን ከሌላው ተሽከርካሪ አንጻር ከመንገድ ላይ ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም አይፈቀድም ።

፫/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ በዚያው መንገድ የሚነዳ ሌላ ተሽከርካሪ ነጂ ከሁለቱም አቅጣጫ ከ፶ ሜትር ርቀት ላይ ለማየት በማይችልበት ሥፍራ ከመንገድ ላይ ተሽከርካሪውን ማቆም አይፈቀድለትም ።

፬/ ይህ ፴፰ኛው አንቀጽ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፫ ለተጻፈው አይጸናም ።

## አንቀጽ ፴፱

## ስለ መሰናከል ፤

ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ፤

፩/ ሌላውን ተላላፊ በሚያሰናክል ወይም በሚከለክል ፤

www.chilot.me



፪/ ሌሎች ተሳላፊዎች የመንገዱን ምልክት በግልጽ ለማየት በማያስችላቸው ሁኔታ ተሽከር ካሪውን ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም ክልክል ነው ።

## አንቀጽ ፵

## ተሽከርካሪውን ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም የተከለከለባቸው ሥፍራዎች

ማናቸውም ሰው ከሌላው ትራፊክ ጋር እንዳይጋጭ ለመከላከል ወይም ማናቸውንም ሌላ ደንብ ለመፈጸም ካልሆነ በቀር ፤ ከዚህ ቀጥሎ በተዘራዘሩት ሥፍራዎች ተሽከርካሪ ውን በሙሉ ወይም በከፊል ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም አይፈቀድም ፤

፩/ መንገዱ ባለአንድ አቅጣጫ ካልሆነ በስተቀር ፤ በማንኛውም ጕዳና በስተግራ ወገን ፤

፪/ በእግረኛ መሄጃ ላይ ፤

፫/ በመስቀልኛ መንገድ ውስጥ ወይም ከመስቀልኛ መንገድ በአሥራ ሁለት (፲፪) ሜትር ውስጥ ፤

፬/ በግል መንገድ ፤ ተሽከርካሪዎች በሚተላለፉበት የቤት መውጫ ወይም መግቢያ ወይም የመንገድ ስፋት ከ፲፪ ሜትር ያነሰ ሆኖ ሲገኝ ፤

፭/ የጕርፍ ማስተላለፊያ ፉካ ካለበት በአምስት (፭) ሜትር ውስጥ ፤

፮/ በእግረኛ ማቋረጫ ውስጥ ወይም ከእግረኛ ማቋረጫ በአሥራ ሁለት (፲፪) ሜትር ውስጥ ፤

፯/ ቁም የሚል ምልክት ወይም የመንገድ ምልክት ካለበት ሥፍራ በ፲፪ ሜትር ውስጥ ፤

፰/ በሐዲድ መንገድ ማቋረጫ ከሚቀርበው ሐዲድ በሃያ (፳) ሜትር ውስጥ ፤

፱/ ከእሳት አደጋ ጣቢያ ወይም የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ከሚሰጥበት ጣቢያ ወይም ሆስፒታል መግቢያ በአሥራ ሁለት (፲፪) ሜትር ውስጥ ወይም ከመግቢያው መካከል ጀምሮ ከመንገዱ ግራና ቀኝ በሃያ አምስት (፳፭) ሜትር ውስጥ ፤ ይሁን እንጂ በሽተኛ ወይም የተጐዳ ሰው ወይም የአደጋ መከላከያ መሣሪያ ይዘው ከዚሁ ከተጠቀሱት ጣቢ ያዎች የሚወጡ ወይም የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በእነዚህ ሥፍራዎች ሊቆሙ ይችላሉ ።

፲/ በመንገድ ጥግ ቆሞ ከሚገኝ ሌላ ተሽከርካሪ ጋር ተደርቦ ፤

፲፩/ በድልድይ ወይም በመሿለኪያ (ታኔል) ላይ ፤

፲፪/ ከአውቶቡስ ማቆሚያ በስተኋላና በስተፊት በ፲፭ ሜትር ውስጥ የመንገዱ ስፋት ከ፲፪ ሜትር በላይ ካልሆነ በቀር በየመንገዱ እንጻር ከአውቶቡስ ማቆሚያ በ፴ ሜትር ውስጥ ፤

፲፫/ በእያንዳንዱ አቅጣጫ ለትራፊክ አንድ ነጠላ መንገድ ብቻ ባለበትና መንገዱ በነጭ ቀለም በተከፋፈለበት ሥፍራ ።

## አንቀጽ ፵፩

## ተሽከርካሪን ስለማቆም ፤

፩/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ እርሱ በሌለበት ጊዜ ተሽከርካሪው ከቆመበት ሥፍራ እንዳ ይነሳ ወይም እንዳይንቀሳቀስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካላደረገ በቀር ፤ ተሽከርካሪውን በማን ኛውም መንገድ ላይ አቁሞ መሄድ ክልክል ነው ።

www.chilot.me



፪/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ነጂ ሞተሩን ሳያጠፋና ማስነሻውን ሳይቆልፍ ፤ የማስነሻውን ቁልፍ ሳያነሳና የእጅ ፍሬን ወይም ተሽከርካሪው ከቆመበት ሥፍራ እንዳይንቀሳቀስ የሚያደርገውን ሌላውንም መሣሪያ ሳያጠብቅ ተሽከርካሪውን ያላንዳች ጥንቃቄ ትቶ መሄድ ክልክል ነው ።

፫/ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነጂ ተሽከርካሪውን ከቁልቁለት መንገድ ላይ ባቆመ ጊዜ ፤ የተሽከርካሪው የፊት እግሮች ከመንገዱ በጣም ወደሚቀርበው ጠርዝ መመለስ አለበት ።

፬/ የድንጋይ ጠርዝ ባለበት መንገድ ላይ ተሽከርካሪውን ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚያቆም ማንኛቸውም ሰው ከድንጋይ ጠርዝ በጣም የሚቀርበውን የተሽከርካሪውን እግር ከ፴ ሳንቲ ሜትር እንዳይርቅ አድርጎ ከድንጋይ ጠርዝ በትይዩ መስመር ማቆም አለበት ። ሆኖም ሥራው የሚመለከተው ባለሥልጣን ተሽከርካሪው በማዕዘናዊ አቀዋም እንዲቆም ፈቅዶ ምልክት ባደረገበት ጉዳና ላይ ይህ ደንብ አይጸናም ።

## አንቀጽ ፺፪

## ፖሊስ ተሽከርካሪዎች እንዲነሱ ለማድረግ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ፤

፩/ ማናቸውም ፖሊስ ተሽከርካሪ እንዳይቆም ከተከለከለበት ጉዳና ላይ ተሽከርካሪ ቆሞ ባገኘ ጊዜ ተሽከርካሪውን ወዲያው እንዲያነሳ ነጂውን ወይም የተሽከርካሪውን ኃላፊ ሊያዝ ይችላል ።

፪/ ማናቸውም ፖሊስ ተላላፊዎችን የሚያሰናክሉ ነገሮችን ለማስቀረት አስፈላጊ መስሎ ሲታየው ተሽከርካሪውን በማናቸውም ሥፍራ እንዲያቆም ፤ ወይም ተሽከርካሪውን ካቆመበት ሥፍራ ወደ ሌላ እንዲያዛውር ማንኛውንም የተሽከርካሪ ነጂ ወይም የተሽከርካሪው ኃላፊ የሆነውን ማንኛቸውንም ሰው ለማዘዝ ይችላል ።

፫/ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር (፩) እና (፪) ስለተመለከተው የተሽከርካሪው ነጂ ወይም የተሽከርካሪው ኃላፊ የሆነው ሰው ከፖሊሱ የተሰጠውን ትእዛዝ ሳይፈጽም ቢቀር ወይም በዚያ ጊዜ በሥፍራው ባይገኝ ፤ ፖሊሱ ተሽከርካሪውን ለማስወገድ ወይም እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል ።

፬/ ማናቸውም ፖሊስ በዚህ በ፺፪ኛው አንቀጽ በተራ ቁጥር (፫) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አንድ ተሽከርካሪ ከቆመበት ሥፍራ እንዲነሳ በፈለገ ጊዜ ፤ የተባለውን ተሽከርካሪ ወደጋራዥ ወይም አደጋ ወደማያስጋበት ወደ ሌላ ሥፍራ ለማዛወር ይችላል ። ስለሆነም ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ስለተሽከርካሪው ደኅንነት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ።

፭/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፫ የተጻፈው በዚህ በ፺፪ኛው አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣን ይወስናል ።

፮/ በዚህ በ፺፪ኛው አንቀጽ በተጻፈው መሠረት ተሽከርካሪውን ለማዛወርና በደንብ ለመያዝ የሚያስፈልገውን ተገቢ ወጪ የተሽከርካሪው ባለቤት ይከፍላል ።

## ፲፫ኛ/ ክፍል ፤ የመንገደኛ ማመላለሻ

## አንቀጽ ፺፫

## ስለመሳፈርና መውረድ ፤

፩/ ማንኛውም ሰው ተሽከርካሪው ጨርሶ ሳይቆም ከተሽከርካሪው ላይ መውጣት ወይም መውረድ ክልክል ነው ።

www.chilot.me



፪/ በዚህ በ፵፮ኛው አንቀጽ በተራ ቁጥር (፩) የተጻፈው ነጂው በቀጠራቸው ሠራተኞች ወይም በረዳቶቹ ፣ ወይም ተሽከርካሪው የጫነው ዕቃ በሚመለከታቸው ሰዎች ላይ አይጸናም ። ይህም የሚፈቀደው ፣

ሀ/ እነዚህን መንገደኞች ያለአንዳች አደጋ ለማሳፈር ተሽከርካሪው የሚስማማና በቂ ዝግጅት ያለው እንደሆነ ፤

ለ/ ተሽከርካሪው አደጋ የማያስከትል መቀመጫ ያለው እንደሆነ ፤

ሐ/ መንገደኞች በዚሁ መቀመጫ ብቻ የሚቀመጡ እንደሆነ ፤

መ/ የመንገደኞቹ ቁጥር ከአራት (፬) የማይበልጥ እንደሆነ ነው ።

፫/ መብቱ የሚፈቅድለት ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ራሱ በሚወስነው ስምምነትና ግዴታ መሠረት በንግድ ተሽከርካሪዎች ላይ መንገደኛ ለማሳፈር ፈቃድ ቢሰጥ በዚህ አንቀጽ የተጻፈው አይከለክለውም ።

፬/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፵፮ የተጻፈው በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የጦር ኃይል ፣ ወይም የፖሊስ ሠራዊት ተሽከርካሪዎች ላይ አይጸናም ።

## ፰ኛ/ ክፍል ፤ ሸቀጦችን ስለማመላለስ

### አንቀጽ ፵፯

### የንግድ ሸቀጦች አጫጫን ፤

፩/ ማናቸውም ሰው ፤

ሀ/ የተሽከርካሪው አሠራር ዕቃዎችን ያለአንዳች አደጋ ለማሳፈር የሚስማማና በቂ ዝግጅት ከሌለው ፤

ለ/ ጭነቱ ከተሽከርካሪው ጐን ተርፎ የሚወጣ ከሆነ ፤

ሐ/ ጭነቱ ከተሽከርካሪው በስተፊት ባለው ጫፍ ከአንድ (፩) ሚትር በስተኋላ ከተሽከ ርካሪው ፣ ከተሳቢው ወይም ከግማሽ ተሳቢው ፣ አካል ከሁለት (፪) ሚትር ተርፎ የሚወጣ ከሆነና ፤

መ/ ጭነቱ ወይም መሸፈኛው ነጂው ወደፊት ፣ ወይም ወደጐን እንዳያይ የሚከለክል ፣ በሚነዳበትም ጊዜ የነጂውን እንቅስቃሴ የሚያሰናክል ወይም ወደነጂው መቀመጫ እንደልብ ለመግባት ወይም ለመውጣት የሚከለክል ከሆን ፤

በማናቸውም ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም በላዩ ማናቸውንም ሸቀጥ መጫን ወይም እንዲጫን ማድረግ ክልክል ነው ።

፪/ ሁለት (፪) ተሽከርካሪዎች ተቀጣጥለው በርዝመቱ ምክንያት በአንድ ተሽከርካሪ ብቻ ሊጫን የማይቻል ጭነት በአንድነት የሚጭኑ ሲሆን ፤ ሁለቱ ተሽከርካሪዎች በዚህ በ፵፯ ኛው አንቀጽ ውስጥ ስለተመለከተው እንደአንድ ተሽከርካሪ ይቆጠራሉ ።

፫/ የጠቅላይ ግዛቱ ፣ ወይም የአውራጃው ግዛት የፖሊስ አዛዥ ፣ ወይም እርሱ በሚገባ የወከለው ሰው በቂ ምክንያት ሲኖረውና ለአንድ ጊዜ ጉዞ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር (፩) በንዑስ ተራ ቁጥር (ለ) እና (ሐ) ከተወሰነው ልዩ በሆነ በሌላ ግዴታ ጭነት ለመጫን መፍቀድ ይችላል ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፺፰

### በተራፊው ጭነት ላይ ምልክት ስለማድረግ ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፺፯ በተራ ቁጥር (፩) በንዑስ ተራ ቁጥር (ለ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ተሽከርካሪ ጭነት ከተሽከርካሪው ግንባር ፤ ወይም ከኋላ ትርፍ ሲገኝ የተሽከርካሪው ነጂ በተራፊው ጭነት ላይ ፤

ሀ/ መብራት በሚበራበት ጊዜ በስተፊት ተርፎ በሚገኘው ጭነት ጫፍ ነጭ ፤ ወይም ብጫ ፤ ከኋላ ተርፎ በሚገኘው ጭነት ላይ ቀይ መብራት ፤

ለ/ መብራት በማያስፈልግበት ጊዜ በተራፊው ጭነት ላይ በፊትና በኋላው ቢያንስ ሠላሳ (፴) ሳንቲ ሜትር ካሬ የሆነ ቀይ ጨርቅ ወይም ቀይ ቀለም የተቀባ ጠፍ ጣፋ እንጨት ማድረግ አለበት ።

## አንቀጽ ፺፱

### ጭነትን በጥብቅ ማሠር ግዴታ ስለመሆኑ ፤

ማናቸውም ሰው ጭነቱንና መሸፈኛም ያለው እንደሆን እንዳይወድቅ ፤ ወይም እንዳይ ፈታ አድርጎ በጥብቅ ሳያስር በማናቸውም መንገድ ላይ ተሽከርካሪ እንዲነዳ አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፻

### በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ መኪና ላይ

### የሚደረግ ልዩ ቁጥጥር ፤

፩/ ማናቸውም ሰው በማንኛውም ወገን ከሊታፊው መሥመር በላይ የሆነ ጭነት ጭኖ የሕ ዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ መኪና በማናቸውም መንገድ ላይ እንዲነዳ አይፈቀድም ።

፪/ ማናቸውም ሰው ከተሽከርካሪው አካል ውጭ ወደፊት ወይም ወደኋላ የሚተርፍ ዕቃ ጭኖ በማናቸውም መንገድ ላይ እንዲነዳ አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፻፩

### አቧራ የሚያመጡ ነገሮችን ስለመጫን ፤

ማናቸውም ሰው በተሽከርካሪው መንቀሳቀስ ፤ ወይም በነፋስ ኃይል ምክንያት እንዳይበን ለመከላከል ጭነቱን በሚገባ ሳይሸፍን አሸዋ ፤ ወይም አፈር እንዳይጭን ክልክል ነው ።

## አንቀጽ ፻፪

### በመንገድ ላይ የፈሰሱትን ነገሮች መጥረግ

### ግዴታ ስለመሆኑ ፤

የተሽከርካሪው ጭነት በመንገድ ላይ የሚፈስ ሲሆን ፤ ወይም ፈሶ ቢገኝ ነጂው ተሽከርካ ሪውን አቁሞ ጭነቱ መፍሰሱን እንዳይቀጥል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካላደረገና አስቀ ድሞ እመንገድ ላይ የፈሰሰውን ካልጠረገ ፤ ወይም እንዲጠረግ ካላደረገ በቀር ጉዞውን መቀጠል አይችልም ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፶፫

### የፖሊስ ሥልጣን ፤

ማናቸውም ፖሊስ በዚህ ደንብ የተጻፈውን በመተላለፍ ዕቃ የጫነ ተሽከርካሪ ሲያገኝ ፤ የተጣሰው ደንብ እስኪፈጸም ድረስ ተሽከርካሪውን እንዲያቆምና ጉዞውን እንዳይቀጥል ነጂውን ለማዘዝ ይችላል ።

## ፱ኛ/ ክፍል ፤ ተሽከርካሪ ስለመጐተት ፤ ስለመጫወቻ ተሽከርካሪዎች

## አንቀጽ ፶፬

### ተሽከርካሪ ስለመጐተት ፤

፩/ አንድ ተሽከርካሪ በሌላ የሞተር ተሽከርካሪ በሚጐተትበት ጊዜ በመካከላቸው ያለው ርቀት ከሦስት (፫) ሜትር የማይበልጥ ሆኖ ሁለቱ ተሽከርካሪዎች በወፍራም ገመድ ፤ በሽቦ ገመድ ወይም በጠንካራ የመሳቢያ ብረት ዘንግ በጥብቅ መያያዝ አለባቸው ።

፪/ በገመዱ ፤ በሽቦው ወይም በመሳቢያው የብረት ዘንግ ላይ በጉልህ ሊታይ የሚችል ቀይ ቀለም የተቀባ ጨርቅ ወይም ሳንቃ ማድረግ ያስፈልጋል ።

፫/ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር አንድ (፩) እንደተመለከተው አንድ ተሽከርካሪ በሚጐተትበት ጊዜ ለሚከተለው ተሽከርካሪ ነጂ ግልጽ ሆኖ ሊታይ በሚቻልበት አኳኋንና ሥፍራ ላይ በሚጐተተው ተሽከርካሪ ኋላ ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል ።

፬/ ማናቸውም የሞተር ተሽከርካሪ በአንድ ጊዜ ከአንድ (፩) ተሽከርካሪ በላይ እንዲጐትት አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፶፭

### የመጫወቻ ተሽከርካሪዎች ፤

ማናቸውም ሰው ለመጫወቻና ለጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የተሠራ ቢስክሌት ፤ በተለይም የሕፃናት ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ክፍት በሆነ በማናቸውም መንገድ ላይ መንዳት ክልክል ነው ።

## ፲ኛ/ ክፍል ፤ ስለሞተር ቢስክሌትና ቢስክሌት

## አንቀጽ ፶፮

### ሞተር ቢስክሌት ስለመንዳት ፤

፩/ ማናቸውም ሰው ለነጂው ተብሎ በሞተር ቢስክሌት ላይ በተዘጋጀው ኮርቻ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ በማናቸውም መንገድ ላይ ሞተር ቢስክሌት መንዳት ክልክል ነው ።

፪/ ማናቸውም ሰው እግሮቹን ከሞተር ቢስክሌቱ በሁለቱም ጐን ላይ ሳያደርግ ሞተር ቢስክሌት መንዳት ክልክል ነው ።

፫/ ማናቸውም የሞተር ቢስክሌት ነጂ ፤ ከነጂው መቀመጫ ኋላ ለመፈናጠጫ በተዘጋጀው ኮርቻ ወይም መቀመጫ ወይም በስተጐን ባለው ተቀጣይ ተሽከርካሪ ካልሆነ በስተቀር በሞተር ቢስክሌቱ ላይ ማናቸውንም መንገደኛ ማሳፈር ክልክል ነው ።

፬/ ማናቸውም የሞተር ቢስክሌት ነጂ የሞተር ቢስክሌቱ ዝግጅትና መንገደኞቹን ለማጓጓዝ የተሰጠው ፈቃድ ከሚፈቅድለት በላይ መንገደኛ ማሳፈር ክልክል ነው ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፶፯

## ቢስክሌት ስለመንዳት ፤

፩/ ማናቸውም ሰው ቢስክሌት በመልካም ሁኔታና አሠራሩም ለመንገድ ተገቢ ካልሆነ በስተቀር ቢስክሌት መንዳት የለበትም ።

፪/ ማናቸውም ሰው ለነጂው ተብሎ በቢስክሌቱ ላይ በተዘጋጀው መቀመጫ ላይ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ ማናቸውንም ቢስክሌት መንዳት የለበትም ።

፫/ ማናቸውም ቢስክሌት ነጂ ቢስክሌቱን በሚነዳበት ጊዜ የቢስክሌቱን መሪ በእጆቹ ሳይዝ፤ በእግሮቹም የቢስክሌቱን ማሽከርከሪያ ሳይቆነጥጥ እንዲነዳ አይፈቀድም ።

፬/ ማናቸውም ሰው ቢስክሌት ሲነዳ ቢስክሌቱን በሙሉ ለመቆጣጠር የሚከለክል ማናቸውንም ጥቅል ፤ ጭነት ወይም ዕቃ መጫን የለበትም ። ቢጭንም የዕቃው ርዝመት ወይም ስፋት በማናቸውም አኳኋን ከሰባ (፸) ሳንቲ ሜትር መብለጥ የለበትም ።

፭/ ማናቸውም ሰው ቢስኪሌት በሚነዳበት ጊዜ፤በማናቸውም አኳኋን በመንገዝ ላይ ያለ ሌላ ተሽከርካሪ መያዝ ፤ ወይም ራሱ ወይም ቢስክሌቱ በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ወይም እንዲጐተት ማድረግ የለበትም ።

፮/ ማናቸውም ቢስክሌት ነጂ ቀድሞ ለመሄድ ካልሆነ በቀር በመንገዝ ላይ ካለ ተሽከርካሪ በግራ ወገን እየነዳ መሄድ ክልክል ነው ።

፯/ በመሠረቱ ቢስክሌት ነጂዎች ቅደም ተከተል መሥመርን ይዘው መንዳት አለባቸው ። ሆኖም ለሌላ ትራፊክ እንቅፋት የማይሆኑ ከሆኑ ሁለት (፪) ቢስክሌት ነጂዎች ብቻ ጐን ለጐን ሆነው ለመንዳት ይችላሉ ።

፰/ ማናቸውም ሰው የማስጠንቀቂያ ደወልና የተሟላ ፍሬን የሌለው ቢስክሌት እንዲነዳ አይፈቀድም ።

## ፲፩ኛ/ ክፍል ፡ ስለእንስሶች

## አንቀጽ ፶፰

## እንስሶችን በመንገድ ላይ ስለመንዳት ፤

፩/ ማናቸውም ሰው በሌላ ሥፍራ ለመንዳት ሲችል ፤ እንስሶችን በማናቸውም መንገድ ላይ መንዳት የለበትም ። ሌላ ሥፍራ ሳይኖር ቀርቶ በመንገድ ላይ መንዳት ግድ ቢሆንበትም ፤ ለትራፊክና በመንገዱ ለሚጠቀሙ ሁሉ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ።

፪/ ማናቸውም ሰው እንስሶችን በመንገድ ላይ ሲነዳ የመንገዱን ቀኝ ወገን ዳር ተከትሎ መንዳት አለበት ።

## አንቀጽ ፶፱

## እንስሶች ስለሚያጋጥሟቸው ተሽከርካሪዎች፤

አንድ የሞተር ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ እንስሶች በገጠሙት ጊዜ ፤ የእንስሶች ጠባቂ ለሞተር ተሽከርካሪ መንገድ ለመልቀቅ የሚቻለውን ሁሉ መፈጸም አለበት ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፹

### የእንስሶች ጠባቂ መብራት መያዝ ስለሚገባው ፤

በማብሪያ ጊዜ እንስሶችን በመንገድ ላይ የሚነዳ ማናቸውም ሰው ፤ በጉልህ የሚታይ መብራት መያዝና ለሚንዝው ተሽከርካሪ አቅራቢያ በሆነው ወገን መብራቱን ማሳየት አለበት ።

## ፲፪ኛ/ ክፍል ፤ ስለእግረኞች ፤

## አንቀጽ ፹፩

### ተሽከርካሪ በሚሄድበት መንገድ ወይም ጉዳና ላይ ስለመሄድ ፤

፩/ ማናቸውም ሰው ፤

ሀ/ የእግረኛ መሄጃ ከሌለ በስተቀር ፤

ለ/ መንገድ ወይም ጎዳና ለማቋረጥ ካልሆነ በስተቀር ፤ ተሽከርካሪ በሚተላለፍበት በማንኛውም መንገድ ላይ መሄድ አይፈቀድለትም ።

፪/ ማናቸውም ሰው ጉዳናውን ወይም መንገዱን ተከትሎ በሚሄድበት ጊዜ ፤ ከፊቱ የሚመ መጣውን ትራፊክ እየተመለከተ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መሄድ አለበት ።

## አንቀጽ ፹፪

### መንገድ ስለማቋረጥ ፤

፩/ ማንኛውም ሰው የትራፊኩን ብዛትና ሁኔታ አጣርቶ ሳይመረምር ፤ በራሱና በሌሎች ተላላፊዎች ጉዳት ሳይደርስ መንገዱን ለማቋረጥ የሚችል መሆኑን ሳያረጋግጥ መንገድ ማቋረጥ አይፈቀድለትም ።

፪/ ማናቸውም ሰው መንገድ ለማቋረጥ በፈለገ ጊዜ ፤ ተገቢውን ጥንቃቄና ፍጥነት በማድረግ ፤ እንዲሁም ያለ በቂ ምክንያት በመንገዱ ላይ ሳይቆም ፤ ወይም ሳይዘገይ ቀጥተኛና አጭር በሆነ መሥመር ማቋረጥ አለበት።

፫/ ማናቸውም ሰው መንገድ ለማቋረጥ በፈለገ ጊዜ ከአንድ መጪ ተሽከርካሪ ኋላ ወይም የአንድ መጪ ተሽከርካሪ ነጂ ሊያየው ከማይችልበት ከማንኛውም ሥፍራ ላይ መንገድ ማቋረጥ የለበትም ።

፬/ የእግረኛ ማቋረጫ ሲኖር ማናቸውም ሰው መንገድ ለማቋረጥ ሲፈልግ በዚሁ በእግረኛ ማቋረጫ ብቻ መጠቀም አለበት ።

፭/ ማናቸውም ሰው በማዘጋጃ ቤት መንገድ ለማቋረጥ ሲፈልግ በተቻለ መጠን በመስቀል ኛው መንገድ አጠገብ ካልሆነ በስተቀር ማቋረጥ የለበትም ።

፮/ ማናቸውም ሰው መስቀልኛን መንገድ በሰያፍ ማቋረጥ የለበትም ።

## አንቀጽ ፹፫

### በመንገድ ወይም በጐዳና ውስጥ ስለመቆም ፤

ማናቸውም ሰው ሕጋዊ ተግባሩን ለመፈጸም ካልሆነ በስተቀር ለመሳፈርም ሆነ ወይም ለሌላ ጉዳይ ተሽከርካሪ እንዲቆም ለማድረግ በማናቸውም መንገድ ውስጥ እንዳይቆም ክልክል ነው ።

www.chilot.me



### አንቀጽ ፷፬

**በአጥር በተከለሉ የእግረኛ መሂጃዎች ፤**

የእግረኛ መሂጃ በአጥር የተከለለ ሆኖ ሲገኝ ፤ ማናቸውም እግረኛ ከአጥሩ በመንገዱ በኩል መቆም ወይም መዘዋወር አይፈቀድለትም ።

### አንቀጽ ፷፭

**በእግረኛ መሂጃ ላይ ስለመቆም ፤**

ማናቸውም ሰው በእግረኛ መሂጃ ላይ ከመቆሙ ወይም ከመዘዋወሩ የተነሳ ተላላፊውን እግረኛ የሚያደናቅፍ የሚሆን ከሆነ በማናቸውም እግረኛ መሂጃ ላይ መቆም ወይም መዘዋወር አይፈቀድለትም ።

### አንቀጽ ፷፮

**በእጅ እየተገፉ ስለሚሽከረከሩ ጋሪዎች ፤**

በሞተር ከሚነዱ ባለመንኩራኩር ወንበሮች በስተቀር በእጅ እየተገፉ የሚሽከረከሩ የጥቃቅን ዕቃ መያገሪያዎች ፤ አካለ ጉዶሎዎች የሚጠቀሙባቸው ባለመንኩራኩር ወንበሮች ከመንገዱ የሚርቀውን የእግረኛ መሂጃ ክፍል ይዘው መሂድ አለባቸው ።

### አንቀጽ ፷፯

**የተለዩ ውሳኔዎች ፤**

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፷፫ እና ፷፭ የተጻፈው በስልፍ ወይም በሬሳ አጀብ ወይም ይህን በመሳሰለው ተካፋይ በሆኑት ላይ አይጸናም ።

## ፲፫ኛ/ ክፍል ፥ ስለመንገድ ምልክቶች

### አንቀጽ ፷፰

**በአንድ ዓይነት የመንገድ ምልክት ስለመጠቀም ፤**

ማናቸውም ሰው ፥ ወኪል ወይም የቀበሌ የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን ትራፊክን ለመቆጣጠር ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት የመንገዱ ምልክቶች ካልሆነ በቀር በሌላ የመንገድ ምልክት መጠቀም አይችልም ።

### አንቀጽ ፷፱

**ስለሥልጣን ፤**

የመንገድ ምልክት ባለሥልጣን ፤

፩/ የመንገድ ምልክቶች እንዲተከሉ የተተከሉበት ቦታ ተለይቶና ታውቆ ምልክቶቹ እንዲጠበቁ ፥ እንዲታደሱ ፥ እንዲጠገኑና ፤

፪/ አስቀድሞ የተተከሉ የመንገድ ምልክቶች እንዲነሱ ለማዘዝ ይችላል ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፸፱

## የማንባር መብራቶችን ኃይል ስለመቀነስ ፤

፩/ ማናቸውም የሞተር ተሽከርካሪ ነጂ ፤

ሀ/ ያለአደጋ ለመንዳት ፤ የመንገዱ መብራት በቂ ካልሆነ በስተቀር በከተማ መንገድ ላይ ሲነዳ ፤

ለ/ ከወደፊቱ ሌላ ተሽከርካሪ ሲቃረብና ተሽከርካሪውም እስኪያልፍ ድረስ ፤

ሐ/ ከአምሳ (፶) ሜትር በማያንስ ርቀት ሌላውን የሞተር ተሽከርካሪ በሚከተልበት ጊዜና ፤

መ/ ተሽከርካሪው በቆመበት ጊዜ ፤ የተሽከርካሪውን የማንባር መብራቶች መቀነስ አለበት ።

## ፲፭ኛ/ ክፍል ፤ ከአደጋ ስለመጠበቅ

## አንቀጽ ፹

## በቁልቁለት መንገድ ላይ ስለመንዳት ፤

፩/ ማናቸውም ሰው ሞተሩ እንዲሠራ ሳያደርግና ማርሽ ሳያገባ በማናቸውም መንገድ ላይ የሞተር ተሽከርካሪ እንዲነዳ አይፈቀድም ።

፪/ በቁልቁለት መንገድ የሞተር ተሽከርካሪ የሚነዳ ማናቸውም ሰው ለቁልቁለቱ ለተሽከር ካሪው ዓይነት አሠራርና ክብደት በሚስማማው አነስተኛ ማርሽ መጠቀም አለበት ።

## አንቀጽ ፹፩

## ተሽከርካሪን ስለማደስ ፤

በጐዳና ወይም በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ የሚጠግን ማናቸውም ሰው ፤ የመጠገኑን ሥራ የሚያከናውንበት ሌላ ዘዴ ከሌለ በስተቀር ፤ ተሽከርካሪው ካለበት ዙሪያ መሥመር ሰው ነቱን ወደ መንገድ አውጥቶ እንዲጠግን አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፹፪

## ነዳጅን ስለመሙላት ፤

፩/ ማናቸውም ሰው የተሽከርካሪው ሞተር እየሠራና የሞተር ተሽከርካሪውም የሕዝብ ማመላለሻ እንደሆነ ፤ በተሽከርካሪው ውስጥ መንገደኞች እያሉ ማናቸውም ነዳጅ እንዲሞላ ወይም እንዲያስሞላ አይፈቀድም ።

፪/ በተሽከርካሪው አጠገብ እሳት ወይም ሲጋራ የሚያጨስ ሰው ሲኖር ማናቸውም ሰው በሞተር ተሽከርካሪው ፤ ነዳጅን እንዲሞላ ወይም የነዳጁን ጋን መክደኛ እንዲከፍት ወይም ሌላው ሰው ይህን እንዲያደርግ መፍቀድ ክልክል ነው ።

## ፲፮ኛ/ ክፍል ፤ ስለአደጋ

## አንቀጽ ፹፫

## አደጋ በሆነ ጊዜ ስለሚፈጸም ተግባር ፤

የመንገድ አደጋ ሆኖ በአደጋው ምክንያት ሰው የሞተ ወይም የተጐዳ እንደሆነ ፤ ወይም በንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ደንቦች ይፈጸማሉ ።

www.chilot.me




መጀመሪያ ወደ ግራ ቀጥሎ ወደ ቀኝ የሚታጠፍ መንገድ ፤


መጀመሪያ ወደ ቀኝ ቀጥሎ ወደ ግራ የሚታጠፍ መንገድ ፤


እየጠበበ የሚሄድ መንገድ ፤


ጠባብ ድልድይ ፤


በመንገዱ ላይ ሠራተኞች አሉ ፤


ባለአራት አቅጣጫ መስቀልኛ መንገድ ፤


መስቀልኛ መንገድ በቀጥታና ወደ ግራ ፤


መስቀልኛ መንገድ ፤ በቀጥታና ወደ ቀኝ ፤


መስቀልኛ መንገድ ፤ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ወደፊት ቀጥታ መንገድ የለም ፤


በማቋረጫ መንገድ ላይ ለትራፊክ ቅድሚያ መስጠት ፤


መዝጊያ ያለው የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ፤


መዝጊያ የሌለው የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ፤

የተደጋገመ የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ማስጠንቀቂያ ፤



ሀ ለ ሐ ሐ ለ ሀ

ሀ/ ወደፊት ፪፻፵ ሜትር ርቀ የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ መኖሩን የሚያመለክት፤
ለ/ ወደፊት ፻፷ ሜትር ርቀ የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ መኖሩን የሚያመለክት፤
ሐ/ ወደፊት ፹ ሜትር ርቀ የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ መኖሩን የሚያመለክት፤

www.chilot.me





የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ፤



አደገኛ ቁልቁለት ፤



የእግረኛ ማቋረጫ ፤



ማስጠንቀቂያ ፣ ስለሕፃናት ፤



በአንድ አቅጣጫ መንገድ ላይ ለጊዜው ትራፊክ በሁለት አቅጣጫ እንዲ ሄድበት የተፈቀደ ፤



የሚያንሸራትት መንገድ ፤



አደጋ ፤

## ፪/ የሚከለከሉ ምልክቶች ፤



በእጅ ለሚገፉት ቁምር ለማንኛውም ተሽከርካሪ የተከለከለ ፤



የተከለከለ አቅጣጫ ፤



ቀስቱ በሚያመለክተው አንጻር መታጠፍ የተከለከለ ፤



ከሁለት እግር በላይ ያላቸውን የሞተር ተሽከርካሪዎች ቀድሞ ማለፍ የተከለ ከለ ፤



ከሁለት እግር በላይ ላላቸው የሞተር ተሽከርካሪዎች የተከለከለ ፤



ለሞተር ቢስክሌት የተከለከለ ፤

www.chilot.me




ለባለሞተር ተሽከርካሪዎች የተከለከለ ።


ጠቅላላ ክብደቱ በምልክቱ ላይ ከተመለከተው በላይ ለሆነ የንግድ ተሽከርካሪ የተከለከለ ።



ጠቅላላ ክብደቱ በምልክቱ ላይ ከተመለከተው በላይ ለሆነ ተሽከርካሪ የተከለከለ ።


ለቢስክሌት የተከለከለ ።


በእንስሳ ለሚሳቡ ተሽከርካሪዎችና ለእንስሶች የተከለከለ ።


በእጅ ለሚገፉ ተሽከርካሪዎች የተከለከለ ።


ለእግረኞች የተከለከለ ።


የአክሲሉ ጭነት በምልክቱ ላይ ከተመለከተው ጭነት በላይ ለሆነ ተሽከርካሪ የተከለከለ ።


ጠቅላላ ስፋቱ በሜትር ፣ በምልክቱ ላይ ከተመለከተው በላይ ለሆነ ተሽከርካሪ የተከለከለ ።


ጠቅላላ ከፍታቸው በሜትር በምልክቱ ላይ ከተመለከተው በላይ ለሆነ ተሽከርካሪ የተከለከለ ።



ፍጥነት የተወሰነበት ክልል ፣ በኪሎ ሜትር በምልክቱ ላይ ከተመለከተው ፍጥነት በላይ የተከለከለ ።


የከተማ ክልል ።


ፍጥነት የተወሰነበት ክልል መጨረሻ ፣ ወይም የከተማ ክልል መጨረሻ ።

www.chilot.me





ምልክቱ እንደሚያመለክተው እግድ የተደረገበት ክልል መጨረሻ ፤



የጥሩንባ ድምፅ ማሰማት የተከለከለበት ፤



ቁም ፤ ይህ ምልክት ባለበት ማናቸውም ተሽከርካሪ ከመስቀልኛው መንገድ ከመግባቱ በፊት መቆም አለበት ።



ይህ ምልክት ካለበት ጀምሮ እስከሚቀጥለው መስቀልኛ መንገድ ፤ ወይም «መጨረሻ» ከሚል ቃል ጋር ቀጥሎ የሚገኝ የዚህ ዓይነት ምልክት እስካለበት ድረስ በመዘግየት ለማቆም የተከለከለ ፤



ይህ ምልክት ካለበት ጀምሮ እስከሚቀጥለው መስቀልኛ መንገድ ፤ ወይም «መጨረሻ» ከሚል ቃል ጋር ቀጥሎ የሚገኝ የዚህ ዓይነት ምልክት እስካ ለበት ድረስ ለማቆም ያልተፈቀደ ፤



ከወደፊት ለሚመጣ ተሽከርካሪ ቅድሚያ ስጥ ፤



ቁም ፤ የጉምሩክ መሥሪያ ቤት ፤



ምልክቱ ያለበትን ቦታ ቀኙን እለፍ ፤



ምልክቱ ያለበትን ቦታ ግራውን እለፍ ፤



ቀስቱ በሚያመለክተው አቅጣጫ እለፍ ፤



የትራፊኩን ክብ አስቀድሞ በመዞር ላይ ላለ ተሽከርካሪ ቅድሚያ ሰጥተህ ቀስቱ እንደሚያመለክተው የትራፊኩን ክብ ዞር ፤

## ፫/ በመንገድ ላይ የሚደረጉ ምልክቶች



ምልክቶችን አስቀድሞ ማመዛዘን ነጂዎች ተሽከርካሪዎቻቸውን ከመስቀልኛ መንገድ ከመግባታቸው በፊት የሚሄዱበትን አቅጣጫ የሚያሳይ የቀስት ምልክት ባለበት ነጣላ መንገድ ላይ ያቆማሉ ፤

www.chilot.me





የማቆሚያ ምልክቶች ፤ ከምልክቱ ውስጥ ሳይተላለፉ ማቆም ይፈቀዳል ።



የመስቀልኛ መንገድ ማስተላለፊያ ምልክቶች ፤ ወደቀኝ የሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች የመስመሩን ቀኝ ይይዛሉ ። በቀጥታ ወደፊት ወይም ወደ ግራ የሚያልፍ ተሽከርካሪ የተቋረጡትን መሥመሮች ማቋረጥ ይችላል ። ያልተቋረጡትን መሥመሮች ማቋረጥ አይቻልም ።



ማስተላለፊያ ምልክቶች ፤ የቀለም ነጠብጣብ ባለባቸው ክልሎች ላይ መንዳት አይቻልም ።

## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፫/፮ (፲፱፻፶፮) ማ. ፶፩ ታረመ ። (በዚህ ማረሚያ መሠረት የአራት የመንገድ ምልክቶች ማገለጫ ተለውጦአል ። )

— አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም.

፳፯/፲ (፲፱፻፷) ሕ. ፫፻፴፭

## በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን (ትራንስፖርትን) ለመቆጣጠርና ለመወሰን በ፲፱፻፷ ዓ.ም. በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ።

፩/ አውጭው ባለሥልጣን ፤

በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን (ትራንስፖርትን) ስለመቆጣጠርና ስለመወሰን (በዚህ ደንብ ውስጥ አዋጅ እየተባለ በሚጠቀሰው) ቁጥር ፪፻፶፮/፲፱፻፷ ዓ.ም. በወጣው አዋጅ አንቀጽ ፳(፪) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት (ከዚህ በኋላ «ሚኒስትር» እየተባለ የሚጠራው) የመገናኛ ሚኒስትር ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፪/ አጭር አርእስት ፤

ይህ ደንብ «ከዚህ ቀደም ስለመንገዶች ጉዞ የወጡትን ደንቦች ስለማጽናት የወጣ የ፲፱፻፷ ዓ.ም. ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፫/ የጸኑት ደንቦች ፤

የሚከተሉት ደንቦች አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአዋጁ መሠረት ሚኒስትሩ እንዳወጣቸው ተቆጥረው የጸኑ ይሆናሉ ፤

www.chilot.me



ራት ፣ ወይም ለማስነዳት ፣ ሌላ ሰው እንዲያንቀሳቅስለት ወይም ከሥራ ላይ እንዲያውል ለት ለማድረግ ከሚኒስቴሩ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር መቀበል አለበት ።

፭/ በውጪ አገር ስላለ ባለንብረት ፤

፩/ ባለንብረቱ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ የማይኖር የማንኛውም የባለ ሞተር ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ ባለይዞታ ፣ ባለንብረት በውጪ አገር መሆኑን የሚያስረዳ ሠነድ ወዲያው አቅርቦ ስለተሽከርካሪው ዓይነትና ባለንብረትነት ዝር ዝር ፣ በተዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት የጽሑፍ መግለጫ ማቅረብ አለበት ፤

፪/ የተባለው ተሽከርካሪ በሚከተለው ሁናቴ ውስጥ የተገኘ እንደሆነ ፤ ባለንብረቱ በውጪ አገር መሆኑን ከሚያስረዳው መግለጫ ጋር የባለንብረትነትን መታወቂያ ደብተር ለመቀበል ማመልከቻ መቅረብ አለበት ፤

ሀ/ በውጭ አገር ምዝገባ ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ከዘጠና (፺) ቀን በኋላ ተሽከርካሪ ውን በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ ለመንዳት ፣ ለማንቀሳቀስ ወይም ለማሠራት የተፈለገ እንደሆነ ፤ ወይም

ለ/ ደንበኛ የውጭ አገር ምዝገባ የሌለው ወይም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መን ግሥት ከማይቀበለው አገር መንግሥት የተሰጠ ወይም ጊዜው ያለፈበት የሆነ እንደሆነ ፤

፫/ ባለንብረቱ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ የሌለ የባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም የተሳቢ ባለይዞታ ፣ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ለመቀበል ማመል ከቻ እንዲያቀርብ ሲያስፈልግ የተባለው ባለይዞታ ለተባለው ባለንብረት ወኪል እንደሆነ ይቆጠራል ።

፮/ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር የማያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች ፤

ከዚህ ለሚከተሉት የተሽከርካሪ ዓይነቶች የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር አስፈላጊ አይሆንም ፤

፩/ ባለንብረትነቱ የባለፋብሪካ ፣ የነጋዴ ፣ የዳግመ ሠሪ ወይም የሬከር የሆነና በመዝገብ የተያዘ ወይም ለንግድ የሚሸጥ ተሽከርካሪ ፤

፪/ በኢንተርናስዮናል ትራፊክ ሥራ ውስጥ ያለና ቀኑ ያላለፈበት የባለንብረትነት መታ ወቂያ ከሌላ አገር የተሰጠው ማንኛውም ተሽከርካሪ ፤

፫/ ማንኛውም የወታደር ተሽከርካሪ ፤

፬/ ማንኛውም የእርሻ መሣሪያ ፤

፭/ ማንኛውም ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ፤ ወይም

፮/ ማንኛውም በራሱ የሚንቀሳቀስ የሕሙማን ጋሪ ፤

፯/ ስለባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር የሚቀርብ ማመልከቻ ፤

፩/ ተሽከርካሪው ለግለጋሎት በተላለፈ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ የተላለፈበት ሰው ፣ ወይም የሚመለከተው ሲሆን ባገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ የባለንብረትነት መታወ ቂያ ደብተር እንዲሰጠው በተመደበው ፎርም ሞልቶ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት ፤

፪/ ከማመልከቻውም ጋር ለሚያስተላልፈው ሰው የተሰጠው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርና የባለቤትነት ማስረጃ ጽሑፍ አብረው መቅረብ አለባቸው ።

www.chilot.me



እንዲያሠራለት ለማድረግ ከሚኒስቴሩ አስፈላጊውን የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ተቀብሎ በተሽከርካሪው ላይ መለጠፍ አለበት ።

፲፫/ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ የማያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች ፤

ከዚህ ለሚከተሉት የተሽከርካሪ ዓይነቶች የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች አስፈላጊ አይሆኑም ፤

፩/ በእንተርናስዮናል ትራፊክ የሚያገለግል ፤ ከሌላ አገር የተሰጠው የታወቀና ቀኑ ያላለፈበት የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ያለው ፤ ማንኛውም ተሽከርካሪ ፤

፪/ ማንኛውም የወታደር ተሽከርካሪ ፤

፫/ ማንኛውም የእርሻ መሣሪያ ፤

፬/ ማንኛውም ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ፤

፭/ ማንኛውም በራሱ የሚንቀሳቀስ የሕሙማን ጋሪ ፤

፲፬/ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ስለማሳየት ፤

፩/ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ሁሉ በሚከተለው አኳኋን ተለጥፎ መታየት አለበት ፤

ሀ/ ለሞተር ሳይክል ሁለት (፪) ተመሳሳይ ሠሌዳዎች ይሰጡታል ። አንዱ ሠሌዳ በፊተኛው ጭቃ መከላከያ ላይ በመንኰራኵሩ ከፍታ ልክ የሚለጠፍ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ሠሌዳ ከኋላ በሞተር ሳይክሉ አግዳሚ ዘንግ ላይ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን እንደሚታይ ሆኖ መለጠፍ አለበት ፤

ለ/ ለባለሞተር ተሽከርካሪ ፤ ከሞተር ሳይክል ሌላ ፤ ሁለት (፪) ተመሳሳይ ሠሌዳ ዎች ይሰጣሉ ። አንደኛው ሠሌዳ ከፊት ሲደረግ ፤ ሁለተኛው ደግሞ ከኋላ ይደረጋል ። ሁለቱም ሠሌዳዎች ከተሽከርካሪው አግዳሚ ዘንግ ጋር በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን እንደሚታዩ ሆነው መለጠፍ አለባቸው ፤

ሐ/ ለተሳቢ ፤ አንድ (፩) ሠሌዳ ይሰጠዋል ። ይህም ሠሌዳ ከኋላ ከተሳቢው አግ ዳሚ ዘንግ ጋር በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን እንደሚታይ ሆኖ ይለጠፋል ።

፪/ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ሁሉ ከላይ ወደታች ወይም እስከተቻለ ድረስ ከላይ ወደታች ሆነው መለጠፍ አለባቸው ።

፫/ ሠሌዳ ሁሉ በግልጽ እንደሚታይና እንደማይከለል ሆኖ ይለጠፋል ።

፲፭/ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ አጠባበቅ ፤

፩/ በመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ላይ ፤ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ለ» እንደተመለከተው ፊደሉ ፤ ቀለሙ ፤ ወይም ምልክቱ የተሰጠበትን ዓላማ ወይም ትርጉም የሚያሳስት ወይም ትክክለኛነቱን የሚያፋልስ ስሕተት ወይም ግድፈት መኖሩን ባወቀ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ፤ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ የሚኖር ባለይዞታ ለሚኒስቴሩ አመልክቶ ሠሌዳው እንዲለወጥ ማቅረብ አለበት ። ስሕተቱ ወይም ግድፈቱ የተፈጸመው በሚኒስቴሩ ጥፋት ፤ አለመጠንቀቅ ወይም ዝንጋታ ብቻ ካልሆነ ፤ ባለንብረቱ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት የመታወቂያ ሠሌዳ በሚለወጥበት ጊዜ የሚከፈለውን ገንዘብ መክ ፈል አለበት ።

፪/ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ፤ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ለ» እንደ ተመለከው ፊደሉ ፤ ቀለሙ ፤ ወይም ምልክቱ የተሰጠበትን ዓላማ ወይም ትርጉም

www.chilot.me



የሚያሳስት ወይም ትክክለኛነቱን የሚያፋልስ የተለወጠ ነገር መኖሩን ባወቀ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ፣ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ የሚኖር ባለ ይዞታ ለሚኒስቴሩ አመልክቶ ሠሌዳው እንዲለወጥ ማቅረብ አለበት ። ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት ሠሌዳ በሚለወጥበት ጊዜ የሚከፈለውንም ገንዘብ ባለንብረቱ መክፈል አለበት ።

፫/ አንዱ ወይም ሁለቱ የመታወቂያ ሠሌዳዎች የጠፉ ፣ የተሰረቁ ፣ የተቀደዱ ፣ የተበላሹ ወይም የማይነበቡ የሆኑ እንደሆነ ፣ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ የሚኖር ባለይዞታ ወዲያው ለሚኒስቴሩ ይህንኑ አመልክቶ የቀረ ወይም የቀሩ ሠሌዳዎች እንዳሉ እንዲለወጡ ማቅረብ አለበት ። ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት የመታወቂያ ሠሌዳዎች በሚለወጡበት ጊዜ የሚከፈለውንም ገንዘብ ባለንብረቱ ይከፍላል ።

## ፲፯/ ስለመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ አለመኖር ፤

ማንኛውም ተሽከርካሪ ፣ ደንበኛ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ ሳይደረግበት የተነዳ ፣ የተንቀሳቀሰ ወይም በሥራ ላይ የዋለ እንደሆነ ፤

፩/ የመታወቂያው አለመታየት የተሽከርካሪው ባለንብረትነት በሚገባ ያልተረጋገጠ ለመሆኑ መነሻ ማስረጃ ሆኖ ይቆጠራል ፤

፪/ የተሽከርካሪው ባለንብረትነት በደንብ መረጋገጡን ማስረዳት የተባለው ተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ ያለ ባለይዞታ ተግባር ይሆናል ፤

፫/ የባለንብረትነቱ ጉዳይና በደንብ የመረጋገጡ ነገር እስኪጣራ ድረስ ፤ ሕግ አስከባሪው ባለሥልጣን ተሽከርካሪውን ማቆየት ይችላል ፤ ተሽከርካሪው ሊለቀቅ የሚችለውም በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈለጉት የተሽከርካሪ መለያ ጉዳዮችና ሠነዶች ሁሉ ከተገኙ ፤ ከቦታው ከተመለሱ ወይም ከተተኩ በኋላ ብቻ ነው ።

## ለ/ ስለነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ፤

## ፲፰/ ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ስለመስጠት ፤

፩/ ከታች በአንቀጽ ፰ የተወሰነው ተፈጻሚ ካልሆነ በስተቀር ፤ ማናቸውም የተሽከርካሪን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ለመቀበል የሚቀርብ ማመልከቻ ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ለማግኘት እንደቀረበ ማመልከቻ ይቆጠራል ፤

፪/ የባለንብረትነት መታወቂያ ለአመልካቹ መስጠት ይገባል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲወስንና አመልካቹ በሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት ለነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚከፈለውን ገንዘብ ሲከፍል ፤ ከባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ጋር በአንቀጽ ፲፩ በተወሰነው መሠረት ፣ የሚፈለገውን ያህል ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ሚኒስቴሩ ለአመልካቹ ይሰጣል ፤

፫/ ስለሆነም ፣ የሥራ ተሽከርካሪ ሲተላለፍ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን ከወሰነ በኋላ አመልካቹ አዲስ ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች እንዲወስድ አይጠየቅም ፤

ሀ/ ፩/ በተላለፈው ተሽከርካሪ ላይ የተለጠፉት ሠሌዳዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ለ» መሠረት ትክክለኛውን ባለንብረት ፣ ተሽከርካሪው በሚሠራበትና በማያገለግልበት ጊዜ መቆሚያ ቦታውን የሚለዩ ሲሆኑ ፤

www.chilot.me



፪/ ሠሌዳዎቹ በግልጽ በሚታዩበትና በሚታወቁበት አኳኋን ሲሆኑ ፤

ለ/ የተደረገውን የባለንብረትነት ለውጥ በመታወቂያ ሠሌዳዎች መዝገብና ሠነዶች ውስጥ ሚኒስቴሩ ሲያስተካክል ።

፲፰/ ስለነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ደንበኛነት ፤

የነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ደንበኛነት የሚጸናው ከተሰጡበት ቀን አንሥቶ ፤

፩/ መታወቂያው የተሰጠው ተሽከርካሪ ከጥቅም ውጭ ፤ ከወላለቀ (ስክሬፕት) ወይም ጨርሶ መንገድ ላይ እንዳይሠራበት እስከተደረገበት ድረስ ፤ ወይም

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ለ» እንደተመለከተው በመታወቂያ ሠሌዳዎቹ ላይ ያለው ፊደል ፤ ቀለም ወይም ምልክት ትክክለኛ ሆኖ እስካልተገኘ በት ጊዜ ነው ። ከሁለቱ ቀድሞ የደረሰው ተፈጻሚ ይሆናል ።

፲፱/ ነዋሪ የመታወቂያ ሠሌዳዎችን ስለማስረከብ ፤

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ያለው ማንኛውም ተሽከርካሪ ከጥቅም ውጭ ፤ ከወላለቀ (ስክሬፕት) ወይም መንገድ ላይ እንዳይሠራበት በተደረገበት በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ባለንብረቱ ወይም በአገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ ጉዳዩን ለሚኒስቴሩ አስታውቆ ሠሌዳዎቹ እንዲሰረዙ ለዚሁ ሚኒስቴር አምጥቶ ማስረከብ ይኖርበታል ፤

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በአባሪ «ለ» ውስጥ እንደተመለከተው ሳይሆን ቀርቶ በመታወቂያ ሠሌዳዎች ፊደል ፤ ቀለም ወይም ምልክት ውስጥ ትርጉሙን የሚለውጥ ነገር ሲገኝ ባለንብረቱ ወይም ባገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ ሠሌዳዎቹ እንዲለወጡ ለሚኒስቴሩ ማስረከብ ይኖርበታል ።

## ሐ/ ዕለታዊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ፤

፳/ ዕለታዊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ስለመስጠት ፤

፩/ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ለመቀበል ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ፤ ባለንብረቱ እንዲታወቅ የቀረበው ተሽከርካሪ ሥራ ላይ በማይውልበት ጊዜ ደንበኛ መቀመጫው ያልታወቀ ወይም ያልተወሰነ ወይም ሚኒስቴሩ በማንኛውም ምክንያት ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች መስጠት የማይቻለው የሆነ እንደሆነ ፤ ለተባለው ተሽከርካሪ የሚሆን ዕለታዊ የመታወቂያ ሠሌዳዎች ለአመልካቹ ይሰጣል ፤

፪/ ለአመልካቹ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር መስጠት ይገባል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲወስንና አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በአባሪ «ሀ» መሠረት ለዕለታዊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚከፈለውን ገንዘብ ሲከፍል ፤ በአንቀጽ ፲፩ በተወሰነው መሠረት የሚፈለገውን ያህል ዕለታዊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ከባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ጋር ሚኒስቴሩ ለአመልካቹ ይሰጣል ።

፳፩/ ስለዕለታዊ የመታወቂያ ሠሌዳዎች ደንበኛነት ፤

፩/ የዕለታዊ የመታወቂያ ሠሌዳዎች ደንበኛነት የሚጸናው ከተሰጡበት ቀን አንሥቶ ለአሥራ አምስት (፲፭) ቀን ነው ፤

www.chilot.me



፪/ ሚኒስቴሩ የመደበው ፎርም ተሞልቶ ሲቀርብና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ገንዘብ ሲከፈል ፤ ጊዜው እንደገና ለአሥራ አምስት ቀን ሊታደስ ወይም ሊራዘም ይቻላል ፤ ስለሆነም ይህ የሚደረገው ተሽከርካሪው በሥራ ላይ በማይውልበት ጊዜ ደንበኛ መቀመጫው ያልታወቀ ወይም ያልተወሰነ እንደሆነ ወይም በማንኛውም ምክንያት ሚኒስቴሩ ነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች መስጠት የማይቻለው የሆነ እንደሆነ ነው ።

፳፪/ ዕለታዊ የመታወቂያ ሠሌዳዎችን ስለማስረከብ ፤

የዕለት መታወቂያ ሠሌዳዎች የተሰጡት ተሽከርካሪ በሥራ ላይ በማይውልበት ጊዜ ደንበኛ መቀመጫው የት እንደሆነ በእርግጥ እንደታወቀ ፤ ወይም ሚኒስቴሩ ነዋሪ የመታወቂያ ሠሌዳዎች እንዳይሰጥ ያደረገው ምክንያት እንደተወገደ ፤ ባለንብረትነቱ ወይም ባገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ የዕለት ሠሌዳዎችን ለሚኒስቴሩ ወዲያው ያስረክባል ፤ በተመደበው ፎርም ላይ ተሽከርካሪው በሥራ ላይ በማይውልበት ጊዜ ደንበኛ መቀመጫው የት እንደሆነ ገልጦ አስቀድሞ ያልተከፈለ ከሆነ ፤ በሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት ለነዋሪ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚከፈለውን ገንዘብ ይከፍላል ።

## መ/ ተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ፤

፳፫/ የተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ልዩ አሠራር ፤

፩/ ተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚሰጡት የባለፋብሪካ ፤ የነጋዴ ፤ የዳግመ ሠሪ ወይም የሬከር ንብረት ለሆነ በመዝገብ ለተያዙ ተሽከርካሪዎች ብቻ በማለዋወጥ እንዲሠራባቸው ነው ፤

፪/ ተላላፊ ሠሌዳዎች የተደረጉባቸው ተሽከርካሪዎች በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገዶች ላይ ሲሄዱ ፤ ሲንቀሳቀሱ ወይም ሲሠራባቸው የሚቻል ለሚከተሉት ጉዳዮች ብቻ ነው ፤

ሀ/ ከገቡበት ወደብ ወይም ከተገዙበት ሥፍራ ወደ ንግድ ሥፍራ ለማዛወር ፤ ስለሆነም ደንበኛ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የተደረገበት የነጋዴ ተሽከርካሪ በሚጐትታቸው አዳዲስ ተሽከርካሪዎች ሠሌዳዎችን መለጠፍ አስፈላጊ አይሆንም ።

ለ/ አልፎ አልፎ ከመጋዘን ወደሚሳያ ክፍል ወይም ለሽያጭ ወደሚታይበት ሥፍራ ለመውሰድና ወደመጋዘን ለመመለስ ፤

ሐ/ ለሙከራ ወይም ለፍተሻ ብቻ የሚደረግ መንዳት ፤

መ/ ለማሳያ ለሚደረግ መንዳት ከሃያ አምስት ኪሎሜትር ለማይበልጥ የደርሶ መልስ ርቀት ፤

ሠ/ በአስቸኳይ ጊዜ ለሚደረግ መንዳት ፤ እና ወይም

ረ/ ከንግድ ሥፍራ ለገዢ ወይም ለተላለፈለት ሌላ ሰው እስከማድረሻ ሥፍራ ለሚደረግ መዘዋወር ፤

፫/ ባለንብረትነታቸው የባለፋብሪካ ፤ የነጋዴ ፤ የዳግመ ሠሪ ፤ የሬከር ወይም የአመላላሽ በሆኑ በሥራ ወይም በአገልግሎት ተሽከርካሪዎች ላይ ምንጊዜም ቢሆን ተላላፊ ሠሌዳዎች አይደረጉም ።

www.chilot.me



፳፬/ ተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎችን ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ ፤

፩/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ወይም የተሳቢ ባለፋብሪካ ፤ ነጋዴ ፤ ዳግመ ሠሪ ወይም ሬከር አንድ ወይም ብዙ ተላላፊ የመታወቂያ ሠሌዳዎችን ለመቀበል በተመደበው ፎርም ሚኒስቴሩን ሊጠይቅ ይችላል ። ከተባለው ማመልከቻም ጋር አመልካቹ እውነተኛ ባለፋብሪካ ፤ ነጋዴ ፤ ዳግመ ሠሪ ወይም ሬከር መሆኑን የሚያረጋግጥ ሚኒስቴሩ የሚጠይቀውን ተገቢ ማስረጃ ማቅረብ አለበት ፤

፪/ ሚኒስቴሩ ማመልከቻው እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጥና ለአመልካቹ ተላላፊ የመታወቂያ ሠሌዳዎች እንዲሰጡ ሲወስን ፤ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ለተላላፊ ሠሌዳዎች የሚከፈለውን ገንዘብ አመልካቹን አስከፍሎ የተጠየቁትን ተላላፊ የመታወቂያ ሠሌዳዎች ይሰጠዋል ፤

፫/ ተላላፊው የመታወቂያ የቁጥር ሠሌዳ ወይም ጥንዱ የተሰጠው ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ የሆነ እንደሆነ ፤ ከአለፈው ጳጉሜ መጨረሻ ቀን ጀምሮ ሠሌዳው እስከተሰጠ በት ቀን ድረስ ላለው ለያንዳንዱ ሙሉ ወር ከአሥራ ሁለት አንድ እጅ ተቀንሶ ይከፈላል ።

፳፭/ የተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች ደንበኛነት ፤

፩/ እያንዳንዱ ተላላፊ የመታወቂያ የቁጥር ሠሌዳ ወይም ጥንዱ ደንበኛ የሚሆነው ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ እስከሚቀጥለው ጳጉሜ መጨረሻ ቀን ድረስ ነው ፤

፪/ እያንዳንዱ ተላላፊ የቁጥር ሠሌዳ ወይም ጥንዱ ለአንድ ተጨማሪ ዓመት ጊዜ ሊታደስ ወይም በአዲስ ሊተካ ይችላል ። ይሀም የሚደረገው አመልካቹ ሚኒስቴሩ በመደበው ፎርም ማመልከቻ ሲያቀርብና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠ ረዥ «ሀ» መሠረት ተገቢውን ገንዘብ ሲከፍል ነው ።

፳፮/ በተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎችን ስለመመዝገብ ፤

እያንዳንዱ የባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም የተሳቢ ባለፋብሪካ ፤ ነጋዴ ፤ ዳግመ ሠሪ ወይም ሬከር ፤ በተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎችንና እያንዳንዱ ሠሌዳ ወይም ጥንዱ በአንድ ተሽከርካሪ ላይ የሚደረግበትን ጊዜ መጠን ሚኒስቴሩ በመደበው ፎርም ሞልቶ መያዝ አለበት ። ይህንም ሠነድ ማናቸውም የተፈቀደለት የፖ ሊስ ሹም ወይም የሚኒስቴሩ ሠራተኛ ለምርመራ ሊያየው ይችላል ።

## ክፍል ፬

## ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ ፤

፳፯/ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ስለማስፈለጉ ፤

ማናቸውም የባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም የተሳቢ ባለንብረት ፤ በሚከተሉ ሁኔቴዎች ካልሆነ በስተቀር ፤ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገዶች ላይ የተባለውን ተሽከር ካሪ ሊነዳ ፤ ሊያንቀሳቅስ ወይም ሊያሠራ ፤ ወይም እንዲነዳ ፤ እንዲንቀሳቀስ ፤ ወይም እንዲ ሠራበት ሊፈቅድ አይችልም ።

፩/ ደንበኛ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ተሰጥቶትና በሚገባ ተለጥፎ የታየ እንደሆነ ፤

www.chilot.me



፪/ የተባለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ የሚነዳው ፤ የሚንቀሳቀሰው ወይም የሚሠራው በተለጣፊው ምልክት ላይ ለተፈቀደው ጉዳይ ብቻ የሆነ እንደሆነ ።

፳፰/ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ስለማያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች ፤

የሚከተሉት የተሽከርካሪ ዓይነቶች መመዝገብ አያስፈልጋቸውም ፤

፩/ ባለንብረቱ ወይም ባገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ ተሽከርካሪውን ወይም ተሳቢውን ቢያንስ ለተወሰነ ለአንድ (፩) ዓመት ጊዜ አልነዳም ፤ አላንቀሳቀሰም ወይም አላሠራም ብሎ በጽሑፍ ለሚኒስቴሩ ሲያስታውቅ ፤

፪/ በሌላ አገር ደንበኛ ምዝገባ የተደረገለትና በኢንተርናስዮናል ትራፊክ የሚሠራ ማንኛውም ተሽከርካሪ ፤

፫/ ባለንብረቱ ባለፋብሪካ ፤ ነጋዴ ፤ ዳግመ ሠሪ ወይም ሬከር ሆኖ በመዝገብ የተያዘ ወይም ለንግድ የተመደበ ማንኛውም ተሽከርካሪ ፤

፬/ ማንኛውም የወታደር ተሽከርካሪ ፤

፭/ ማንኛውም የእርሻ መሣሪያ ፤

፮/ ማንኛውም ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ፤

፯/ ማንኛውም የሕሙማን ጋሪ ፤

፳፱/ ለዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ማመልከቻ ስለማቅረብ ፤

፩/ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ በመንገድ ላይ እንዲውል ሲደረግ እና ፤

፪/ ከዚያም በኋላ በዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ፤ በማንኛውም አኳኋን ከየካቲት ፴ ቀን በፊት ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ለመቀበል ባለንብረቱ ወይም በአገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ ለሚኒርስቴሩ በሁለት ግልባጭ ማመልከቻ ማቅረብና የተዘጋጀውን (ቅጽ) ፎርም በሚገባ መሙላት አለበት ።

፴/ ስለማመልከቻ አቀራረብ ፤

፩/ ለዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ማመልከቻ እንደደረሰው ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን ይፈጽማል ፤

ሀ/ ማመልከቻውን ከአፊሴፄል መዝገቡና ከሠነዶቹ ጋር ማነጻጸር ፤

ለ/ በማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የመለያ ቁጥር በተሰረቁና በተለወጡ ተሽከርካሪዎች መዝገብ ውስጥ ካሉ ቁጥሮች ጋር ማስተያየት ፤

ሐ/ በጠቅላላውም ፤ የባለሞተር ተሽከርካሪው ወይም የተሳቢው የባለንብረትነት መታወቂያ በሚገባ የተረጋገጠና አመልካቹ እውነተኛ ባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ ያለ ባለይዞታ መሆኑን ማረጋገጥ ፤

፪/ ከዚህ በኋላ ፤ ሚኒስቴሩ አንዱን ግልባጭ ለአመልካቹ ይመልስለታል ፤ በዚህ ግልባጭ መሠረትም የተሽከርካሪው ምርመራ ይደረጋል ።

፴፩/ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችንና ተሳቢዎችን ለምርመራ ስለማቅረብ ፤

፩/ የባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም የተሳቢ ባለንብረት ወይም በአገር ውስጥ ያለ ባለይዞታ ለዓመታዊ ምዝገባ ማመልከቻውን ካቀረበ በኋላ ፤ የተባለውን ተሽከርካሪ ሚኒ

www.chilot.me



ስቴሩ የዚያ ዓይነት ተሽከርካሪ እንዲመረመር በሚመድበው ወይም በሚፈቅደው የምርመራ ጣቢያ ለምርመራ ማቅረብ ይኖርበታል ፤

፪/ እጅግ አስቸጋሪ ወይም አደጋች በሚሆንበት ጊዜና በጽሑፍ አቤቱታ ሲቀርብለት ፤ ሚኒስቴሩ በማያገለግሉበት ጊዜ በሩቅ ሥፍራ ለሚቀመጡ ተሽከርካሪዎች የምርመራ ግዴታን ሊያስቀር ይችላል ።

፴፪/ <u>የምርመራ ጣቢያዎች ፤</u>

፩/ የምርመራ ጣቢያዎች ከታች በአንቀጽ ፴፫ በተደነገባው መሠረት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችንና ወይም ተሳቢዎችን ለመመርመር የሚችሉ ድርጅቶች ይሆናሉ ፤

፪/ የምርመራ ጣቢያዎች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ ፤

ሀ/ በሚኒስቴሩ ተቋቁሞ የሚካሔድ ድርጅት ፤

ለ/ ወይም ፤ ሚኒስቴሩ የሚችል ፤ የሚያገለግልና ለሕዝብ ጥቅም ተስማሚ ነው ብሎ አስቀድሞ ሲወስን ሥልጣን ተሰጥቶት እንዲመረምር የተወከለ ማንኛውም የባለሞተር ተሽከርካሪ እና ወይም የተሳቢ አገልግሎት (ጋራዥ) ወይም የማደሻ ድርጅት ። ውክልናውም በጽሑፍ ተዘርዝሮ ለተወካዩ ከሚኒስትሩ ይሰጣል ።

፫/ ስለሆነም ፤ ምንጊዜም ቢሆን አዲስ ተሽከርካሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በመንገድ ላይ እንዲያገለግል ሲደረግ ሚኒስቴሩ ባቋቋመውና በሚያካሂደው ድርጅት መመርመር አለበት ።

፴፫/ <u>ስለምርመራ መምሪያ ፤</u>

በምርመራ ጣቢያዎች ሥልጣን የተሰጣቸው መርማሪዎች የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የሚቀርበውን እያንዳንዱ ተሽከርካሪ መመርመር አለባቸው ፤

፩/ በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርና በመጨረሻው ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ላይ የሠፈሩት የመለያ ዝርዝር ጉዳዮች ትክክለኛ መሆናቸውን ፤

፪/ አመልካቹ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጠው ባቀረበው ማመልከቻ ላይ ያመለከተውን ጉዳይ ተሽከርካሪው አደጋን በማያስከትል አኳኋን ለመፈጸም የሚችል መሆኑን ፤

፫/ ተሽከርካሪው ስለተሽከርካሪ አሠራር ፤ አያያዝ ፤ መጠንና ክብደት የተመደቡትን ሕጎችና ደንቦች የተከተለ መሆኑን ።

፴፬/ <u>የምርመራ ምስክርነት ስለመስጠት ፤</u>

ተሽከርካሪው የሚፈለግበትን የምርመራ መምሪያ በሙሉ መፈጸሙን ካረጋገጠ በኋላ ፤ ሥልጣን የተሰጠው መርማሪ ለባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ ላለው ባለይዞታ አንድ የምርመራ ምስክርነት ይሰጠዋል ። ለዚሁም ባለንብረቱ ወይም ባገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ በሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ለተሽከርካሪ ምርመራ የተመደበውን ገንዘብ ይከፍላል ።

፴፭/ <u>ስለምርመራ ምስክርነት ጠባይና ጽኑነት ፤</u>

የምርመራ ምስክርነት ምርመራ ስመደረጉ የሠነድ ማስረጃ ሆኖ ለአንድ (፩) ዓመት ጸንቶ የሚቆይ ነው ፤ ከታች በአንቀጽ ፴፮ በተወሰነው መሠረት ካልሆነም ፤ በዚህ በተባለው ዓመት ውስጥ ተሽከርካሪው እንደገና አይመረመርም ።

www.chilot.me



፴፮/ ስለልዩ ምርመራ ፤

በትራፊክ ፖሊስ ደንብ መሠረት ሥልጣን የተሰጠው ማናቸውም የትራፊክ ፖሊስ መኰንን ማንኛውም ተሽከርካሪ የሚከተሉት በግልጽ የጐደሉት እንደሆነ በማንኛውም ጊዜ ልዩ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ይችላል ።

፩/ ተሽከርካሪው በመንገድ ላይ ለማገልገል ብቁ ያልሆነ እንደሆነ ፤

፪/ ስለተሽከርካሪ አሠራር ፣ አያያዝ ፣ መጠንና ክብደት የተመደቡትን ሕጎችና ደንቦች ያልተከተለ የሆነ እንደሆነ ፤ ወይም

፫/ በመንገድ አደጋ ምክንያት ከባድ ጉዳት የደረሰበት የሆነ እንደሆነ ።

ስለሆነም ፤ እንዲህ ያለው ልዩ ምርመራ ሲደረግ የሚቻለውና የሚደረገው ሚኒስቴሩ ባቋቋመውና በሚያካሄደው የምርመራ ጣቢያ ሲሆን ነው ። ስለዚህ ዓይነት ልዩ ምርመራ ዋጋ ወይም ገንዘብ አይከፈልም ።

፴፯/ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ስለመስጠት ፤

፩/ ሚኒስቴሩ ማመልከቻው እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጥና ምርመራው እንዲቀር ካልተደረገ በደንበኛ የምርመራ ምስክርነት ላይ በተመለከተው መግለጫ መሠረት ተሽከርካሪው ለመንዳት ፣ ለመንቀሳቀስ ወይም ለመሥራት ብቁ መሆኑን ሲወስን ፤ አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ተገቢውን ገንዘብ ከፍሎ አንድ (፩) ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል ፤

፪/ ስለሆነም ፤ አዲስ ተሽከርካሪ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያገለግል ሲመዘገብ ፤ ከምዝገባው ጊዜ አልፎ እንደሆነ የዓመቱ ተከፋይ ገንዘብ ከየካቲት ወር መጨረሻ ቀን አንሥቶ የምዝገባው ተለጣፊ ምልክት እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ላለው ለያንዳንዱ ሙሉ ወር ከአሥራ ሁለት አንድ እጅ ተቀናሽ ይሆናል ።

፴፰/ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክትን ስለመያዝና ማሳየት ፤

፩/ ከፊት የነፋስ መከላከያ መስታወት ላላቸው ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የተሰጠው ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ከመስታወቱ ላይ በታችኛው የቀኝ ማዕዘን ተለጥፎ መታየት አለበት ፤

፪/ ለሌሎች ባለሞተር ተሽከርካሪዎችና ተሳቢዎች የተሰጠው ዓመታዊ የምዝገባ ተለ ጣፊ ምልክት ግን በተሰጠው ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም ተሽከርካሪው በማንኛውም በንተሡ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ በሚነዳበት ፤ በሚንቀሳቀስበት ወይም በሚሠራበት ጊዜ ሁሉ ተሽከርካሪውን በሚነዳው ፤ በሚያንቀሳቅሰው ወይም በሚያ ሠራው ሰው እጅ መቀመጥ አለበት ።

፴፱/ ስለዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት አጠባበቅ ፤

፩/ በተለጣፊው ምልክት ላይ በተመለከቱት ዝርዝሮች ውስጥ አንዳች ስሕተት ወይም ትክክል ያልሆነ ዝርዝር መኖሩን ባወቀ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ፤ ዓመታዊ የምዝ ገባ ተለጣፊ ምልክት የያዘ ሰው ለሚኒስቴሩ አስታውቆ ምልክቱን ለአርማት ማቅ ረብ አለበት ። በተጨማሪም ፣ ስሕተቱ ወይም ትክክል ያልሆነው ዝርዝር የተደረገው በሚኒስቴሩ ጥፋት ፤ አለመጠንቀቅ ወይም ዝንጋታ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ፣ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ የተመደበውን ገንዘብ መክፈል አለበት ፤

www.chilot.me



፪/ በተለጣፊው ምልክት ውስጥ ከተመለከቱት ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ መለወጥ የሚያስፈልጋቸው መኖራቸውን ባወቀ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ፣ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት የያዘ ሰው የሚለወጡትን ጉዳዮች ለሚኒስቴሩ አስታውቆ እንዲሠረዙ ወይም እንዲተካከሉ ካርዱን ማቅረብ አለበት ። በተጨማሪም ፤ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ የተመደበውን ገንዘብ መክፈል አለበት ፤

፫/ ሀ/ አንድ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት የጠፋ ፣ የተሰረቀ ፣ የተቀደደ ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ ፤ የተመዘገበው ተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባገር ውስጥ ያለው ባለይዞታ ግልባጭ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጠው ወዲያው ለሚኒስቴሩ ማመልከት አለበት ፤

ለ/ አመልካቹ አጥጋቢ መረጃ ለሚኒስቴሩ ካቀረበና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» በተወሰነው መሠረት ለግልባጭ የተመደበውን ገንዘብ ከከፈለ በኋላ ፤ «ይህ ግልባጭ ነው» የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት አንድ ግልባጭ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል ።

ሐ/ ግልባጭ የተሰበጠበትን ዋና ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ያገኘ ሰው ፣ ግልባጩ እንዲሠረዝና እንዲቀደድ ፣ ወዲያው ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት ።

፵/ የዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ጽኑነት ፤

እያንዳንዱ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ የሚከተለው ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ ይፀናል ።

፵፩/ ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ስለአለመያዝ ፤

አንድ ተሽከርካሪን የሚነዳ ፣ የሚያንቀሳቅስ ወይም የሚያሥራ ሰው ዓመታዊ የምዝገባ ተለጣፊ ምልክቱን እንዲያሳየው በትራፊክ ፖሊስ ደንብ ሥልጣን የተሰጠው የትራፊክ ፖሊስ መኰንን ሲጠይቀው ለማሳየት ያልቻለ እንደሆነ ፤

፩/ የዚህ ዓይነት የተሽከርካሪ መለያ አለመኖር ፣ ተሽከርካሪው በሚገባ ላለመመዝገቡ መጀመሪያ ማስረጃ ሆኖ ይቆጠራል ፤

፪/ ተሽከርካሪው በሚገባ መመዝገቡን የማስረዳቱ ተግባር የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም የባለይዞታው ይሆናል ፤

፫/ የመመዝገቡ ጉዳይ እስኪረጋገጥ ድረስ ሕግ አስከባሪው ባለሥልጣን ተሽከርካሪውን ይዞ ማቆየት ይችላል ። ተሽከርካሪው የሚለቀቀውም በዚህ ደንብ የተወሰነው የተሽከርካሪ መለያ ተግባር ከተፈጸመና የሚፈለጉ ሠነዶች ከተገኙ ፣ ከተመለሱ ወይም ከተተኩ በኋላ ብቻ ነው ።

## ክፍል ፰

## ስለ ኦፊስዬል መዝገብ ፣ ሠነዶችና ዝርዝሮች ፤

፵፪/ ስለመነሻ ማስረጃና ስለቅድሚያ ፤

፩/ በኦፊስዬል ሠነዶች የተያዙና በኦፊስዬል መዝገብ ላይ የሰፈሩ ማመልከቻዎች ፣ ደብዳቤዎች ፣ ፎርሞችና ሠነዶች ለተመዘገቡትና ለተያዙት ጉዳዮች መነሻ ማስረጃ ይሆናሉ ፤

www.chilot.me



፪/ የባለንብረትነት መብት በተላለፈላቸው ሰዎች መካከል ወይም እርስ በርሳቸው ክርክር በሚነሣበት ጊዜ ቅድሚያ የሚሰጠው የባለንብረትነት መታወቂያ በተሰጠበት ጊዜና ቀን መሠረት ነው ።

፵፫/ አፊስዬል መዝገብና ሠነዶችን ለሕዝብ ስለማሳየት ፤

፩/ አፊስዬል መዝገቡንና አፊስዬል ሠነዶቹን ለመመልከት ለሚፈልግና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» የተመደበውን ገንዘብ ለሚከፍል ለማናቸውም ሰው በሚኒስቴሩ የሥራ ሰዓቶች ጊዜ መዝገቡና ሠነዶቹ ክፍት ይሆናሉ ፤

፪/ በአፊሲዬል ሠነዶች ወይም በአፊሲዬል መዝገብ ውስጥ ያለን የማንኛውንም ሠነድ ግልባጭ በሙሉ ወይም በከፊል ለሚጠይቅ ፤ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» የተመደበውን ገንዘብ ለሚከፍል ለማናቸውም ሰው ሚኒስቴሩ ግልባጩን ይልካል ፤

፫/ ስለሆነም ፤ ሕግ አስፈጻሚ ባለሥልጣን ለሥራው አፈጻጸም እንዲረዳው መዝገቡንና ሠነዶቹን ለመመልከት ወይም ግልባጭ ለማግኘት ሲፈልግ ገንዘብ አይከፈልበትም ።

፵፬/ የታወቁና የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር ስለመያዝ ፤

፩/ ሚኒስቴሩ ባለንብረትነታቸው የታወቀና በያመቱ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ሁሉ ሙሉ ዝርዝር በሚገባ ይይዛል ፤

፪/ ሚኒስቴሩ የእነዚህን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር በየጊዜው ያዘጋጃል ፤ ሲጠየቅም ለሚገባቸው ባለሥልጣናት ያለዋጋ ፤ ለሌሎች ግን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» የተመደበውን ገንዘብ አስከፍሎ ያድላል ።

፵፭/ የተሰረቁ ወይም የተለወጡ ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር ስለመያዝ ፤

፩/ ሚኒስቴሩ የተሰረቁ ፤ የተለወጡ ፤ ጠፍተው የተገኙና ወይም ባለንብረቱ ያልተገኘ ተሽከርካሪዎችን ሙሉ ዝርዝር በሚገባ ይይዛል ።

፪/ ሚኒስቴሩ የእነዚህን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር በየጊዜው ያዘጋጃል ፤ ሲጠየቅም ለሚገባቸው ባለሥልጣኖች ያለዋጋ ፤ ለሌሎች ግን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሠንጠረዥ «ሀ» የተመደበውን ገንዘብ አስከፍሎ ያድላል ፤

፫/ ሚኒስቴሩ ተገቢ መስሎ በታየው በማናቸውም ጋዜጣ ዝርዝሮቹን ሊያሳትም ይችላል ።

## ክፍል ፯

## መደምደሚያ ውሳኔዎች ፤

፵፮/ ይህን ደንብ ስለመተላለፍ ፤

በዚህ ደንብ ውስጥ ከተሰጡት ውሳኔዎች ማንኛውንም የሚተላለፍ ማናቸውም ሰው እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ በተፈረደበት ጊዜ በዋናው አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ይቀጣል ።

www.chilot.me



ሐ/ ከ፲፩ ኩንታል በላይ ፤ ........................ 172.50
በተጨማሪም በኩንታል ፤ ........................ 0.50

፬/ ማንኛውም ያህል የኩንታል ጭነት መጠን ላላቸው ለንግድ ተሳቢዎች ፤ ........................ 25.00
በተጨማሪም በኩንታል ........................ 0.60

፭/ ለልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ፤ ........................ 150.00

ለ/ ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ ፤ በያንዳንዱ ጉዳይ ........................ 1.00

ሐ/ ለዓመታዊ የምዝገባ ካርድ ግልባጭ ........................ 5.00

፭/ <u>ኦፊሲዩል መዝገብን ፤ ሠነዶችንና ዝርዝሮች ለማየት ለሚጠይቅ ሰው ፤</u>

ሀ/ ኦፊሲዩል መዝገብን ሠነዶችንና ዝርዝሮች ለመመልከት ........................ 1.00
ለ/ በኦፊሲዩል መዝገብ ወይም በሠነዶች ውስጥ የሚገኝ የማንኛ ውንም ሠነድ ትክክለኛ ግልባጭ በሙሉ ወይም በከፊል ለመቀበል ለያንዳንዱ ገጽ ወይም ለከፊሉ ፤ ........................ 2.00
ሐ/ ለኦፊሲዩል ዝርዝር ግልባጭ ፤ ለገጽ ወይም ለከፊሉ ........................ 1.00

## <u>ሠንጠረዥ «ለ»</u>

### <u>የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሳቢ መታወቂያ ሠሌዳ ዘዴዎች ፤</u>

፩/ <u>የቀለም ኅብር ፤</u>

በመታወቂያ ሠሌዳዎች ላይ የሚሠራበት የቀለም ኅብር ሠሌዳዎቹ የተለጠፉባቸውን ተሽከርካሪዎች ባለንብረትነትና የሚውሉበትን ተግባር ይገልጻል ። እንደሚከተለው የተዘረዘረው የቀለም ኅብር የሚከተለው ትርጉም ይኖረዋል ፤

| <u>የቀለም ኅብር ፤</u> | <u>ትርጉም ፤</u> |
|---|---|
| ሀ/ <u>ነጭ ሠሌዳ</u> ከጥቁር ፊደሎችና ቁጥሮች ጋር ፤ | ሀ/ ከወታደራዊ ክፍል በቀር ፤ የኢትዮጵያ ን. ነ. መንግሥት መ/ቤቶች ወይም ራሳቸውን የቻሉ ድርጅቶች ንብረት የሚሆንና ለመንግሥት ሥራ የሚውል። |
| ለ/ ክፍት <u>ሰማያዊ ሠሌዳ</u> ከብርማ ፊደሎችና ቁጥሮች ጋር ፤ | ለ/ ለተባበሩት መንግሥታት ፤ ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ወይም ለሌላ ለማንኛውም እንተርናስዮናል ድርጅት ወይም ለቅርንጫፎቻቸው ንብረት የሚሆንና ለኦፊስዩል ሥራ የሚውል ። |
| ሐ/ <u>ነጭ</u> ሠሌዳ ከጥቁር ፊደሎችና ቁጥሮች ጋር ፤ በስተግራ በኩል <u>ቢጫ</u> የተቀባ ፤ | ሐ/ ለዲፕሎማቲክ ፤ ለቆንሲላ ወይም ለሌሎች የውጭ አገር መልክተኞች ወይም ለቅርንጫፎቻቸው ንብረት የሚሆንና ለኦፊስዩል ሥራ የሚውል ። |
| መ/ <u>ጥቁር</u> ሠሌዳ ከነጭ ፊደሎችና ቁጥሮች ጋር ፤ | መ/ ማናቸውም ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው በንብረቱ ላይ አድርጎ በግል የሚጠቀምበት ። |
| ሠ/ <u>አረንጓዴ</u> ሠሌዳ ከነጭ ፊደሎችና ቁጥሮች ጋር ፤ | ሠ/ እንደታክሲ ባለ በግል ንብረት ላይ ተደርጎ ለኪራይ ወይም ለንግድ የሚውል ። |

www.chilot.me



፪/ የፊደል ጣምራ ፤

በመታወቂያ ሠሌዳዎች ላይ የሚሠራበት የፊደል ጣምራ የሚከተለው ትርጉም ይኖረዋል ፤

ሀ/ የሚከተሉ የፊደል ጣምራ ሠሌዳዎች የተለጠፉባቸውን ተሽከርካሪዎች ባለንብረት ነትና ለምን ሥራ እንደሚውሉ ይገልጻሉ ።

| የፊደል ጣምራዎች ፤ | ትርጉም ፤ |
|---|---|
| ፩. CC | ፩/ የቆንስላ መልእክተኞች ወይም የቅርንጫፎቻቸው ንብረት የሚሆንና ለኦፊስዮል ሥራ የሚውል ፤ |
| ፪. CD | ፪/ የዲፕሎማቲክ ፤ ወይም የሌሎች የውጪ አገር መልክተኞች ወይም የቅርንጫፎቻቸው ንብረት የሚሆንና ለኦፊስዬል ሥራ የሚውል ፤ |
| ፫/ የተ.መ. UN | ፫/ የተባበሩት መንግሥታት ወይም የቅርንጫፎቹ ንብረት የሆነና ለኦፊስዬል ሥራ የሚውል ። |
| ፬/ ታክሲ (Taxi) | ፬/ የግል ንብረት የሆነና ለኪራይ ወይም ለንግድ ሥራ የሚውል ። |

ለ/ የሚከተሉት ዓይነቶች የፊደል ጣምራ ሠሌዳዎች የተለጠፉባቸው ተሽከርካሪዎች በማይንቀሳቀሱበት ጊዜ መደበኛ መቀመጫቸው የሆነውን ጠቅላይ ግዛት ይገልጻሉ ።

| የፊደል ጣምራዎች ፤ | ትርጉም ፤ |
|---|---|
| ፩/ አሰ/ (አሰላ) | ፩/ አሩሲ ጠቅላይ ግዛት |
| ፪/ ጎባ (ጎባ) | ፪/ ባሌ ጠቅላይ ግዛት |
| ፫/ አሥ (አሥመራ) | ፫/ ኤርትራ ጠቅላይ ግዛት |
| ፬/ ጎን (ጎንደር) | ፬/ በጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት |
| ፭/ አ/ም (አርባ ምንጭ) | ፭/ ገሙ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት |
| ፮/ ደ/ማ (ደብረ ማርቆስ) | ፮/ ጎጃም ጠቅላይ ግዛት |
| ፯/ ሐረ (ሐረር) | ፯/ ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት |
| ፰/ ጎሬ (ጎሬ) | ፰/ ኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት |
| ፱/ ጅማ (ጅማ) | ፱/ ከፋ ጠቅላይ ግዛት |
| ፲/ አ/አ (አዲስ አበባ) | ፲/ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት |
| ፲፩/ አዋ (አዋሳ) | ፲፩/ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት |
| ፲፪/ መቀ (መቀሌ) | ፲፪/ ትግሬ ጠቅላይ ግዛት |
| ፲፫/ ነቀ (ነቀምቴ) | ፲፫/ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት |
| ፲፬/ ደሴ (ደሴ) | ፲፬/ ወሎ ጠቅላይ ግዛት |

፫/ ልዩ ሠሌዳዎች ፤

ሀ/ የዕለት የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚከተለው ይታይባቸዋል ፤

፩/ ቀይ ሠሌዳ ከነጭ ፊደሎችና ቁጥሮች ጋር ፤

፪/ «የዕለት ሠሌዳ» የሚል ጽሑፍ ።

ለ/ ተላላፊ የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳዎች የሚከተለው ይታይባቸዋል ፤

www.chilot.me



በጠቅላላው ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት የሆነና የተሽከርካሪዎች ሊመላለሱበት የሚችሉ ማንኛውም መንገድ ነው ።

፭/ <u>ጠቅላላ መሠረታውያን አሳቦች ፤</u>

፩/ ማናቸውም ሰው ፤ ተሽከርካሪው አደጋን ሳያስከትል ሊነዳ የሚችልበትን ሁናቴ ሁሉ በሚገባ አመዛዝኖ ካልሆነ በቀር ፤ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገድ ላይ ከፍ ባለ ፍጥነት ተሽከርካሪ መንዳት የለበትም ። የተባለው ሁናቴም ፤ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ፤ የሚከተለውን ይጠቀልላል ፤

ሀ/ የመንገዱ ንጣፍ ፤ ስፋትና ጠቅላላ ሁኔታ ፤

ለ/ መንገዱ የሚያልፍበትን መሬት ሁኔታና በዚህ ምክንያት የሚገጥመውን የመንገድ መጠምዘዝና የመንገዱ ስፋት መጠን ፤

ሐ/ የዝናም ፤ የጭጋግ ወይም የሌላ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖርና ይህ ማየትንና መንዳትን እንዴት እንደሚነካ ፤

መ/ በአካባቢው ያለው የነዋሪው ሕዝብ መጠን ፤

ሠ/ ያለው ወይም ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የትራፊክ ብዛት መጠን ፤

ረ/ መዞሪያዎች ፤ የተዘጉ መተላለፊያዎች ፤ የተሰናከሉ ተሽከርካሪዎች ፤ የወደቀ እለትና ሌላም መተላለፍን የሚያውክ መሰናክል መኖሩንና ፤

ሰ/ ነጂው በማንኛውም ጊዜ ተሽከርካሪውን በሙሉ እንዳይቆጣጠርና አደጋን በማያደርስ አኳኋን እንዳይነዳ የሚያውክ ማንኛውም ሁኔታ ።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የአንዳድ ሁናቴ ቢዘረዘርም ፤ ማናቸውም ሰው ፤ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፮ እና ፯ ወይም በአንቀጽ ፰ የተመደበውን የፍጥነት ወሰን በመተላለፍ ባለሞተር ተሽከርካሪን በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ፤ መንገድ ላይ መንዳት የለበትም ።

፫/ ማናቸውም ሰው ፤ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገድ ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪውን በሚነዳበት ጊዜ ፤ ከአደጋ ለመዳን በዝግታ እንዲያሽከርክር አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ፤ የትራፊክን መንቀሳቀስ በማይገባ በሚያግድ ዝግተኛ ፍጥነት መንዳት የለበትም ።

፬/ አደጋ እንዳይደርስ በዝግታ መንዳት አስፈላጊ ሲሆን ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፮ እና ፯ ወይም በአንቀጽ ፰ መሠረት ፤ በዝግታ መንዳት የተመደበ ሲሆን ፤ በአጠገቡ ከሚንቀሳቀስ ትራፊክ ሲነጻጸር በዝግታ የሚነዳና በዚያው አቅጣጫ የሚጓዝ ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ የመንገዱን የቀኝ ጠርዝ ይዞ መሔድ አለበት ።

፮/ <u>ከከተማ ክልል ውጪ በጠቅላላ የሚፈቀድ የፍጥነት ወሰን ፤</u>

ማናቸውም ሰው ፤ ከከተማ ክልል ውጪ ፤

፩/ የግል አቶሞቢል ወይም ሞተር ሳይክል ቀጥሎ ከተመለከተው የፍጥነት መጠን በላይ መንዳት የለበትም ፤

ሀ/ በአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት መቶ (፻) ኪሎ ሜትር ፤

ለ/ በሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት ሰባ (፸) ኪሎ ሜትር ፤

ሐ/ በመጋቢ መንገድና በቀበሌ መጋቢ መንገድ ላይ በሰዓት ስድሳ (፷) ኪሎ ሜትር ፤

www.chilot.me



፪/ ያልተጫነ ሌላ ማንኛውንም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ ትራፊክ በማይበዛበት መንገድ ላይ መንዳት ይችላል ።

ሀ/ ስለሆነም ፤ «ለማጅ» የሚል ምልክት ከተሽከርካሪው በስተኋላ ተለጥፎ በሃምሳ ሜትር (፶) ርቀት ለተከታይ አሽከርካሪ በግልጽ የሚታይ መሆን አለበት ፤ እና

ለ/ ደግሞም ፤ ከለማጁ ጋር አንድ አስተማሪ ወይም አስለማጅ መኖር አለበት ፤ አስተማሪውም ራሱ ፤

፩/ ለሚያስተምርበት ዓይነት ተሽከርካሪ የመንጃ ፈቃድ እንዲኖረው ያስፈልጋል ።

፪/ ተሽከርካሪው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሁሉ ከለማጁ ጐን መቀመጥ አለበት ፤ እና

፫/ ለማጁ ተሽከርካሪውን በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ ለሚያደርሰው ጥፋትና ጉዳት በማይከፋፈል ሁኔታ በአንድነት ከለማጁ ጋር ኃላፊ መሆን አለበት ።

፮/ የመንጃ ፈቃድ ደረጃዎች ፤

የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንጃ ፈቃዶች ከዚህ በታች በተዘረዘረው ዓይነትና ደረጃ ይሰጣሉ ።

፩/ አንደኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ በዚህ ፈቃድ ላይ ፤ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ የሚከተሉትን ለማሽከርከር መቻሉን ማሳየት ያስፈልጋል ።

ሀ/ ማንኛውንም ዓይነት ሞተር ሳይክል ፤ የጐን ተሳቢ ቢኖረውም ባይኖረውም ፤

ለ/ ማንኛውንም ዓይነት ሦስት እግሮች ያሉትና ክብደቱ ሳይጫን ከአራት መቶ (፬፻) ኪሎ ግራም የማይበልጥ ባለሞተር ተሽከርካሪ ፤

፪/ ሁለተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ በዚህ ፈቃድ ላይ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ የሚከተሉትን ለማሽከርከር መቻሉን ማሳየት ያስፈልጋል ።

ሀ/ በሕግ ሊፈቀድ የሚቻለው ከጭነቱ ጋር ጠቅላላ ክብደቱ ከሦስት ሺህ አምስት መቶ (፫ሺ፭፻) ኪሎ ግራም የማይበልጥ ማንኛውም ዓይነት የንግድ ተሽከርካሪ ፤

ለ/ የነጂውን መቀመጫ ጨምሮ ፤ ብዛቱ ከስምንት (፰) የማይበልጥ መቀመጫ ያለውን ማንኛውንም ዓይነት የግል አውቶሞቢል ፤

ሐ/ ከላይ የተመለከቱት የተሽከርካሪ ዓይነቶች ከቀላል ተሳቢ ጋር ፤

፫/ ሦስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ በዚህ ፈቃድ ላይ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ የሚከተሉትን ለማሽከርከር መቻሉን ማሳየት ያስፈልጋል ።

ሀ/ በሁለተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ የሚነዳ ማንኛውም ተሽከርካሪ ።

ለ/ በሕግ ሊፈቀድ የሚቻለው ከጭነቱ ጋር ጠቅላላ ክብደቱ ከሦስት ሺህ አምስት መቶ (፫ሺ፭፻) ኪሎ ግራም እስከ አምስት ሺህ (፭ሺህ) ኪሎ ግራም ድረስ የሆነ ማንኛውንም ዓይነት የንግድ ተሽከርካሪ ፤

ሐ/ የነጂውን መቀመጫ ጨምሮ ፤ ብዛቱ ከስምንት (፰) የማይበልጥ መቀመጫ ያለውን የሕዝብ አገልግሎት ተሽከርካሪ ፤ እና

www.chilot.me



መ/ ከላይ የተመለከቱት የተሽከርካሪ ዓይነቶችና ከቀላል ተሳቢ ጋር ።

፬/ አራተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ በዚህ ፈቃድ ላይ በማንኛውም በንግድ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ የሚከተሉትን ለማሽከርከር መቻሉን ማሳየት ያስፈልጋል ።

ሀ/ በሁለተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድና በሦስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ የሚነዳ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ።

ለ/ በሕግ ሊፈቀድ የሚቻለው ከጭነቱ ጋር ጠቅላላ ክብደቱ ከአምስት ሺህ (፭ሺህ) ኪሎ ግራም በላይ የሆነ ማንኛውንም ዓይነት የንግድ ተሽከርካሪ ፤

ሐ/ የነጂውን መቀመጫ ጨምሮ ፤ ከስምንት (፰) የሚበልጥ መቀመጫ ያለውን ማንኛውንም ዓይነት የሕዝብ አገልግሎት ተሽከርካሪ ፤

መ/ ከላይ የተመለከተውን የተሽከርካሪ ዓይነት ከቀላል ተሳቢ ጋር ።

፭/ አምስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ በዚህ ፈቃድ ላይ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ በሁለተኛ ፤ በሦስተኛ ወይም በአራተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ለማሽከርከር ከተፈቀደ ከማንኛውም ተሽከርካሪ ጋር ቀላል ተሳቢ ያልሆነ ማንኛውንም ዓይነት ተሳቢም ለማሽከርከር መቻሉን ማሳየት ያስፈልጋል ።

፮/ ስድስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ በተለይ በዚህ ፈቃድ ላይ የተገለጹትን የከባድ ሥራ የተሽከርካሪ ዓይነቶችን ለማሽከርከር መቻሉን ማሳየት ያስፈልጋል ።

፯/ ስለአሽከርካሪ ዕድሜና ልምድ ፤

ከዚህ በታች በተዘረዘረው ሁኔታ ለሚገኝ ለማናቸውም ሰው የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ አይሰጥም ።

፩/ ከአሥራ ስድስት (፲፮) ዓመት ዕድሜ በታች ለሆነ ሰው የአንደኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤

፪/ ከአሥራ ስምንት (፲፰) ዓመት ዕድሜ በታች ለሆነ ሰው የሁለተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤

፫/ ከሃያ አንድ (፳፩) ዓመት በታች ለሆነ ወይም በሁለተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ከአንድ (፩) ዓመት ያነሰ የመንዳት ልምድ ላለው ሰው ፤ የሦስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤ እና

፬/ ከሃያ አንድ (፳፩) ዓመት ዕድሜ በታች ለሆነ ወይም በሦስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ከአንድ (፩) ዓመት ያነሰ የመንዳት ልምድ ላለው ሰው ፤ የሚከተሉት ፈቃዶች አይሰጡም ።

ሀ/ ያራተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤

ለ/ አምስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤

ሐ/ ስድስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ፤

www.chilot.me



፰/ ለአካለ መጠን ላልደረሱ ሰዎች ዋስ ስለማስፈለጉ ፤

፩/ አሥራ ስምንት (፲፰) ዓመት ዕድሜ ያልሞላው የአንደኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ጠያቂ ፤ በማመልከቻው ላይ ለአካለ መጠን የደረሰ አንድ ዋስ አብሮት እንዲፈርም ያስፈልጋል ።

፪/ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ተሽከርካሪ በሚነዳበት ጊዜ ለሚያደርሰው ጥፋት ወይም ጉዳት በሕጉ መሠረት ዋሱ ኃላፊ ይሆናል ።

፫/ በዚህ ሁኔታ የተሰጠ ፈቃድ

ሀ/ ዋሱ ሲሞት ወዲያው ይሰረዛል ፤ ወይም

ለ/ ከዋሱ ተጽፎ ቀን የተደረገበትና የተፈረመ የዋስትና ማውረጃ ጽሑፍ ሚኒስቴሩ ሲቀበል ይሰረዛል ። ስለሆነም ፤ ሌላ ዋስ የፈረመበት እንደሆነ በፈቃዱ እንደገና እንዲሠራበት ማድረግ ይቻላል ።

፱/ ስለአሽከርካሪ የችሎታ ፈተና ፤

፩/ ማናቸውም የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ ፤ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩ የፈተና ዓይነቶች በሚገባ ካልታለፉ ለአመልካች አይሰጥም ።

ሀ/ የመንገድ ሥነ ሥርዓት ፈተና ፤ አመልካቹ መጻፍ የሚችል የሆነ እንደሆነ በጽሑፍ ይቀርባል አለዚያም በቃል ይሆናል ። ይህም ፈተና የሚሰጠው ፤ ስለመንገድ ሥነ ሥርዓት ደንቦች ፤ ስለ ልዩ ልዩ የመንገድ ምልክቶችና ማመልከቻዎች ትርጉም ፤ ስለፍጥነት ወሰንና በቀዋሚ ሕግ ወይም ደንቦች መሠረት ተሽከርካሪዎችን በመንገዶች ላይ ያለ ሥጋት ስለማመላለስ ስለወጣው ስለማንኛውም ደንብ ያለውን እውቀት ለማረጋገጥ ነው ።

ለ/ የመንዳት ችሎታ ፈተና ፤ መንጃ ፈቃድ ሊሰጥበት የቀረበውን ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ በሚገባና አደጋን በማያስከትል ችሎታ ለመንዳትና ለማንቀሳቀስ መቻሉን ለማረጋገጥ የተባለውን ተሽከርካሪ መንዳት መቻሉን ለፈታኙ ሹሙ ማሳየት ፤ ፈታኝ ሹሙም የሚከተሉትን ተመልክቶ ማስታወሻ መያዝ አለበት ።

፩/ አመልካቹ ሁልጊዜ ተሽከርካሪውን ለመቆጣጠር ያለውን ችሎታ ፤

፪/ ተሽከርካሪውን በሚገባና በልበ ሙሉነት ለማንቀሳቀስ አመልካቹ ያለውን ችሎታ ፤

፫/ አመልካቹ አስፈላጊ የሆኑ የመንገድ ሥነ ሥርዓት ደንቦችን ፡ የመንገድ ምልክቶችን ሁሉና የፍጥነትን ወሰን በጥንቃቄ ማክበሩን ።

፪/ መንጃ ፈቃድ ለተጠየቀለት ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ ፤ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ፤ አመልካቹ መንጃ ፈቃድ የነበረው የሆነ እንደሆነ ፈቃድ ሰጪው ሹም ከላይ የተመለከቱትን ሁለት የፈተና ዓይነቶች መስጠት የለበትም ።

፫/ አመልካቹ የውጭ አገር መንጃ ፈቃድ ወይም እንተርናስዮናል መንጃ ፈቃድ ያለው የሆነ እንደሆነ ፤ ፈቃድ ሰጪው ሹም ከላይ የተመለከቱትን ሁለት የፈተና ዓይነቶች መስጠት የለበትም ፤ ስለሆነም ፤ ሚኒስትሩ እንደሚወስነው ፤ ፈቃዱን የሰጠው የውጭ አገር ተመሳሳይ መብት ለኢትዮጵያ ሰጥቶ እንደሆነ ነው ።

፬/ ለሚሰጠው ለያንዳንዱ ፈተና አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» የተመለከተውን የአገልግሎት ዋጋ መክፈል አለበት ።

www.chilot.me



፭/ አመልካቹ የሚፈለግበትን የፈተና ዓይነት ከፈጸመና የተመደበውን ያገልግሎት ዋጋ ከከፈለ በኋላ ፤ አመልካቹ ባቀረበው ባለሞተር ተሽከርካሪ ዓይነት ባሳየው የመንዳት ችሎታ ውጤት መሠረት ፈቃድ ሰጭው ሹም የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ።

፲/ ስለአሽከርካሪ የጤንነት ግዴታ ፤

ፈቃድ ሰጪው ሹም የአመልካቹ የሰውነት ጉንካሬ ፤ የማየት ፤ የመስማት ችሎታ ውና ጠቅላላው የጤንነቱ ሁኔታ አጥጋቢ ሆኖ ካላታየው ፤ ለማናቸውም የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በዚህ ደንብ መሠረት መንጃ ፈቃድ አይሰጥም ወይም አያድስም ።

፩/ የመጀመሪያ መንጃ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ሲቀርብ ፤ ፈቃድ ሰጪው ሹም አመልካቹ ከመንግሥት ሐኪም ዘንድ ሄዶ ጠቅላላ የጤንነት ምርመራ እንዲደረግ ለት ያዝዛል ።

፪/ ከዚያም በኋላ መንጃ ፈቃድ በሚታደስበት ጊዜ ፤ ፈቃድ ሰጪው ሹም ማንኛውም የአካል በሽታ ፤ የችሎታ ማነስ ፤ የእክል ወይም ሌላ ያለአደጋ አንድን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማንቀሳቀስ የሚያውክ ማንኛውም ዓይነት ሌላ ምክንያት መኖሩን የጠረጠረ እንደሆነ ፤ የሚከተሉትን ማዘዝ አለበት ።

ሀ/ የዓይን ምርመራ ፤

ለ/ የጆሮ ምርመራ ፤

ሐ/ ሌላ ማንኛውም ተገቢ ምርመራ እና ወይም

መ/ ጠቅላላ የጤንነት ምርመራ ፤

እንደ አስፈላጊነቱ የመንግሥት ሐኪም ለአመልካቹ እንዲያደርግ ።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚታዘዘው ለያንዳንዱ ምርመራ የመንግሥት ሐኪሙ ውጤቱን (ሪፖርቱን) (ሚኒስቴሩ በመደበው ቅጽ) ፎርም ሞልቶ ያስታውቃል ።

፬/ አመልካቹ የአሽከርካሪ ፈቃድ ለማግኘት ብቁ መሆኑ ወይም አለመሆኑ በምን ዓይነት ልዩ ሁኔታ ወይም ገደብ ፈቃድ ሊሰጠው እንደሚገባ የመንግሥት ሐኪሙ የሚሰጠው ውሳኔ መጨረሻ ውሳኔ ይሆናል ።

፲፩/ ለመንጃ ፈቃድ ማመልከቻ ስለማቅረብ ፤

፩/ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርበውን ማመልከቻ ሁሉ ሚኒስቴሩ በመደበው ቅጽ (ፎርም) ሞልቶ አመልካቹ ራሱ ለፈቃድ ሰጪው ሹም ያቀርባል ። አመልካቹ መጻፍ የሚችል እንደሆነ በፎርሙ ላይ የተጠየቁትን ጉዳዮች በራሱ እጅ ጽሕፈት ይሞላል ።

፪/ እያንዳንዱ አመልካች የሚያቀርበው ማመልከቻ ማናቸውም ፈታኝ ሹም ወይም የተፈቀደለት ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ተፈላጊ የሆነውን ምርመራና ፈተና አመልካቹ በሚገባ ማለፉን ካረጋገጠበት የምስክር ወረቀት ሁሉ ጋር ይቀርባል ።

፲፪/ መንጃ ፈቃድ ስለመስጠት ፤

፩/ አመልካቹ ማመልከቻውን በሚገባ አጠናቅቆ ከተፈላጊው የምስክር ወረቀት ሁሉ ጋር ሲያቀርብና ከዚህ ደንብ ጋር በተያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት ተገቢውን የአገልግሎት ዋጋ ሲከፍል ፤ ፈቃድ ሰጭው ሹም አስፈላጊ መስሎ የታየውን ወሰን ወይም ገደብ መንጃ ፈቃዱ ላይ አመልክቶ ፤ ከሚኒስቴሩ በተመደበው ቅጽ (ፎርም) የተጠየቀውን ዓይነት መንጃ ፈቃድ ይሰጠዋል ።

www.chilot.me



፪/ በያንዳንዱ መንጃ ፈቃድ ላይ የተፈቀደለት ሰው ፎቶግራፍ ይለጠፋል ፤ የሚኒስቴሩም አፊስዬል ማኅተም በፎቶግራፉ ላይ ይታተማል ።

፫/ በያንዳንዱ መንጃ ፈቃድ ላይ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጽሕፈት ወይም የአውራ ጣት ፊርማ ይደረጋል ።

፲፫/ <u>ስለመንጃ ፈቃድ አያያዝና አጠባበቅ ፤</u>

፩/ ማናቸውም ሰው በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገዶች ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪውን በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ ሁሉ ደንበኛ የመንጃ ፈቃዱን ይዞ መገኘት አለበት ። ደንበኛ መንጃ ፈቃድ በእጅ ሳይኖር ለማናቸውም ሰው ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት አይፈቀድም ።

፪/ በመንጃ ፈቃድ ላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ውስጥ ስሕተት መኖሩን ወይም እርማት ማስፈለጉን ባወቀ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ መንጃ ፈቃድ የያዘ ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከትና መንጃ ፈቃዱ እንዲተካከል ማቅረብ አለበት ፤ ስሕተቱ ወይም የሚያስፈልገው እርማት የተደረገው በሚኒስቴሩ ስሕተት ፤ አለመጠንቀቅ ወይም ዝንጋታ ብቻ ካልሆነ ፤ ፈቃዱን የያዘው ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» ለማስተካከያ የተመደበውን የአገልግሎት ዋጋ ይከፍላል ።

፫/ (በመንጃ ፈቃድ ላይ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚለወጥ መኖሩን ባወቀ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ፤ መንጃ ፈቃድ የያዘ ሰው ስለሚፈለገው ለውጥ ለሚኒስቴሩ አመልክቶ ፤ መንጃ ፈቃዱንም አቅርቦ ዝርዝር ጉዳዩ እንዲሠረዝና) ወይም እንዲተካከል ማስደረግ አለበት ፤ በተጨማሪም ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» የተመለከተውን ለዝርዝር ጉዳዮች ለውጥ የሚከፈለውን የአገልግሎት ዋጋ መክፈል አለበት ።

፬/ ሀ/ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የመንጃ ፈቃድ የጠፋ ፤ የተሰረቀ ፤ የተቀደደ ወይም የተበላሸ ፤ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ ፤ መንጃ ፈቃዱን የያዘ ሰው ወዲያው ቅጂው እንዲሰጠው ማመልከቻ ማቅረብ አለበት ።

ለ/ የሚፈለገውን መረጃ ለሚኒስቴሩ ካቀረበና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» መሠረት የተመደበውን ገንዘብ ከከፈለ በኋላ ፤ በላዩ ላይ «ይህ ቅጅ ነው» የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት የፈቃድ ግልባጭ ይሰጠዋል ።

ሐ/ የፈቃድ ቅጅ የተሰጠበትን ዋናውን መንጃ ፈቃድ ያገኘ ሰው ቅጂውን ወዲያው ለሚኒስቴሩ አቅርቦ እንዲሠረዝ ወይም እንዲቀደድ ያደርጋል ።

፲፬/ <u>መንጃ ፈቃድ ስለሚረጋበት ጊዜና ስለማደስ ፤</u>

፩/ እያንዳንዱ የመንጃ ፈቃድ ደረጃ የሚረጋው ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ ለሁለት (፪) ዓመት ጊዜ ነው ፤ በተጨማሪም ለሁለት (፪) ዓመት ጊዜ ሊታደስ ይችላል ።

፪/ ባለመንጃ ፈቃድ ፈቃዱን ለፈቃድ ሰጪው ሹም በማቅረብ ሊያሳድስ ይችላል ።

፫/ አመልካቹ መንጃ ፈቃዱን አቅርቦ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «ሀ» የተመደበውን ገንዘብ ከከፈለና አስፈላጊውን ምርመራ ማለፉ ከተረጋገጠ በኋላ ፤ ፈቃድ ሰጪው ሹም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ አንድ (፩) ለተመደበው ጊዜ መንጃ ፈቃዱን ያድሳል ።

፲፭/ <u>ስለመንጃ ፈቃድ ሰጪው ሹም ሥልጣን ፤</u>

፩/ ሀ/ ማናቸውም ሰው ከበሽታ ወይም ከስንኩልነት የተነሣ አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳቱ ለሕዝብ አደጋን የሚያስከትል መስሎ ሲታየው ፤ ፈቃድ ሰጪው

www.chilot.me



ሀ/ መንጃ ፈቃዱ ቀኑ ያላለፈበት መሆኑን ፤

ለ/ መንጃ ፈቃዱን ያቀረበው በእርግጥ መንጃ ፈቃድ የተሰጠው ሰው መሆኑን ፤

ሐ/ ሚኒስትሩ እንደሚወስነው የውጪ አገር መንግሥት የኢትዮጵያ ዜጎች በአገሩ ውስጥ በጉብኝት ሆነ ለጊዜው በሚቆዩበት ጊዜ የያዙትን የኢትዮጵያ መንጃ ፈቃድ እውቆ ያከብር እንደሆነ ፤

፫/ በዚህ አኳኋን የተፈቀደ የውጪ አገር መንጃ ፈቃድ ወይም ዋጋ ያለው እንተርናሽናል መንጃ ፈቃድ የያዘ ሰው ፤ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንገድ ላይ ፈቃድ የተሰጠበትን የተሽከርካሪ ዓይነት ወይም ዓይነቶች ከዚህ ለሚከተለው ጊዜ ለማሽከርከር ይችላል ።

ሀ/ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ከገባበት ቀን አንሥቶ እስከ ዘጠና (፺) ቀን ድረስ ወይም ፤

ለ/ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን እስካለቀበት ድረስ ፤ ከሁለቱ ቀድሞ እስከሚደርሰው ቀን ድረስ ።

፬/ ከላይ የተመለከተው ጊዜ ሲፈጸም ፤ የተባለው ሰው ማመልከቻ አቅርቦ በዚህ ደንብ በተመደበው መሠረት ተፈላጊውን መንጃ ፈቃድ መቀበል አለበት ።

፲፰/ <u>ስለወታደር መንጃ ፈቃድ ፤</u>

፩/ የወታደር መለያ ቁጥር ሠሌዳዎች በሚገባ የተደረጉባቸውን የወታደር ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ለመንዳት በጦር ኃይሎች ውስጥ ለሚያገለግሉ ሠራተኞች የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ መስጠት ፤ ማደስ ፤ መሠረዝና ማገድ በዚህ ደንብ ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ተፈቅዶለታል ፤ ሥልጣንም ተሰጥቶታል ።

ሀ/ ስለሆነም ፤ የተባለውን መንጃ ፈቃድ የመስጠትን ጉዳይ እንዲያከናውኑ የተመደቡ ያገር መከላከያ ሚኒስቴር ሠራተኞች በጠቅላላው በዚህ ደንብ እንዲፈጸም የተወሰነውን አሠራርና ግዴታ ሁሉ መጠበቅና ማስፈጸም አለባቸው ።

ለ/ የመገናኛ ሚኒስትሩ ፤ ይህ ደንብ በሙሉ መጠበቁን ለማረጋገጥ ስለተባለው መንጃ ፈቃድ የመስጠት ጉዳይ ያገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚሠራውንና ሠነዶቹን በማንኛውም ጊዜና በየጊዜው ለመመርመርና ለመመልከት መብት አለው ፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ፲፰ መሠረት በሚሰጥ በማንኛውም የወታደር መንጃ ፈቃድ ላይ «ለኦፊስዩል የወታደር ጉዳይ ብቻ» የሚሉ ቃላት መጻፍ አለባቸው ።

፪/ ሀ/ በዚህ አንቀጽ ፲፰ መሠረት ፤ ካገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚሰጡ የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንጃ ፈቃዶች የሚጸኑት የወታደር መለያ ቁጥር ሠሌዳዎች በሚገባ የተደረጉባቸውን የወታደር ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ለመንዳት ብቻ ነው ።

ለ/ የወታደር መንጃ ፈቃድ ያለው ሰው ፤ የወታደር መለያ ቁጥር ሠሌዳዎች ያልተደረጉበትን ማንኛውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት ፤ ተገቢውን ደረጃ የሲቪል መንጃ ፈቃድ ከመገናኛ ሚኒስቴር መቀበል አለበት ።

፲፱/ <u>መሸጋገሪያ ውሳኔ ፤</u>

፩/ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ከሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ ስም የተሰጡ የባለሞተር ተሽከርካሪ መንጃ ፈቃዶች ሁሉ በዚህ ደንብ መሠረት እንደተሰጡ ተቆጥረው የጸኑ ይሆናሉ ።

www.chilot.me



፪/ ስለሆነም ፤ እነዚህ መንጃ ፈቃዶች ፤

ሀ/ በመንጃ ፈቃዶቹ ላይ የተመለከተው ቀን ሲያልፍ ወይም

ለ/ ይህ ደንብ ከጸና በኋላ ሁለት (፪) ዓመት ሲያልፍ ፤ ከሁለቱ ቀድሞ በሚደር ሰው ጊዜ ዋጋ የሌላቸው ይሆናሉ ።

፫/ የተባለው ፈቃድ የተሰጠበት ቀን ሲያልፍ ፤ ፈቃዱን የያዘው ሰው ፈቃዱን ለፈቃድ ሰጪው ሹም ማቅረብ አለበት ። ፈቃድ ሰጪው ሹምም ይህን አድራጎት ፈቃዱን ለማሳደስ እንደቀረበ ተያቄ ቆጥሮ በሠንጠረዥ «ለ» መሠረት የተመለከተውን የመንጃ ፈቃድ ወይም የመንጃ ፈቃድ ደረጃ በቀድሞ በመለወጥ መስጠት አለበት ።

፳/ ይህን ደንብ ስለመተላለፍ ፤

በዚህ ደንብ የተመደበውን ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጠውን ማንኛውንም ሕጋዊ ትእዛዝ የሚተላለፍ ማናቸውም ሰው ፤ እንደ ደንብ ተላላፊ ተቆጥሮ በዋናው አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሠረት ይከሰሳል ፤ ጥፋተኛነቱም ሲረጋገጥ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ መሠረት ይቀጣል ።

የተጠቀሰው ሕግ

እዚህ የተጠቀሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጾች የወ.መ.ሕ. ፲፯/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፶፱) አን. ፫፻፺፬ ፤ ፫፻፳፬ ፤ ፬፻፶፱—፭፻፪ ፤ ፯፻፵፯ ፤ ፯፻፹፪ ፤ ፯፻፹፫ እንደሆኑ ይገመታል ።

፳፩/ ይህ ደንብ ስለሚጸናበት ጊዜ ፤

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

ሠንጠረዥ «ሀ»

የአገልግሎት ዋጋ

| | | የኢት/ብር |
|---|---|---|
| ፩/ | ለችሎታ ፈተና ፤ | |
| | ሀ/ የመንገድ ሥነ ሥርዓት ፈተና | 2 |
| | ለ/ የመንዳት ችሎታ ፈተና | |
| | ፩/ አንደኛ ደረጃ | 1 |
| | ፪/ ሁለተኛ ደረጃ | 2 |
| | ፫/ ሦስተኛ ደረጃ | 5 |
| | ፬/ አራተኛ ደረጃ | 5 |
| | ፭/ አምስተኛ ደረጃ | 7 |
| | ፮/ ስድስተኛ ደረጃ | 7 |
| ፪/ | የመንጃ ፈቃድ ሲሰጥ ወይም ሲታደስ ፤ | |
| | ሀ/ አንደኛ ደረጃ | 10 |
| | ለ/ ሁለተኛ ደረጃ | 15 |

www.chilot.me



| | የኢት/ብር |
|---|---|
| ሐ/ ሦስተኛ ደረጃ | 20 |
| መ/ አራተኛ ደረጃ | 20 |
| ሠ/ አምስተኛ ደረጃ | 25 |
| ረ/ ስድስተኛ ደረጃ | 25 |

፫/ ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ ፤

ለያንዳንዱ ጉዳይ ፤ 1

፬/ ለመንጃ ፈቃድ ግልባጭ / ቅጂ ፤ 10

## ሠንጠረዥ «ለ»

## የቀድሞውንና የአሁኑን መንጃ ፈቃድ ደረጃ ስለማነጻጸር

| የቀድሞ መንጃ ፈቃድ ደረጃ ፤ | የአሁኑ መንጃ ፈቃድ ደረጃ ፤ |
|---|---|
| አንደኛ ደረጃ ፤ | ሁለተኛ ደረጃ ፤ |
| ሁለተኛ ደረጃ ፤ | ሦስተኛ ደረጃ ፤ |
| ሦስተኛ ደረጃ ፤ | አራተኛ ደረጃ ፤ |
| ሦስተኛ ደረጃ ከነተሳቢው ፤ | አምስተኛ ደረጃ ፤ |

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፱ መሠረት የመንጃ ፈቃድ ለውጥ የሚሰጠው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ነው ።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም

## ፳፰/፲ (፲፱፻፷፩) ሕ. ፫፻፷፫

## በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ።

፩/ አውጪው ባለሥልጣን ፤

ይህን ደንብ በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ (ከዚህ በታች «ዋናው አዋጅ» እየተባለ በሚጠቀሰው) ቁጥር ፪፻፶፮/፲፱፻፶፰ ዓ.ም. አንቀጽ ፭ እና ፳፫ ፤ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመገናኛ ሚኒስትር (ከዚህ በታች «ሚኒስትሩ» እየተባለ የሚጠቀሰው) ያወጣው ነው ።

፪/ አጭር አርእስት ፤

ይህ ደንብ «የ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. በመንገዶች ላይ ጉዞን የመቆጣጠር ሥልጣን ውክልና ደንብ » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

www.chilot.me



፯/ ውክልና ስለመመርመርና መሰረዝ ፤

፩/ ይህ ደንብና የተሰጠው ውክልና በሚገባ በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ፤ ሚኒስትሩ ተገቢ መስሎ በታየው በማንኛውም ጊዜና በየጊዜው ይህን ጉዳይ የሚመለከተውን የማንኛውንም የተወከለ ማዘጋጃ ቤት የአስተዳደር አመራርና ሥነዶች ይመረምራል ፤ አሠራሩንም ይመለከታል ።

፪/ ሀ/ የተወከለ ማዘጋጃ ቤት የተወከለበትን ሥራ ሲፈጽም ከባድ ጉድለት ማድረጉን ሲረዳ ፤ ሚኒስትሩ ጉድለቱን ለማሟላት ማድረግ የሚገባውንና ወደፊት ጉድለቱ እንዳይደገም መውሰድ ያለበትን እርምጃ ለተባለው ማዘጋጃ ቤት ያስታውቃል ።

ለ/ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ጉድለቱን ለማስወገድ እርምጃ ያልተወሰደ እንደሆነ ፤ ሚኒስትሩ አስፈላጊ መስሎ እንደሚታየው ለተወከለው ማዘጋጃ ቤት ፤

፩/ የቀድሞውን ውክልና በሙሉ የሚሰርዝ ደብዳቤ ይሰጣል ፤ ወይም ፤

፪/ ቀድሞ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በከፊል የሚቀንሰውን ዝርዝር በደብዳቤ ይሰጣል ።

ውክልናው የሚሰረዘው ማስታወቂያው በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከሠላሳ (፴) ቀን በኋላ ነው ። በሠላሳው ቀን ውስጥ የተወከለው ማዘጋጃ ቤት የተሰረዘውን ሥልጣንና ተግባር የሚመለከት ማንኛውንም ማመልከቻ መቀበል ወይም መፈጸም አይችልም ።

፰/ ስለሚቋቋሙ የማዘጋጃ ቤት የሥራ ክፍሎች ፤

የተወከሉ ማዘጋጃ ቤቶች የተወከሉበትን ሥልጣንና ተግባር በሚያከናውኑበትና በሚፈጽሙበት ጊዜ እያንዳንዳቸው ለሥራው የሚያስፈልገውን የተለየ የሥራ ክፍል አቋቁመው በአንድ ኃላፊ ሹም አማካይነት ያካሂዳሉ ።

ሹሙም ፤

፩/ በጠቅላላ በውክልና የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ለመዋሉና ለመፈጸሙ ፤ በጠቅላላውም ለአስተዳደሩ ኃላፊ ነው ።

፪/ ሚኒስትሩ በውክልናው ላይ የሚያደርገውን ልዩ ተፈላጊ ጉዳይና ገደብ በመከተል ፤ በዚህ ደንብ መሠረት ጠቅላላ ደንቦቹን ከሥራ ላይ ለማዋልና ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፫/ በጠቅላላ ደንቦቹ ውስጥ በተመለከተውና ሚኒስትሩ በውክልናው ላይ ባደረገው ገደብ መሠረት የምዝገባ ሹምና የመንጃ ፈቃድ ሰጪ ሹም ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል ።

፱/ ስለማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች የችሎታ መጠን ፤

በውክልና የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሚያከናውኑበትና በሚያስፈጽሙበት ጊዜ ፤ የተወከሉ ማዘጋጃ ቤቶች ፤ በአንቀጽ ፰ መሠረት የሚሾም ፤ ወይም የሚመደብ ሹም ፤

፩/ በሚቻል መጠን ከሚከተሉት ሕጎችና ደንቦች የተለማመደና የሚያበተውላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው ፤

ሀ/ ፩/ ዋናውን አዋጅ ፤

፪/ ጠቅላላ ደንቦቹን ፤

www.chilot.me



፫/ ይህን ደንብ እና፤

፬/ ሌሎችን ስለተሽከርካሪ አሠራር፤ ስለዕቃና መጫሪያ፤ ስለመጠንና ክብደት፤ ስለትራፊክ ሕጎችና ደንቦች፤ ስለትራፊክ ምልክቶችና ማመልከቻዎች ትርጉም፤ ስለፍጥነት ወሰንና ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን በመንገድ ላይ አደጋን በማያስከትል አኳኋን ለማመላለስ ስለወጡ ሌሎች ደንቦች።

ለ/ በማዘጋጃ ቤቱ ክልል ውስጥ ባሉ መንገዶች ላይ ትራፊክ ከአደጋ የሚጠበቅበትን ሁኔታ በሚገባ ማወቅና መረዳት፤

፪/ ተሽከርካሪ በመመዝገብና በመመርመር ጉዳይ የተባለውን ሹም ከሚረዱ መርማሪዎች ሁሉ የሚከተለው የችሎታ መጠን ይፈለግባቸዋል፤

ሀ/ ስለተሽከርካሪ አሠራር፤ ስለዕቃና መጫሪያ፤ ስለመጠንና ክብደት የወጡትን ሕጎችና ደንቦች በሚገባ ማወቅ፤

ለ/ የባለሞተር ተሽከርካሪ መካኒስያን ተገቢ ትምህርት ወይም ልምድ፤

፫/ የመንጃ ፈቃድ በመስጠት የተባለውን ሹም የሚረዱ ፈታኝ ሹሞች ሁሉ የሚከተለው የችሎታ መጠን ይፈለግባቸዋል።

ሀ/ ስለትራፊክ ሕጎችና ደንቦች፤ ስለትራፊክ ምልክቶችና ማመልከቻዎች ትርጉም፤ ስለፍጥነት ወሰንና ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን በመንገድ ላይ አደጋን በማያስከትል አኳኋን ለማመላለስ ስለወጡ ስለሌሎች ደንቦች ሁሉ በሚገባ ማወቅ፤

ለ/ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን በሚገባ የመንዳትና የማመላለስ ልምድ፤ ቢያንስም የአራተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃድ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

፲/ <u>ስለሠነዶች፤</u>

የተወከለ ማዘጋጃ ቤት የተቀበላቸውን የማመልከቻዎች፤ የቅጾች (ፎርሞችና) የሌሎች ሠነዶች ግልባጮች ሁሉ እንዲሁም የተወከለ ማዘጋጃ ቤቱ የሰጣቸውን የምስክር ወረቀቶች፤ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሮች፤ የመለያ ቁጥሮች፤ የምዝገባ ካርዶችና የመንጃ ፈቃዶች መግለጫዎች ሁሉ በኦፊስዬል መዝገብ ውስጥ እንዲሠፍሩና ከኦፊስዬል ሠነዶች ጋር እንዲቀመጡ ሚኒስትሩ በሚወስነው አኳኋን ባለማቋረጥ ለሚኒስቴሩ መላክ አለበት።

፲፩/ <u>ባለንብረትነትን ለጊዜው ስለማወቅ፤</u>

በጠቅላላ ደንቡ መሠረት ባለንብረትነትን ስለማወቅ የሚቀርብ ማመልከቻ ሚኒስቴሩ ከሚይዘው ኦፊስዬል መዝገብ፤ ሠነዶችና/ወይም ዝርዝሮች ጋር እንዲገናዘብ በሚያስፈልግበት ጊዜ፤

፩/ የተወከለ ማዘጋጃ ቤቱ ማመልከቻው እንደቀረበለት ትክክለኛውን ግልባጭ በተቻለ ፍጥነት ለሚኒስቴሩ ይልካል፤

፪/ የተባለው ግልባጭ እንደደረሰው፤ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን ይፈጽማል፤

ሀ/ በግልባጩ የተመለከቱትን ዝርዝር ጉዳዮች ከደንበኛው መዝገብ፤ ሠነዶችና ወይም ዝርዝሮች ጋር ማገናዘብ፤

ለ/ በተባለው ግልባጭ ላይ «የተፈቀደ» ወይም «ያልተፈቀደ» ብሎ ምልክት ማድረግ፤ ያልተፈቀደ እንደሆነም ምክንያቱን መግለጽ፤

ሐ/ የሚኒስቴሩን ማኅተም በላዩ ማተም፤

www.chilot.me



መ/ ለላኪው የተወከለ ማዘጋጃ ቤት ግልባጩን መልሶ መላክ፤

፫/ ከላይ የተመለከተው ማገናዘቢያ በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ማመልከቻው የተፈቀደ መሆኑ ከሚኒስቴሩ እስኪታወቅ ድረስ፣ የተወከለ ማዘጋጃ ቤቱ ሊሰጥ የሚችለው፣ በጉልህ የሚታይ «ጊዜያዊ» የሚል ቃል የተጻፈበት የባለንብረትነት መታወቂያ ብቻ ነው። የዚህ ዓይነት መታወቂያ የተሰጠው አላገባብ መሆኑ እንዲተረጋገጠ በስድሳ (፷) ቀን ውስጥ ይሰረዛል።

፲፬/ ስለገቢ ገንዘብ፤

፩/ በጠቅላላው ደንቡቹ መሠረት፤ ሠነዶችን ለማግኘት ወይም ለማሳደስ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ሁሉ ለምን ያህል ጊዜ ተሽከርካሪው በአቅራቢያው ባለው ማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥና ውጪ እንዲሠራ መታሰቡን ይገልጻሉ፤ ወይም ይህንኑ የሚገልጽ ጽሑፍ በአባሪነት ይቀርባል። የሚቀርበው መግለጫ፤

ሀ/ ስለ ባለንብረትነት መታወቂያ ወይም ምዝገባ የሆነ እንደሆነ፣ ተሽከርካሪው በማይንቀሳቀስበት ጊዜ የሚቀመጥበትን መደበኛ ቦታ መግለጽ ይኖርበታል፤

ለ/ ስለመንጃ ፈቃድ የሆነ እንደሆነም፣ አመልካቹ የሚኖርበትና/ወይም የሚሠራበት ቦታ መገለጽ አለበት።

፪/ ከተሽከርካሪው የሥራ ጊዜ ከመቶ ሃምሳው (50%) ወይም ከመቶ ሃምሳ (50%) በላይ የሚሆነው በርግጥ የሚያልፈው በማዘጋጃ ቤቱ ክልል ውስጥ የሆነ እንደሆነ፣ ሠነዱን ለማግኘት ወይም ለማሳደስ የሚከፈለው ገንዘብ እንደሚከተለው ይከፋፈላል።

ሀ/ ከመቶ ሰባ አምስቱ (75%) ለተወከለ ማዘጋጃ ቤቱ ይመደባል፤

ለ/ ከመቶ ሃያ አምስቱም (25%) ለሚኒስቴሩ ይመደባል።

፫/ ከተሽከርካሪው የሥራ ጊዜ ከመቶ ሃምሳ (50%) በላይ የሚሆነው በርግጥ የሚያልፈው ከማዘጋጃ ቤቱ ክልል ውጪ የሆነ እንደሆነ ሠነዱን ለማግኘት፤ ወይም ለማሳደስ የሚከፈለው ገንዘብ እንደሚከተለው ይከፋፈላል፤

ሀ/ ከመቶ ሰባ አምስቱ (75%) ለሚኒስቴሩ ይመደባል፤

ለ/ ከመቶ ሃያ አምስቱ (25%) ለተወከለ ማዘጋጃ ቤቱ ይመደባል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጾች የተመለከቱት ሳይታሰቡ፤ አንዳንድ የአስተዳደር ሥራን የሚያከናውን ባለሥልጣን፣ ሚኒስቴሩም ቢሆን ወይም የተወከለ ማዘጋጃ ቤቱ፣ ለዚያ የሚከፈለውን የአገልግሎት ዋጋ ሁሉ ማስቀረት ይችላል።

፲፭/ ስለሒሳብ አያያዝ፤

፩/ የሚኒስቴሩና የተወከሉ ማዘጋጃ ቤቶቹ የሥራ ክፍሎች የተሟላና የተጠናቀቀ ሒሳብ መያዝ አለባቸው፤

፪/ ይህን ጉዳይ የሚመለከቱ የያንዳንዱ የተወከለ ማዘጋጃ ቤት የሒሳብ መዝገቦችና ሠነዶች ለሚኒስቴሩ ምርመራ ክፍት መሆን አለባቸው።

፲፮/ መሸጋገሪያ ውሳኔ፤

ስለባለሞተር ተሽከርካሪዎችና ተሳቢዎች የባለንብረትነት መታወቂያ፣ መለያ፣ መመዝገቢያና/ወይም መመርመሪያና/ወይም ስለባለሞተር ተሽከርካሪዎች መንጃ ፈቃድ እስካሁን ስለሚኒስቴሩ ሆኖ ወይም ተወክሎ የሚሠራ ማንኛውም ማዘጋጃ ቤት ወይም ከተማ፣ ይህ ደንብ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት (፮) ወር ድረስ የቀድሞ ሥራውን ወይም ውክልናውን መቀጠል ይችላል።

www.chilot.me



፲፭/ ይህ ደንብ ስለሚጸናበት ቀን ፤

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

ሠንጠረዥ ።

በዚህ ደንብ መሠረት የተመደቡ ማዘጋጃ ቤቶች የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ አዲስ አበባ ፤
፪/ አሥመራ ፤
፫/ አርባ ምንጭ ፤
፬/ አሰላ ፤
፭/ አዋሳ ፤
፮/ ደብረ ማርቆስ ፤
፯/ ደሴ ፤
፰/ ጐባ ፤
፱/ ጐንደር ፤
፲/ ጐሬ ፤
፲፩/ ሐረር ፤
፲፪/ ጅማ ፤
፲፫/ መቀሌ ፤
፲፬/ ነቀምቴ ፤

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም.

፳፰/፳፩ (፲፱፻፳፩) ሕ. ፫፻፫

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ።

፩/ አውጪው ባለሥልጣን ፤

ይህን ደንብ የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) አስተዳደር ያወጣው በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ (አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፮/ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም.) ከዚህ በታች «አዋጁ» እየተባለ የሚጠቀሰው በአንቀጽ ፲ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው ።

፪/ አጭር አርእስት ፤

ይህ ደንብ «የ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. የንግድ ተሽከርካሪ ልዩ ምዝገባ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፫/ ትርጉም ፤

በዚህ ደንብ ውስጥ ያሉ ቃላት ትርጉም በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው ፤ የሚከተሉት ቃላትም እንደሚከተለው ይተረጐማሉ ።

፩/ «የንግድ ተሽከርካሪ ልዩ ምዝገባ » ወይም ባጭሩ «ልዩ ምዝገባ» ሲባል የግል ወይም የሕዝብ የንግድ ማመላለሻ የሚሠራ የማንኛውም ተሽከርካሪ ባለንብረት ፤ በአዋጁ አንቀጽ ፯ (፪) እና ፲ (፪) ( በ) መሠረት ፤ ከአስተዳደሩ በልዩ መመዝገብና ፈቃድ መቀበል ማለት ነው ።

www.chilot.me



፪/ «የተገጠመ ተሽከርካሪ» ሲባል ራሱ ጭነት የማይዝ ጐታች መኪና ሆኖ ግማሽ ተሳቢን የሚጐትት ማንኛውም ተሽከርካሪ ማለት ነው ።

፫/ «መለያ ምልክት» ማለት በተፈቀደው አኳኋን ባንድ ተሽከርካሪ ላይ በሚገባ በመደረግ የተሽከርካሪው ባለንብረት ተሽከርካሪውን በልዩ ያስመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ ተለጣፊ ምልክት ነው ።

፱/ <u>የንግድ ተሽከርካሪ ልዩ ምዝገባ ስለሚፈልጉ ፤</u>

በግል ወይም በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ውስጥ የሚሠራ የማንኛውም ተሽከርካሪ ባለንብረት በዚህ ደንብ መሠረት የልዩ ምዝገባ ማስረጃ ማግኘት ፤ በየዓመቱ ማሳደስ አለበት ። ነገር ግን የተባለው ተሽከርካሪ ከሥራው የሚበዛውን ክፍል የሚያከና ውነው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው «ሠንጠረዥ» በተጠቀሰው የማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ አይሆንም ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

የዚህ] አንቀጽ የእንግሊዝኛው እትም «ከዚህ ጋር በተያያዘው (ሠንጠረዥ ለ)» ይላል ።

፲/ <u>ስለሥነ ሥርዓት ፤</u>

፩/ ለልዩ ምዝገባ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ፤ የማሳደሻና የማሻሻያ ማመልከቻዎችም አስተዳደሩ በሚያዘጋጀው ቅጽ (ፎርም) ላይ በተጠየቀው መሠረት የሚፈለገውን መረጃ ሁሉ መግለጽ አለባቸው ። በተጨማሪም የሚከተሉትን ይገልጻሉ ።

ሀ/ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የሆነ እንደሆነ ፤

፩/ ሊሠራበት ያቀደውን መሥመር ወይም መሥመሮችና በወር ስንት ቀን ተሽከርካሪው በያንዳንዱ መሥመር ላይ እንደሚመላለስ ፤

፪/ የተሽከርካሪው ዓይነትና የሚይዘው መንገደኛ ብዛት ፤

፫/ ለአቀደው አገልግሎት የሚያስከፍለውን ዋጋ የሚያሳይ የኪራይ ሠንጠረዥ ፤

ለ/ ሌላ ማንኛውም የንግድ ተሽከርካሪ የሆነ እንደሆነ ፤

፩/ ሊሠራበት ያቀደውን መሥመር ወይም መሥመሮችና በወር ስንት ቀን ተሽከርካሪው በያንዳንዱ መስመር ላይ እንደሚመላለስ ፤

፪/ የተሽከርካሪው ዓይነትና የጭነቱ መጠን ፤

፪/ እያንዳንዱ ማመልከቻም ከመገናኛ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ካለው ከሌላ የመንግ ሥት ባለሥልጣን የተሰጠ ሆኖ የሚከተሉትን ከሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ጋር ይቀርባል ።

ሀ/ ተሽከርካሪው በሚገባ መመርመሩን ፤

ለ/ ልዩ ምዝገባ ለሚደረግበት ተግባር ብቁ ሆኖ መገኘቱንና

ሐ/ ከመገናኛ ሚኒስቴር ተሽከርካሪዎች ከአደጋ ስለሚጠበቅበት ፤ እንዲሁም ስለ ተሽከርካሪዎች መጠንና ክብደት የወጡትን ደንቦች በሚገባ መፈጸሙን ፤

፫/ በተጨማሪም በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲ መሠረት ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት እንዲያ መች እያንዳንዱ ማመልከቻ ከአስተዳደሩ የሚፈለገውንና የሚጠየቀውን ተጨማሪ መረጃ ሁሉ በሙሉ መያዝ አለበት ።

www.chilot.me



ሀ/ ቀድሞ ልዩ ምዝገባ የተደረገለትን ተሽከርካሪ ለመተካት የልዩ ምዝገባ ማስረጃ ለማግኘት ወይም ለማስተላለፍ ሲጠይቅ ፡፡ ይህም የሚሆነው አስተዳዳሪው የተተኪው ተሽከርካሪ የጭነት መጠን ወይም የመንገደኛ መቀመጫ ብዛት ከቀድሞው ተሽከርካሪ ምንም ያህል ብልጫ የማያመጣ መሆኑን ሲረዳ ነው ፡፡

ለ/ ልዩ ምዝገባ የተሰጠበት ጊዜ ሲፈጸም ማደስን ወይም ፤

ሐ/ አንድን ልዩ ምዝገባ ቀድሞ ከተፈቀደለት ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ ሲጠይቅ ፡፡

፬/ አስተዳዳሪው ልዩ ምዝገባ በሚደረግበት ወይም በሚታደስበት ወይም በሚሻሻልበት ጊዜ ከላይ በአንቀጽ ፮ (፩) እና ከዚህ በታች የተመለከቱት ጉዳዮች እንዲፈጸሙ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን መምሪያ መስጠት ይችላል ፡፡

ሀ/ ከአስተዳዳሪው የተፈቀደውን የኪራይ መጠንና የሰዓት ሠንጠረዥ ለሕዝብ በሚታይበት ቦታ እንዲደረጉ ፤

ለ/ ለተሽከርካሪው ደንበኛ ልዩ ምዝገባ መደረጉን የሚያረጋግጥ የመለያ ምልክት አስተዳደሩ በመደበው አኳኋን ለሕዝብ በሚታይበት ቦታ እንዲደረግ ፡፡

ሐ/ ልዩ ምዝገባ የተደረገለት ሰው የሚይዘው መዝገብና ሠነድ ፤ ለአስተዳደሩ በየጊዜው የሚያቀርበውንም መግለጫና መረጃ መወሰን ፤ ስለሆነም አስተዳዳሪው ልዩ ምዝገባው በሚጸናበት በማንኛውም ጊዜ ስለ መግለጫና መረጃ አቀራረብ አስፈላጊ መስሎ የሚታየው ሁሉ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል ፡፡

፭/ ልዩ ምዝገባ የተደረገለት ሰው ልዩ ምዝገባው ሲደረግ የተወሰነውን የተላለፈ እንደሆነ ልዩ ምዝገባው በሚጸናበት በማንኛውም ጊዜ አስተዳዳሪው ልዩ ምዝገባውን ሊሠርዝ ወይም እንዳይታደስ ወይም እንዳይሻሻል ለማድረግ ይችላል ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜም ባለጉዳዩ በአንቀጽ ፩ (፫) በተሰጠው የይግባኝ መብት ይጠቀማል ፡፡

፮/ ግማሽ ተሳቢ ሊቀጠልበት የተጋጠመ ተሽከርካሪ ስለሚባለው የጉታች መኪና ባለንብረት ልዩ ምዝገባ ሲጠይቅ ግን ጉታች መኪናው ወይም ግማሽ ተሳቢው ለየብቻው እንዲያገለግል የሚደረግ ከሆነ ባለንብረቱ ለሁለቱም ለየብቻ ልዩ ምዝገባ እንዲደረግ ማመልከት አለበት ፡፡ በዚህ ጊዜ አስተዳዳሪው ፤ ለጐታች መኪናው ልዩ ምዝገባ ማድረግ ይችላል ፡፡ ልዩ ምዝገባውም ጐታች መኪናው ለማማሽ ተሳቢው በተደረገው ልዩ ምዝገባ መሠረት ማንኛውንም ግማሽ ተሳቢ ለመጐተት የሚያስችለው ይሆናል ፡፡

፯/ ስለሌሎች ተፈላጊ ነገሮች ፤

፩/ ልዩ ምዝገባ የተደረገለት ሰው የልዩ ምዝገባው ማስረጃ በተሰጠው ተሽከርካሪ ውስጥ ሁልጊዜ እንዲገኝና በማስረጃውም ላይ ፤ የተመለከቱት ዝርዝር ጉዳዮች ለማንበብ በሚቻል ሁኔታ መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት ፡፡ ለተሽከርካሪው የተሰጠውም መለያ ምልክት ለማንበብ በሚቻል ሁኔታና በተፈቀደው አኳኋን በተሽከርካሪው ላይ ተደርጎ በሚገባ መጠበቁን ማረጋገጥ ይኖርበታል ፡፡

፪/ በተጨማሪም ልዩ ምዝገባ የተደረገለት ሰው ፤

ሀ/ ቋሚ አድራሻውን የለወጠ እንደሆነ በለወጠ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ አዲሱን ቋሚ አድራሻ ለአስተዳዳሪው ማስታወቅ አለበት ፤

ለ/ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) ውስጥ ሲሠራ የነበረ ተሽከርካሪ አገልግሎቱን ሲያቋርጥ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ይህንኑ ለአስተዳ

www.chilot.me



ዳሬው ማስታወቅና ለተሽከርካሪው የተሰጠው የልዩ ምዝገባ ማስረጃ እንዲሠረዝ መመለስ አለበት ።

ሐ/ በልዩ ምዝገባ ማስረጃው የተመለከተውን የማመላለሻ ተግባር በሚያከናውንበት መሥመር በሙሉ ወይም በከፊል ወይም በማንኛውም ማስረጃው ውስጥ በተመለከተው ቀበሌ ለጊዜው አገልግሎት ለማቋረጥ የታሰበ እንደሆነ አስቀድሞ የአስተዳዳሪውን ፈቃድ ማግኘት አለበት ፤

መ/ በልዩ ምዝገባ ማስረጃው የተመለከተው የማመላለሻ ተግባር በሚከናወንበት መሥመር በሙሉ ወይም በከፊል ወይም በማንኛውም በማስረጃው ውስጥ የተመለከተው ቀበሌ አገልግሎቱን ያቋረጠ እንደሆነ ልዩ ምዝገባው እንዲሻሻል ለአስተዳዳሪው ማቅረብ አለበት ፤

ሠ/ ለተመዘገበ ተሽከርካሪ ሌላ ልዩ ምዝገባ እንዲደረግ የተጠየቀ እንደሆነ የቀድሞ ልዩ ምዝገባ እንዲሻሻል መመለስ አለበት ፤

ረ/ በማንኛውም ምክንያት አንድ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከሃያ አራት (፳፬) ሰዓት ለበለጠ ጊዜ አገልግሎት ያቋረጠ እንደሆነ በዚሁ በሃያ አራት (፳፬) ሰዓት ጊዜ ውስጥ ወዲያው ለአስተዳዳሪው አስታውቆ እንዳስፈላጊነቱ የአገልግሎቱ መቋረጥ እንዲቀጥል ፈቃድ መጠየቅ አለበት ።

፰/ ስለ ልዩ ምዝገባ ማስረጃ አሰጣጥና ስለሚጸናበት ጊዜ ፤

ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው «ሠንጠረዥ» «ሀ» የተመለከተው ዋጋ ከተከፈለ በኋላ በተመደበው ቅጽ (ፎርም) መሠረት የልዩ ምዝገባ ማስረጃ ይሰጣል ። በቅጹ (ፎርሙ) ላይም የተሰጠው ሰውና የተሽከርካሪው ዝርዝር ሁኔታ ፣ አስተዳዳሪው እንዲፈጸሙ የወሰናቸው ጉዳዮችም መገለጽ አለባቸው ። በዚህ ደንብ መሠረት ካልተሠረዘ በስተቀር የተሰጠው ልዩ ምዝገባ ማስረጃ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ላንድ ዓመት ይጸናል ።

፱/ ስለ ቅጣት ፤

፩/ ማናቸውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት በሚቀርብ በማንኛውም ማመልከቻ ወይም ሠነድ ውስጥ ማንኛውንም ነገር ትክክል ወይም ዕውነት አለመሆኑን እያወቀ ገልጾ ወይም ጽፎ ቢያቀርብ እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ ይከሰሳል ፤ በተፈረደበትም ጊዜ በአዋጁ በአንቀጽ ፳፱ መሠረት ይቀጣል ።

፪/ ማናቸውም ሰው የዚህን ደንብ አንቀጽ ፯ ወይም ማንኛውንም ሌላ አንቀጽ የተላለፈ እንደሆነ እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ ይከሰሳል ፤ በተፈረደበትም ጊዜ በአዋጁ በአንቀጽ ፳፱ መሠረት ይቀጣል ።

የተጠቀሰው ሕግ

እዚህ የተጠቀሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጾች የወ.መ.ሕ. ፲፭/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) አን. ፫፻፵፩ ፣ ፫፻፷፩ ፣ ፬፻፲፱—፭፻፪ ፣ ፯፻፵፯ ፣ ፯፻፹፪ ፣ ፯፻፹፫ እንደሆኑ ይገመታል ።

፲/ ይህ ደንብ ስለሚጸናበት ጊዜ ፤

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

www.chilot.me



## ሠንጠረዥ «ሀ»

### ሀ/ ለካሚዮኖች ፡

| የጭነቱ ልክ በኩንታል | | | ዓመታዊ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| ከ 1 | እስከ | 15 | $ 20 |
| » 15 | » | 20 | $ 22 |
| » 20 | » | 30 | $ 26 |
| » 30 | » | 40 | $ 30 |
| » 40 | » | 50 | $ 32 |
| » 50 | » | 60 | $ 36 |
| » 60 | » | 70 | $ 40 |
| » 70 | » | 80 | $ 42 |
| » 80 | » | 90 | $ 46 |
| » 90 | » | 100 | $ 50 |
| » 100 | » | 110 | $ 52 |
| » 110 | » | — | $ 56 |

### ለ/ ለተሳቢዎች ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከ 1 | እስከ | 20 | $ 8 |
| » 20 | » | 40 | $ 10 |
| » 40 | » | 60 | $ 12 |
| » 60 | » | 70 | $ 13 |
| » 70 | » | 80 | $ 14 |
| » 80 | » | 90 | $ 16 |
| » 90 | » | 100 | $ 18 |
| » 100 | » | 110 | $ 20 |
| » 110 | » | 120 | $ 22 |
| » 120 | » | 130 | $ 24 |
| » 130 | » | 140 | $ 26 |
| » 140 | » | 150 | $ 28 |
| » 150 | » | — | $ 30 |

### ሐ/ ለአውቶቡሶች ፡

| የመቀመጫ መጠን ፡ | | | ዓመታዊ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| ከ 1 | እስከ | 10 | $ 20 |
| » 10 | » | 15 | $ 26 |
| » 15 | » | 20 | $ 30 |
| » 20 | » | 25 | $ 32 |
| » 25 | » | 30 | $ 36 |
| » 30 | » | 45 | $ 42 |
| » 40 | » | 50 | $ 50 |
| » 50 | » | 60 | $ 52 |
| » 60 | » | 70 | $ 66 |
| » 70 | » | — | $ 75 |

www.chilot.me



መ/ ለጉታች መኪና ልዩ ማስመዝገቢያ ያለተሳቢ ............... $ 40

ሠ/ ለልዩ ምዝገባ ማሻሻያ ................................ $ 16

ረ/ ለልዩ ምዝገባ ማስረጃ ግልባጭ ፤ ........................... $ 5

ሠንጠረዥ «ለ»

በአንቀጽ ፬ የተጠቀሱ ማዘጋጃ ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የመገናኛ ሚኒስትሩ የውክልና ሥልጣን የሚሰጣቸው ማዘጋጃ ቤቶች ናቸው ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም.

፳፯/፯ (፲፱፻፷) ት. ፶፪*

የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) አስተዳደር ለማቋቋም
የተሰጠ ትእዛዝ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን የኤኮኖሚ መስፋፋት በበለጠ በሚረዳ አኳኋን የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን ሥራ ለመቆጣጠርና ለማካሄድ አንድ የተሟላ ድርጅት ማቋቋም ስላስፈለገ ፤

በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በ፳፯ኛው አንቀጽ የተጻፈውን መሠረት በማድረግና የሚኒስትሮቻችን ምክር ቤት የመከረበትን አይተን ቀጥሎ ያለውን አዝዘናል ።

፩/ አጭር አርእስት ፤

ይህ ትእዛዝ «የ፲፱፻፷ ዓ.ም. የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) አስተዳደር ትእዛዝ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ ስለመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) አስተዳደር መቋቋም ፤

ከዚህ በታች «አስተዳደር» ተብሎ የሚጠራ ራሱን ችሎ የሚተዳደር አንድ የኢትዮጵያ ን/ነ/መንግሥት የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) አስተዳደር ባለሥልጣን በዚህ ትእዛዝ ተቋቁሟል ።

---

*የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳፯/፲፫ (፲፱፻፷) ግ. ፳፰ (በአማርኛው ብቻ) ታረመ ።

www.chilot.me



የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፩፻፷፮/፲፫ (፲፱፻፷) ግ. ፷፭ (በአማርኛው ብቻ) ታረመ ።

፫/ የአስተዳደሩ አመሠራረት ፤

አስተዳደሩ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ይጠቀልላል

፩/ ከዚህ በታች «ቦርድ» ተብሎ የሚጠራውን አንድ የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስ ፖርት) ቦርድ ፤

፪/ ከዚህ በታች «አስተዳዳሪ» ተብሎ የሚጠራውን አንድ የመንገድ ማመላለሻ (ትራ ንስፖርት) አስተዳዳሪ ፤

፫/ አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ መሪዎችና ሠራተኞች ፤

፬/ የአስተዳደሩ ዓላማና ተግባር ፤

፩/ የአስተዳደሩ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ የግልና የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመ ላለሻን (ትራንስፖርትን) ሥራ መቆጣጠር ፤ መወሰንና መከታተል ነው ።

፪/ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጠቅላላነት ሳይቀነስ ፤ አስተዳደሩ በሕግ መሠረት ከዚህ የሚከተሉትን ለመፈጸም ኃላፊ ነው ።

ሀ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን የሥራ መምሪያዎችና ፕሮግራሞችን ማጽደቅና ማስፈጸም ፤

ለ/ የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት ማኅበሮችን ማትጋት ፤ መከታተል ፤ መቆጣጠ ርና መምራት ፤

ሐ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርትን የሥራ መምሪያዎችና ፕሮግራሞች በሚገባ የሚያስፈጽምና የሚያካሄድ አስተዳደራዊ ድርጅት ማቋቋም ፤

መ/ የተቀበለውን ፤ ወይም እንዲተዳደርበት የተመደበለትን ገንዘብ በሕግ መሠረት ማስተዳደር ፤

ሠ/ በሕግ የተሰጡትን ማናቸውንም ሌሎች ተግባሮች መፈጸም ፤

፭/ የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) ቦርድ ፤

፩/ ከዚህ በታች «ቦርድ» ተብሎ የሚጠራ አንድ የመንገድ ማመላለሻ (ትራንስፖርት) ቦርድ ተቋቁሟል ፤ በውስጡም የሚከተሉት አባሎች ይገኙበታል ።

ሀ/ የመገናኛ ሚኒስትራችን ፤ በሊቀ መንበርነት ፤

ለ/ አስተዳዳሪው ፤

ሐ/ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ፤ የአገር ግዛት ሚኒስቴርና የሥራ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ፤

መ/ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ድርጅቶች የሚወክሉት (፪) ሁለት አባሎች ፤

ሠ/ ዕቃ አስጫኞች የሚወክሏቸው (፪) ሁለት አባሎች ፤

፪/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ፤ አስፈላጊም ሲሆን በሊቀ መንበሩ ጥሪ በማናቸ ውም ጊዜ ይሰበሰባል ።

www.chilot.me



## ምዕራፍ ፬

## የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር ።

### ፲፫/ ፖስታ ቤትን መቆጣጠር ።

ፖስታ ቤት በሚኒስትሩ ጠቅላላ መሪነትና ተቆጣጣሪነት ሥራውን ያከናውናል ። ተግባ ሩንና ኃላፊነቱንም ይፈጽማል ።

### ፲፬/ ኢንተርናሲዮናል ግዴታዎች ።

የፖስታን አገልግሎት በሚመለከት ኢንተርናሲዮናል ጉዳይ ሁሉ ስለፖስታ አገልግሎት በሚደረጉ ኢንተርናሲዮናል ጉባዔዎች ፤ ኮንፍራንሶችና ስብሰባዎች ወይም ንግግሮች ጭምር ሚኒስቴሩ የኢትዮጵያ ወኪልና እንደራሴ ነው ።

### ፲፭/ ዝርዝር ሥልጣን ።

፩/ ፖስታ ቤትን ለመምራትና ለመቆጣጠር በዚህ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሚኒስትሩ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን መወሰን ይችላል ።

ሀ/ ፖስታ ቤት የሚሰጠውን አገልግሎት ዓይነትና መጠን ፤

ለ/ ፖስታ ቤት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለውን የፖስታና ሌላ ዋጋ ፤

ሐ/ ፖስታ ቤት የሚገለገልባቸውን ቅጾች (ፎርም) ፤

መ/ ፖስታን መቀበል ፣ መላክና ማስረከብ ፣ በአደራ መስጠትና ለሌላም ልዩ አገል ግሎት ደረሰኝ መስጠትን ፤ ፖስታን ተቀብሎ ማስረከብን ፣ ምስክርነትን መስ ጠትንም የሚመራ አሠራር ፤

ሠ/ የፖስታ ቴምብሮችን ፣ ቴምብር የታተመባቸው እንቮሎፖችን ፣ የፖስታ ካርዶ ችንና ሌሎች የቴምብር እትሞችን አሳትሞ ማውጣትን ፤

ረ/ የተበላሹ ፣ የማይሠራባቸው ወይም አላግባብ የሚሠራባቸው ቴምብሮች ወይም ሌሎች የፖስታ እትሞች እንዳይሠራባቸው የሚመራ አሠራር ፤

ሰ/ የጠፋ ፣ የተበላሸ ወይም በስሕተት የተሰጠ ፖስታን ዝርዝር ሁኔታና አሠራር፤

ሸ/ በዚህ አዋጅ የተወሰነውን ማናቸውንም ጉዳይ በሚገባ አኳኋን መፈጸም ፤

፪/ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፲፭ መሠረት የሚመደበው ደንብ ሁሉ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል ።

## ምዕራፍ ፭

## ፖስታን ስለማመላለስ ።

### ፲፮/ የማመላለሱ አሠራርና ሁናቴ ።

፩/ ፖስታን በየብስ ፣ በባሕር ወይም በአየር ማመላለስ ይቻላል ።

፪/ ማናቸውም አመላላሽ ፖስታ ቤት ሲጠይቀው ፤ ፖስታን ለመቀበል ፣ ለማመላለስ ወይም ለማስረከብ እምቢ ማለት አይችልም ። ሆኖም ለአገልግሎቱ ተገቢ ዋጋ ይከ ፈለዋል ።

፫/ ፖስታን ስለማመላለስ ጉዳይ ፖስታ ቤትና አመላላሾች ስምምነት ያደርጋሉ ።

www.chilot.me



ለፍ ፤ ሊያዝ ወይም ሊጣል (ሊቀደድ) ይቻላል ። ፖስታው የሚያዝ ወይም የሚጣል እንደሆነ ግን ፤ መያዙን ወይም መጣሉን ላኪው ፖስታ ቤት እንዲያውቅ ይደረጋል ።

፳፬/ አገልግሎትን ማቋረጥ ።

በዚህ አዋጅ የተመደበው ሳያግደው ሁናቴው ያስገደደ እንደሆነ ወይም ከአቅም በላይ የሆነበት እንደሆነ የፖስታ ቤት አስቀድሞ ማስታወቂያ ሳያወጣ ማናቸውንም የፖስታ አገልግሎት ሊያቋርጥ ወይም ሊቀንስ ይችላል ።

ምዕራፍ ፯

ስለፖስታ ግለኝነት ።

፳፭/ የግለኝነት ማረጋገጫ ።

፩/ የፖስታ ግለኝነት በዚህ አዋጅ ተረጋግጦአል ። ስለሆነም በሀገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ ሁናቴ የሚታወጅበት ወቅት ፖስታን መመርመር ይቻላል ።

፪/ ለፖስታ ቤት የተሰጠ ማንኛውንም ፖስታ መክፈት ፤ ማንበብ ፤ መጣል ፡ መቅደድ ፤ መደበቅ ወይም መስረቅ ለማንም አይፈቀድም ። የፖስታ ቤት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ያየውንና የሰማውን ማንኛውንም ነገር በማናቸውም ጊዜ ላልተፈቀደ ለት ሰው እዳይገለጽ ተከልክሏል ።

፫/ ማናቸውም አመላላሽ በኃላፊነቱ እንዲያደርስ በተሰጠው የፖስታ ከረጢት ላይ ጥፋት እንዳያደርስ ተከልክሏል ።

፳፮/ ውሳኔው የማይጸናበት ሁናቴ ።

በዚህ ምዕራፍ የተወሰነው የሚከተለውን ከማድረግ ፖስታ ቤትን አያግደውም ።

፩/ ስለጉዳዩ ለፖስታ ላኪ ወይም ተቀባይ መረጃ መስጠት ፤

፪/ በሕግ መሠረት ለፍርድ ቤት ፤ ለሒሳ ለሚገባው ባለሥልጣን መረጃና ፖስታ መስጠት ፤

፫/ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልበት ኮሊ ፖስታ የሆነ እንደሆነ ወይም በአንቀጽ ፳ የተከለሉ ነገሮችን የያዘ መሆኑ የተጠረጠረ እንደሆነ መክፈት ፤

፬/ ከደብዳቤ በቀር ደረጃውንና ተገቢውን የፖስታ ዋጋ ለማወቅ ወይም ከፖስታ ዋጋ ነፃ ነው ተብሎ የተላከ ፖስታን በነፃ መላክ እንደሚገባው ለማረጋገጥ መክፈት ።

ምዕራፍ ፰

የሥራ ሰዓት ።

፳፯/ የተመደቡ ሰዓቶች ።

በየሥፍራው እንደሚያስፈልግ ፤ የፖስታ ቤት ለተመደበ ጊዜ ይከፈታል ። ስለሆነም በሥራ ቀን የፖስታ ቤት በቀን ከአራት ሰዓት ፤ በእሑድና በሕዝብ በዓል ቀንም ከሁለት ሰዓት ለማያንስ ጊዜ ይከፈታል ።

፳፰/ የሥራ ሰዓቶችን ማሳወቅ ።

የፖስታ ቤት ለሕዝብ የሚከፈትበት ጊዜ ፤ የፖስታ መምጫና መሄጃ ሰዓት ጭምር በየ ፖስታ ቤቱ በማስታወቂያ በሚታይ ሥፍራ ይደረጋል ።

www.chilot.me



## ምዕራፍ ፱ ።

## የጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች የፖስታ ቤት ያልሆኑ ቀረጦችን ስለ መሰብሰብ ።

### ፳፱/ ቀረጥን የመሰብሰብ ሥልጣን ።

ፖስታ ቤት የጉምሩክ ባለሥልጣን ሲወክለው ፖስታ ከሚልክ ወይም ከሚቀበል ሰው የጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች የፖስታ ቤት ያልሆኑ ቀረጦችን መቀበል ይችላል ።

### ፴/ የጉምሩክ ፍተሻ ሥፍራ ።

በፖስታ ላይ የሚደረግ የጉምሩክ ፍተሻ ፡ የጉምሩክና የፖስታ ሠራተኞች ባሉበት በፖስታ ቤት ውስጥ ይፈጸማል ።

### ፴፩/ ጉምሩክን መርዳት ።

የጉምሩክ ፍተሻ በሚደረግበት ገቢና ወጪ ፖስታ የፖስታ ቤት ከጉምሩክ አስተዳደር ጋር ይተባበራል ፡ ይረዳዋልም ።

## ምዕራፍ ፲

## ስለፖስታ ቴምብርና ስለፖስታ ዋጋ ።

### ፴፪/ አስቀድሞ መክፈል ።

በልዩ ደንብ ከሚወሰነው በቀር የፖስታን ታሪፍ ፡ ሌላውንም ዋጋ ላኪው አስቀድሞ በገንዘብ ወይም በቴምብር ይከፍላል ።

### ፴፫/ በዕለት ማኅተም መደምሰስ ።

በፖስታ ቴምብሮችን ፡ ቴምብር የታተመባቸው አንቬሎፖችን ፡ የፖስታ ካርዶችንና ሌሎች የፖስታ እትሞችን ፡ በዕለት ማኅተም ማተም ወይም መደምሰስ የሚችሉ የተፈቀደላቸው የፖስታ ቤት ሠራተኞች ብቻ ናቸው ።

### ፴፬/ የሽያጭ ወሰን ።

፩/ የፖስታ ቴምብሮችን ፡ ቴምብር የታተመባቸው አንቬሎፖችን ፡ የፖስታ ካርዶችንና ሌሎች የፖስታ እትሞችን መሸጥ ወይም የፖስታ ሚኒስትሩ የሚፈቅድለት የፖስታ ቤት ለዚሁ ጉዳይ የሚሰጠው ፈቃድ ሳይኖረው ፡ የፖስታን ዋጋ አስቀድሞ የሚያስከፍል የቴምብር ማኅተም መሥራት ወይም በማኅተሙ መገልገል ለማናቸውም ሰው አይፈቀድም ።

፪/ የፖስታ ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የታተመባቸው ቅጾችን ከተወሰነው ዋጋ ሌላ አስቀድሞ ስለፖስታ ዋጋ መሸጥ ለማንም አይፈቀድም ።

### ፴፭/ በዕለት ማኅተምና በሌሎች ማኅተሞች መገልገል ።

፩/ በፖስታ ቤት የሚሠራባቸው የዕለት ማኅተምና ሌሎች ማኅተሞች በደንብ ይወሰናሉ ።

፪/ ለፖስታ ቤት የተሰጠበትን አስመስሎ ባንድ ፖስታ ላይ በሐሰት ሌላ ቀን ማተም ለማንም አይፈቀድም ።

www.chilot.me



፴፯/ በማስመሰል የሚታተሙና የተገለገለባቸው ቴምብሮች ።

ተቀባይ (ባለአድራሻው) መጠቅለያውን ወዲያው ለፖስታ ቤት ካላስረከበ ፣ የሐሰት ወይም በማስመሰል የታተመ ወይም የተሠራበት ቴምብር የተለጠፈበት ማናቸውም ፖስታ አይ ሰጥም ። ቴምብሩን ወይም ቴምብሮቹን ከፖስታው መለየት (ማላቀቅ) ያልተቻለ እንደ ሆነ ፣ ተቀባዩ (ባለአድራሻው) ፖስታውን እንዳለ ያስረክባል ። የሚፈለገውን መረጃ ይሰ ጣል ።

፴፰/ ቴምብር መላጥ ።

ለመስረቅ በማሰብ ፣ በማናቸውም ፖስታ ላይ የተለጠፈ ቴምብርን መላጥ ለማንም አይፈ ቀድም ።

፴፱/ ከፖስታ ዋጋ ነፃ መሆን ።

፩/ ማናቸውም ፖስታ ቤት ለሌሎች ፖስታ ቤቶች የሚልከው ፖስታ በነፃ ይላካል ።

፪/ ኢትዮጵያ በተባበረችበት እንተርናስዮናል የፖስታ ስምምነት መሠረት ፖስታ ከፖ ስታ ዋጋ ነፃ የሚሆነው የሚወሰነውን ደንብ ተከትሎ ነው ።

፵፪/ የፖስታ ዋጋ መጓደል ።

ቴምብር ሳይለጠፍበት ወይም የሚበቃ የቴምብር ዋጋ ሳይከፈልበት በተገኘ ፖስታ የጐ ደለውን የቴምብር ዋጋ የፖስታ ቤት ተቀባዩን ወይም ላኪውን በእጥፍ ያስከፍላል ። ስለሆነ ግን ፣

፩/ ለአደራ ፖስታ የጐደለው ዋጋ ብቻ ይከፈላል ።

፪/ ለበነ አድርጎት በተጨማሪ (በሰርቻርጅ) በቴምብር ላይ ለሚከፈል ያልተከፈለው ወይም የጎደለው ዋጋ ብቻ ይከፈላል ።

፫/ ለፖስታ ቤት አካባቢ የተላከን ፖስታ ከአካባቢው ወጪ መላክ ያስፈለገ እንደ ሆነ ለአካባቢው የሚከፈለውና ከአካባቢው ውጪ የሚከፈለው የዋጋ ልዩነት ብቻ ይከፈላል ።

፵/ አድራሻው የሚለወጥ ፖስታ ።

ተጨማሪ ዋጋ ከማይከፈልበት ከፖስታ መልእክት በቀር አድራሻው የሚለወጥ ወይም ለላኪው የሚመለስ ፖስታ መደበኛ የፖስታ ዋጋ እንደገና ይከፈልበታል ።

፵፩/ የፖስታ ዋጋ ወሰን ።

ፖስታን ለመቀበል ፣ ለማመላለስና ለማደል በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚመደበው የፖስታ ዋጋ በላይ አይከፈልም ።

ምዕራፍ ፲፩
ስለፖስታ ባለቤትነት ።

፵፪/ የላኪው መብት ።

፩/ በዚህ አዋጅ በተወሰነው መሠረት ለባለአድራሻው እስኪሰጥ ድረስ ፖስታ የላኪው ንብረት ሆኖ ይቆያል ።

www.chilot.me



፪/ በዚህ አዋጅ በተወሰነው መሠረት ፖስታ በፖስታ ቤት እጅ እስካለ ድረስ ላኪው የሚከተለውን ማድረግ ይችላል ።

ሀ/ ፖስታውን መልሶ መውሰድ ፤

ለ/ የፖስታን አድራሻ ማስተካከል ወይም መለወጥ ፤

ሐ/ ፖስታው ለሌላ ባለአድራሻ እንዲላክ መጠየቅ ፤

መ/ ፖስታው በነፃ እንዲሰጥ ፣ ሲሰጥ ገንዘቡ በሙሉ ወይም በቅናሽ እንዲከፈልበት መጠየቅ ፤

ሠ/ ፖስታው እንዲመለስለት መጠየቅ ፤

ረ/ ፖስታው እንዲሸጥ ወይም እንዲጣል (እንዲቀደድ) መጠየቅ ወይም

ሰ/ የፖስታውን ባለቤትነት መልቀቅ ።

## ፵፫/ የባለአድራሻው (የተቀባዩ) መብት ።

፩/ ባለአድራሻው ፖስታ ከመቀበል በፊት የሚከተለውን ማድረግ ይችላል ።

ሀ/ በተወሰነው ደንብ መሠረት ፖስታው ወደሌላ አድራሻ እንዲላክለት ፤ ወይም እንዲቆይለት መጠየቅ ፤

ለ/ ፖስታውን የሚቀበልለትን መወከል ፤

ሐ/ ላኪው ፖስታውን በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ እንዲላክለት እንዲያደርግ ፖስታ ቤትን መጠየቅ ፤

መ/ ፖስታው የተጐዳ ፣ የተዘረፈ ፣ ወይም የጠፋ እንደሆነ ለመብቱ መከላከል ወይም ካሣ መጠየቅ ፤ ወይም

ሠ/ ፍርድ ቤት እንዲቀበል ካላዘዘ ፖስታን ላለመቀበል ፤

፪/ አንድ ባለአድራሻ ገንዘቡን ከመክፈሉ በፊት እንዲከፈልበት የተላከ ፖስታን ከፍቶ እንዲያይ መጠየቅ አይችልም ።

## ፵፬/ የፖስታ ቅጾች (ፎርም) ።

የኮሊ መላኪያ ዝርዝር ፣ የሐዋላ ቅጽ (ፎርም) ፣ የአቤቱታ ቅጽ ፣ የፖስታ መድረስ ወይም አለመድረስ ማስታወቂያ የተለጠፈበት ቴምብር ጭምር ፣ እንዲሁም ማንኛውም ሌላ የፖስታ ቅጽ ሁሉ በፖስታ ቤት እጅ እስካለ ድረስ ንብረቱ ሆኖ ይቆያል ። ከዚህ በላይ በተጠቀሱ ቅጾች ሁሉ ላይ ጉዳት የሚያመጣ ማናቸውም ሰው በኃላፊነት ይጠየቃል ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የዚህ አንቀጽ የእንግሊዝኛው ቅጅ የመጨረሻው ዐረፍተ ነገር «ማናቸውም» የሚለው ቃል አይገኝበትም ።

## ምዕራፍ ፲፪

## ፖስታን ስለማደል ።

## ፵፭/ የማደል ወሰን ።

በዚህ አዋጅ በተወሰነው መሠረት ፖስታ ለባለአድራሻው ፣ ለወኪሉ ፣ ለሞግዚቱ ፣ ወይም ለሕጋዊ ወራሹ ብቻ ይሰጣል (ይታደላል) ።

## ፵፮/ ተመላሽ ፖስታ ።

የተመለሰ ፖስታ ለላኪው ወይም በአንቀጽ ፵፭ ለተጠቀሱ ሰዎች ብቻ ይሰጣል (ይታደላል) ።

www.chilot.me



፹፯/ የሚከፈል የፖስታ ዋጋ ፡፡

ለላኪው በሚመለስ ፖስታ የሚከፈለውን ዋጋ ፖስታውን መልሶ መቀበል ግዴታ ያለ በት ላኪው ይከፍላል ፡፡

፹፰/ ተቀባይ ያጣ ፖስታ ፡፡

በአንቀጽ ፳፫ ከተከለከለው በቀር ባለአድራሻው አልቀበል ያለው ወይም ተቀባይ ያጣ ወይም በየምክንያቱ ለመስጠት ያልተቻለ ፖስታ ያልተሰጠበት ምክንያት ተገልጾ ወዲያው ለላኪው ይመለሳል ፤ ወይም በዚህ ሕግ እንደተወሰነው ይፈጸምበታል ፡፡

ምዕራፍ ፲፫

ጥያቄና ኃላፊነት ፡፡

፹፱/ የጊዜ ወሰን ፡፡

፩/ ስለተሰጠ ፖስታ የፖስታ ቤት ጥያቄን የሚቀበል ፖስታው ከተሰጠበት ቀን አን ስቶ እስከ አንድ ዓመት ነው ፡፡

፪/ የፖስታውን መድረስ ለማወቅ በተለይ ላኪ አስቀድሞ ከሚከፈለው በቀር ግናቸውም (ጥያቄ) የሚያቀርብ ሰው የተመደበውን ዋጋ ይከፍላል ፡፡

፫/ የጥያቄው ውጤት ከፖስታ ቤት መሳሳት የተነሣ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ለአቤቱታ የተከፈለው ገንዘብ ይመለሳል ፡፡

፺/ ለጠፋ ዕቃ ኃላፊ መሆን ፡፡

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፩ የተዘረዘረው ፖስታ የጠፋ ፣ የተበላሸ ወይም የተሰረቀ እንደ ሆነ ፤ በሕግ እንደተወሰነው የፖስታ ቤት ለላኪው ወይም ለመብቱ የሚከላከል መሆ ኑን ሲገልጽ ለተቀባዩ ካሣ ይከፍላል ፡፡

፺፩/ የካሣ ወሰን ፡፡

የፖስታ ካሣ የሚከፈለው ፖስታው ከተሰጠ በኋላ በ፲፪ ወር ውስጥ ጥያቄ ላቀረበበት ፤ በአደራ ተሰጥቶ ለጠፋ ፣ ለተበላሸ ፣ ለተሰረቀ ወይም ያለአድራሻው ለተሰጠ ፖስታ ፣ የፖስታ ጥቅል (ኮሊ) ወይም በሐዋላ ለተላከ ገንዘብ ብቻ ነው ፡፡

፺፪/ ውሳኔው የማይጸናበት ሁኔታ ፡፡

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተነሣ ለጠፋ ፣ ለተጐዳ ፣ ለተሰረቀ ወይም ያለአ ድራሻው ለተሰጠ የአደራ ፖስታ ፣ ለፖስታ ጥቅል (ኮሊ) ወይም በሐዋላ ለተላከ ገን ዘብ ካሣ አይከፈልም ፡፡

፩/ ከፖስታ ቤቱ አቅም በላይ ወይም ከ«ፎርስሜዠር» የተነሣ ሲሆን ፤

፪/ ከላኪው ወይም ከባለአድራሻው ቸልተኝነት የተነሣ ሲሆን ፤

፫/ ኃላፊነቱ በሌላ አኳኋን ካልተረጋገጠ ፣ ከፖስታ ቤቱ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ኦፊሲየል ሠነዶች ጨርሰው የተበላሹ ወይም የጠፉ ሲሆኑ ፤

፬/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፫ መሠረት የተከለከለ ሲሆን ፤

፭/ ኃላፊነቱን በማይቀበል አገልግሎት ወይም አመላላሽ እጅ ሳለ ለሚጠፋ ፣ ለሚበላሽ ፣ ለሚሰረቅ ፤ ወይም ያለአድራሻው ለሚሰጥ ፖስታ ሲሆን ፤ ወይም

www.chilot.me



፭/ በአንቀጽ ፶፩ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ስለፖስታው አቤቱታ ያልቀረበ ሲሆን ፤

፶፫/ የካሣ አወሳሰን ።

ከፖስታው መጥፋት ፣ መበላሸት ፣ መሰረቅ ወይም ያለአድራሻ መሰጠት የተነሣ በቀጥታ ያልደረሰ (ያልታሰበ) ጉዳት ወይም የቀረ ጥቅም በካሣ ውስጥ አይታሰብም ።

፶፬/ ስለሚጠፋ እንተርናስዮናል ፖስታ ።

ለጠፋ ፣ ለተበላሸና ለተሰረቀ ወይም ያለአድራሻው ለተሰጠ ፣ እንተርናስዮናል ፖስታ የሚከፈለው ካሣ በዓለም የፖስታ ኅብረት ስምምነት (ኮንቬንሽን) በተወሰነውና ከሌሎች አገሮች ጋር በሚደረጉ ልዩ ስምምነቶች መሠረት ነው ።

፶፭/ የካሣ መክፈያ ጊዜ ።

ካሣ የሚከፈለው አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ከስድስት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ነው ።

፶፮/ ካሣን ማስተካት ።

ለጠፋ ፣ ለተበላሸ ፣ ለተሰረቀ ወይም ያለአድራሻው ለተሰጠ ፖስታ የፖስታ ቤት የሚከፈለውን ማናቸውንም ካሣ ለጥፋቱ ኃላፊ የሆነ ሰው ወይም የሆኑ ሰዎች ይተኩታል ።

፶፯/ ጉዳትን የሚያስከትል ፖስታ ።

የጥፋቱ የአመላላሽ ወይም የፖስታ ቤት መሆኑ ካልተረጋገጠ ያንድ ፖስታ ላኪ ላልተከፈለ ዋጋ እንዲሁም ፖስታው በሌላ ፖስታ ፣ በአመላላሹ ወይም የማመላለስን ሥራ በሚያከናውኑ ሰዎች ላይ ለሚያመጣው ጉዳት ሁሉ ኃላፊ ይሆናል ።

፶፰/ የአቤቱታን ዘመን ስለመወሰን (ይርጋ) ።

ሌላ ውሳኔ የተሰጠበት ካልሆነ የፖስታ አገልግሎትን አሠራርና ሥራ የሚመለከት ማንኛውም መብት አቤቱታ ወይም ሕጋዊ ክስ በሁለት ዓመት ውስጥ ካልተጠቀሙበት በይርጋ ይታገዳል ።

## ምዕራፍ ፲፩

## ተጨማሪ ውሳኔ ።

፶፱/ ከግብር ነፃ መሆን ።

የፖስታ አገልግሎትን ለማከናወን ከውጪ አገሮች በሚያስመጣቸው ወይም ወደ ውጪ አገሮች በሚልካቸው ዕቃዎች ፣ መሣሪያዎች ወይም ሌሎች ነገሮች ለሌሎች የመንግሥቱ ሚኒስቴሮች በሚፈቀደው መሠረት የፖስታ ቤት ከግብር ፣ ከቀረጥና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ነው ።

፷/ መለዮ ።

የፖስታ ቤት መለዮ ፣ የኢትዮጵያ ፖስታ ምልክት ፣ በስንጥቅ ዘንግ የተሳካ ፖስታን የያዘ የፖስተኛ እጅ ሆኖ ከበላዩ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ፣ ከበታቹ «የኢትዮጵያ ፖስታ» የሚል ጽሑፍ ያለበት ነው ።

www.chilot.me



፩/ ደብዳቤዎች ፤

፩/ ለመጀመሪያው ፳ ግራም $ 0.30

፪/ በተጨማሪ ለሚቀጥለው ፳ ግራም ወይም ለክፍያው $ 0.20

፪/ ለፖስታ ካርድ ፤

፩/ ለተራ የፖስታ ካርድ $ 0.20

፪/ ደርሶ መልስ የፖስታ ካርድ $ 0.40

ማሳሰቢያ ፤ የፖስታ ቤቱ በሚሸጠው ባለሥዕል የፖስታ ካርድ በተጨማሪ 0.05 ይከፍላል ።

፫/ የዕቃ ዓይነቶች (ሌሽንትዩ) እና የታተሙ ጽሑፎች ፤

፩/ ለመጀመሪያው ፶ ግራም $ 0.15

፪/ በተጨማሪ ለሚቀጥለው ፶ ግራም ወይም ለክፍያው $ 0.05

፫/ ለንግድ ለሚሆኑ ወረቀቶችና የዕቃ ሌሽንትዩ ብቻ አነስተኛ ዋጋው $ 0.30

፬/ ለዕውራን የሚያገለግሉ ጽሑፎች በነፃ

፭/ ጋዜጣዎች ፤

ከዚህ በላይ በ፫ኛው ቁጥር ለታተሙ ወረቀቶች ከተወሰነው ላይ በኢትዮጵያ ለሚታተሙ ጋዜጦች በመቶ ሃምሳ (50%) ቅናሽ በማድረግ እንደሚከተለው ይከፈላል ።

፩/ እስከ ፶ ግራም $ 0.08

፪/ በተጨማሪ ለሚቀጥለው ፶ ግራም ወይም ለክፍያው $ 0.03

፫/ የሚከፈል አነስተኛ ዋጋ $ 0.15

፮/ ትንንሽ ፓኬዎች (ጥቅሎች) ፤

፩/ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው $ 0.15

፪/ የሚከፈል አነስተኛ ዋጋ $ 0.65

፯/ የትንንሽ ፓኬዎች ማደያ ዋጋ ፤

፩/ በፖስታ ቤት ሲሰጥ $ 0.35

፪/ ለባለ አድራሻው እቤቱ ድረስ ሊላክ $ 0.50

፰/ የኢንተርናሲዮናል የመልስ ኩፖን ፤ $ 0.35

## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷፭/፲፯ (፲፱፻፶፭) ሕ· ፫፻፲፭ አን· ፫ ይህ ቁጥር ተሰጠው ፤ በ፷፭/፲፯ (፲፱፻፶፭) ሕ· ፫፻፲፭ አን· ፫-፱ ተሻሻለ ።

www.chilot.me



## ምዕራፍ ፫

## የአየር የፖስታ ዋጋ ።

| የአገር ስም | ለደብዳቤ ለ፲ ግራም ክብደት የኢ.ት/ብር | ለካርድ ለ፳ ግራም ክብደት የኢ.ት/ብር | ለሌሎች ዕቃዎች ለ፶ ግራም ክብ ደት የሚከፈል የኢ.ት/ብር | ለአየር መልእክት የሚከፈል የኢ.ት/ብር |
|---|---|---|---|---|
| ፩/ ሀይቲ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪/ ሁንጋሪያ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፫/ ህንድ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፬/ ሆላንድ (ኔዘርላንድ) | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፭/ ሆንዱራስ ሪፐብሊክ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፮/ ሆንዱራስ የእንግሊዝ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፯/ ሆንግ ኮንግ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፰/ ሉክሳምቡርግ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፱/ ሊባኖስ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፲/ ሊብያ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፲፩/ ሊዋርድ ደሴቶች | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፲፪/ ላቡዋን | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፲፫/ ላኦስ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፲፬/ ላይቤሪያ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፲፭/ ሉያልቲ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፲፮/ መካከለኛ የአፍሪቃ ሬፑብሊክ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፲፯/ ሙስካትና ኦማን | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፲፰/ ሚድዌይ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፲፱/ ማሊ ሪፐብሊክ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፳/ ማላዊ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፳፩/ ማላጋሲ ሪፐብሊክ (ማዳጋስካር) | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፳፪/ ማሊዝያ ፌዴሬሲዮን | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፳፫/ ማልታ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፳፬/ ማሪያና ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፳፭/ ማርኬሰስ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፳፮/ ማርሻል ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፳፯/ ማርቲንክ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፳፰/ ማካዎ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፳፱/ ማዴይራ ደሴቶች | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፴/ ማጁር (ማርሻል ደሴቶች የአሜሪካ) | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፴፩/ ሜክሲኮ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፴፪/ ሞሪሸስ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፴፫/ ሞሪታንያ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፴፬/ ሞሮኮ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፴፭/ ሞናኮ (ፍራንስ) | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፴፮/ ሞንትስራት | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፴፯/ ሞንጎሊያ ሪፐብሊክ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፴፰/ ሞዛምቢክ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፴፱/ ሰሎሞን ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፵/ ሴኔጋል | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፵፩/ ሱማሌ (የፈረንሣይ ጅቡቲ) | 0.40 | 0.25 | 0.20 | 0.30 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፻፹፰/ ዩጋንዳ | 0.40 | 0.25 | 0.20 | 0.30 |
| ፻፹፱/ ዮርዳኖስ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፻፺/ የተባበረው የዐረብ ረፐብሊክ (ግብፅ) | 0.40 | 0.25 | 0.20 | 0.30 |
| ፻፺፩/ ደቡባዊ ምዕራብ አፍሪቃ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፻፺፪/ ደቡብ አፍሪቃ ኅብረት | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፻፺፫/ ዳሆሜይ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፻፺፬/ ዳንማርክ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፻፺፭/ ዶሚኒካ ደሴት | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፻፺፮/ ዶሚኒካን ረፐብሊክ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፻፺፯/ ጀርመን (ምሥራቃዊት) | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፻፺፰/ ጀርመን (ምዕራባዊት) | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፻፺፱/ ጃሜካ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻/ ጃፓን | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፩ ጅብራልታር | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፪፻፪/ ጅቡቲ (የፈረንሳይ ሱማሌላንድ) | 0.40 | 0.25 | 0.20 | 0.30 |
| ፪፻፫/ ጆርጅያ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፬/ ጐዋም | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፭/ ጐዋቲማላ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፮/ ጊልበርትና ኤሊስ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፯/ ጊኒ ሪፐብሊክ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፰/ ጊያና (የሆላንድ ሱሪናም) | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፱/ ጊያና (የእንግሊዝ) | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፲/ ጊያና (የፍራንስ) | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፲፩/ ጋምቢያ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፲፪/ ጋቦን | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፲፫/ ጋና | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፲፬/ ግራናዳ ደሴት | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፲፭/ ግሪክ | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፲፮/ ግሪንላንድ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፪፻፲፯/ ግብፅ የተባበረው ዐረብ ረፐብሊክ | 0.40 | 0.25 | 0.20 | 0.30 |
| ፪፻፲፰/ ጓደሎፕ | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፲፱/ ፈረናንዶፖ ደሴት | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፪፻፳/ ፈኒንግ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፳፩/ ፊጂ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፳፪/ ፎልኡን ደሴቶች | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፳፫/ ፊንላንድ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፪፻፳፬/ ፋርስ ባሕር አገሮች | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፳፭/ ፋርስ ደሴቶች (ዳንማርክ) | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፪፻፳፮/ ፊኒክስ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፳፯/ ፍራንስ | 0.60 | 0.35 | 0.30 | 0.30 |
| ፪፻፳፰/ ፍክላንድ ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፳፱/ ፒትከርን ደሴቶች | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፴/ ፓራጉዋይ | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |
| ፪፻፴፩/ ፓናማ (ሪፑብሊክ) | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፴፪/ ፓናማ (ካናል ዞን) | 0.80 | 0.45 | 0.40 | 0.55 |
| ፪፻፴፫/ ፓኪስታን | 0.50 | 0.30 | 0.25 | 0.30 |
| ፪፻፴፬/ ፓፒዋ | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.50 |
| ፪፻፴፭/ ፔሩ | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.50 |
| ፪፻፴፮/ ፖሊኔዚያ (የፍራንስ) | 1.00 | 0.55 | 0.50 | 0.55 |

www.chilot.me



| | | የኢ.ት/ብር |
|---|---|---|
| ፯/ | ለሚያስቸኩል (ኤክስፕሬስ) ጥቅል ፖስታ | 0.65 |
| ፯/ | ኮሊ. ፖስታ ባለመወሰዱ ማሳሰቢያ ሲጻፍ | 0.35 |
| ፰/ | ሀ/ ለኮሊ. ፖስታ ኢንሹራንስ ዋጋ ለእያንዳንዱ ፪፻ የወርቅ ፍራንክ ወይም የኢ.ት/ብር ፻፳፩ | 0.40 |
| | ለ/ በኢንሹራንስ ኮሊ. መላክ የሚቻል እስከ | 800.00 |
| ፱/ | መድረሱን ለማረጋገጥ ሲፈለግ | |
| | ሀ/ ኮሊው ሲላክ የተጠየቀ እንደሆነ | 0.35 |
| | ለ/ ከተሰጠ በኋላ የተጠየቀ እንደሆነ | 0.50 |
| ፲/ | መረጃ ለማግኘት ሲጠየቅ | 0.50 |
| ፲፩/ | ኮሊ. ለማስመለስ ወይም አድራሻውን ለመለወጥ ሲጠየቅ | 0.65 |
| ፲፪/ | በአስቸኳይ ለሚላክ ኮሊ. እጥፍ ይከፈላል | |
| ፲፫/ | በቀላል ለሚሰበርና ከባድ ለሆነ ኮሊ. ፖስታ በመቶ ሃምሳ በተጨማሪ ይከፈላል ። | |
| ፲፬/ | በየበስ ለሚላኩ ጥቅል ፖስታዎች ከሕዝቡ የሚከፈለው ገንዘብ ከዚህ በላይ ከተመለከተው በቀር ፣ በትራንዚት (ለሚያልፉባቸው አገሮችና ለሌላም አገልግሎት በተጨማሪ ይከፈልባቸዋል) ። ይህም በልዩ ሠንጠረዥ ተሠርቶ የፖስታ አድሚኒስትራሲዮን በየጊዜው እያሻሻለ የሚሠራበት ነው ። | |
| ፲፭/ | በአየር ለሚላኩ ኮሊ. ፖስታዎች በቁጥር ፲፬ ከተመለከተው በቀር የአየር ጭነት ዋጋ ይከፈላል ። | |

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፩/፲፯ (፲፱፻፶፰) ሕ· ፫፻፲፩ አን· ፯ ተሻሻለ ።

## የአገር ውስጥ የፖስታ አገልግሎት

### ምዕራፍ ፩ ።

### የደብዳቤዎች ፖስታ ።

| | | የኢ.ት/ብር |
|---|---|---|
| ፩/ | የፖስታ መልእክቶች | |
| | ሀ/ ፖስታ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ | |
| | ፩/ ለመጀመሪያው ፳ ግራም | 0.10 |
| | ፪/ በተጨማሪ ለሚቀጥለው ፳ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.05 |
| | ለ/ ፖስታ ቤቱ ካለበት ራቅ ብሎ በሚገኝ አውራጃ ውስጥ ሲሆን ፣ ከፖስታ አካባቢ ውጭ (ለሌሎች የአገር ክፍሎች) | |
| | ፩/ ለመጀመሪያው ፳ ግራም | 0.15 |
| | ፪/ በተጨማሪ ለሚቀጥለው ፳ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.05 |

www.chilot.me



| | | |
|---|---|---|
| ፪/ | የፖስታ ካርዶች | የኢት/ብር |
| | ሀ/ ፖስታ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ | |
| | ፩/ ለተራ የፖስታ ካርዶች | 0.05 |
| | ፪/ ለደርሶ መልስ ካርዶች | 0.10 |
| | ለ/ ከፖስታ ቤቱ አካባቢ ውጭ (ለሌሎች የአገር ክፍሎች) | |
| | ፩/ ለተራ የፖስታ ካርዶች | 0.10 |
| | ፪/ ለደርሶ መልስ ካርዶች | 0.20 |
| | ፫/ ለእጅ ጽሑፎችና ለሙዚቃ ጽሑፎች ልዩ ቅናሽ በማድረግ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.03 |
| | ፬/ በትምህርት ቤቶች አማካይነት ተማሪዎች ለሚላላኳቸው ደብዳቤዎች ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.03 |
| | ፭/ በከተማ ውስጥ አድራሻ ሳይኖርባቸው ለሚታደሉ የማስታወቂያ ጽሑፎች በልዩ ቅናሽ ለያንዳንዱ ጽሑፍ ወይም ጥራዝ ሲሆን ለ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.03 |
| | ፮/ ለጋዜጦችና ለመጽሔቶች ልዩ ዋጋ | |
| | (በፖስታ ሚኒስቴር ተመዝግበው መላኪያው አስቀድሞ ሲከፈል) | |
| | ሀ/ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.03 |
| | ለ/ ከጋዜጣው ጋር ለሚታደሉ ለታተሙ ጽሑፎች ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.05 |
| ፫/ | የንግድ ወረቀቶች | |
| | ፩/ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.05 |
| | ፪/ የሚከፈል አነስተኛ ዋጋ | 0.10 |
| ፬/ | ለታተሙ ጽሑፎች (ለእትሞች) | |
| | ፩/ ጠቅላላው ዋጋ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.05 |
| | ፪/ ለመጻሕፍትና ለተጠረዙ ጽሑፎች (በአታሚዎችና በትምህርት ቤቶች አማካይነት ሲላኩ) ልዩ ቅናሽ በማድረግ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.03 |
| ፭/ | ለዕውራን የሚሆኑ ጽሑፎች | በነፃ |
| ፮/ | የዕቃ ዓይነቶች (አሸንቲዩን) | |
| | ፩/ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.05 |
| | ፪/ ለሚከፈል አነስተኛ ዋጋ | 0.10 |

www.chilot.me



| | | የኢ.ት/ብር |
|---|---|---|
| ፯/ | **ትንንሽ የደብዳቤ ፓኬቶች** | |
| | ፩/ ለያንዳንዱ ፶ ግራም ወይም ለክፍያው | 0.10 |
| | ፪/ የሚከፈል አነስተኛ ዋጋ | 0.30 |

## ለልዩ አገልግሎት በተጨማሪ የሚከፈል

| | | |
|---|---|---|
| ፰/ | ለአደራ (ሬኮማንዴ) ደብዳቤ ማስመዝገቢያ | 0.25 |
| ፱/ | **የፖስታ ዋጋ ሳልተከፈለበት ወይም በከፊል ለተከፈለበት ፖስታ** | |
| | ሳይከፈል የቀረው በእጥፍ ይከፈላል ። | |
| ፲/ | ፖስታ ወደ ሌላ አድራሻ ሲመራ | በነፃ |
| ፲፩/ | **ለአስቸኳይ (ኤክስፕሬስ) ፖስታ** | |
| | ፩/ የፖስታ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ሲታደል | 0.50 |
| | ፪/ ከከተማው ክልል ውጭ ለየ፳ ኪሎ ሜትር ወይም ለክፍያው በተጨማሪ | 0.50 |
| ፲፪/ | **ፖስታው ለመድረሱ የደረሰኝ ሲጠየቅ** | |
| | ፩/ ደብዳቤው በሚላክበት ጊዜ የተጠየቀ እንደሆነ | 0.25 |
| | ፪/ ደብዳቤው ከተሰጠ በኋላ የተጠየቀ እንደሆነ | 0.50 |
| ፲፫/ | **የተላከ ፖስታ እንዲመለስ ወይም አድራሻው እንዲለወጥ ሲጠየቅ** | |
| | ፩/ ጥያቄው በፖስታ እንዲላክ የተፈለገ እንደሆነ | 0.40 |
| | ፪/ ጥያቄው በቴሌግራም እንዲላክ የተፈለገ እንደሆነ (ከቴሌግራሙ ኪሣራ በቀር) | 0.40 |
| ፲፬/ | **የፖስታ ተቀባይ አድራሻ ተለውጦ ሲገኝ ወደ ተለወጠው ለመምራት** | በነፃ |
| ፲፭/ | **የፖስታ ሣጥን ኪራይ** | |
| | ፩/ ለአነስተኛ ሣጥን በዓመት | 12.00 |
| | ፪/ ለመሀከለኛ ሣጥን በዓመት | 18.00 |
| | ፫/ ለከፍተኛ ሣጥን በዓመት | 24.00 |
| | ፬/ ለያንዳንድ ተጨማሪ የሣጥን ቁልፍ | 2.00 |
| | ፭/ ቁልፍ ሲጠፋ መደቡን ለመለወጥ | 8.00 |
| ፲፮/ | **ስለተላከ ፖስታ ጥያቄ ወይም መረጃ ሲፈለግ** | 0.30 |
| ፲፯/ | ለአየር መልእክት (ለኤሮግራም) የሚከፈል | 0.10 |

